# አድቫንስ በቡድን የማብቃት አገልግሎት መምሪያ

Advance Group Mentoring Guide

የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የተወሰዱት ከአዲሱ መደበኛ ትርጉም (ኢ.መ.ት) የእንግሊዘኛው ቅጂ ከኒው ኢንተርናሽናል ቨርሽን የተወሰደ፤ ኮፒ ራይት 1973፣ 1978፣ 1984፣ 2011 በቢብሊካ ኢንተ. በዞንደርቫን ፈቃድ ጥቅም ላይ የዋለ። በዓለም አቀፍ ደረጃ ሙሉ መብቱ የተጠበቀ www.zondervan.com.

የተጻፈው በቤን ጃክ

2019 The Message Trust

# ማውጫ

እንኳን ወደ አድቫንስ በደህና መጣችሁ

የትምህርቱ መምሪያ

1. የአድቫንስ ክፍል መግቢያ
2. የወንጌላዊ ማንነት
3. የወንጌላዊው መልዕክት
4. የወንጌላዊው ተግባር
5. የወንጌላዊው ኃይል
6. የወንጌላዊው ግላዊ የጥሞና ጊዜ
7. የወንጌላዊው መገዛት
8. የወንጌላዊው ባህርይ
9. የወንጌላዊው መልካም ዕድል
10. የወንጌላዊው መሰጠት
11. የወንጌላዊው ተነሣሽነት
12. የአንድነት ጊዜ

# ተጨማሪ ትምህርቶች እና ግብዓቶች

-----------------------------------------------------------------------------------------------------

ተጨማሪ ትምህርቶች፡- በውይይት መልክ ወንጌልን መመስከር

ተጨማሪ ትምህርቶች፡ ክርስትናና ምካቴ-እምነት

ተቀጥላ፡-፡ የወንጌል አስተምሮ

ተቀጥላ፡- የወንጌል ትረካ

ተቀጥላ፡- የዐሥር ደቂቃ የወጣቶች የወንጌል ውይይት ተምሳሌት

ተቀጥላ፡- የወንጌል ዝየዳ መንገዶች

ተቀጥላ፡- “አንድ-ጉዳይ” የተባሉ መጣጥፎች ስብስብ

የሚመከሩ ንባቦች ዝርዝር

የተጠያቂነት ጥያቄዎች

# እንኳን ወደ አድቫንስ በደህና መጣችሁ

የአድቫንስ ቡድኖች የወንጌላውያንን ጥሪ በማበረታታት እና በማሳደግ ወንጌልን ለመስበክ ያላቸውን ጥሪ ድጋፍ ያደርጋሉ።

የአድቫንስ ከወንጌላዊ አንዲ ሃውቶርን (The Message Trust: UK ) ዐሥራ ሁለት ሰባኪ ወንጌላውያንን ለማሳደግ እና ለማበረታታት ከዚያም ሌሎች ልምድ ያላቸውን አገልጋዮች ይህንን እንዲሠሩ በማደፋፈር - በሥልጠናው ውስጥ የሚያልፉት የራሳቸውን ቡድን እንዲይዙ ለማበረታታት ባለው ራዕይ የተጀመረ ነው።

ወርሃዊ በሆነው ስብሰባዎች ቡድኑ በትምህርት፣ በውይይት እርስ በእርሳቸው እየተቀራረፁ እንዲሁም የግል እና መንፈሳዊ ሕይወታቸውን በግልጽ ይከፋፈላሉ። አዳዲስ መረጃዎች መደበኛ በሆነ መልኩ (ኂትስአፕ ወይም ተመሳሳይ የሆኑትን በመጠቀም) አንዳቸው ከሌላኛቸው ጋር ባሉት የቡድን ክፍለ-ጊዜያት ይለዋወጣሉ። ይህም፣ ስለ ዕድሎች እና ወንጌልን ለማካፈል የቻሉባቸውን ግንኙነቶችን እና በእነዚህ ዕድሎች የመጣውን ፍሬ የሚከፋፈሉበት ነው።

ከአንድ አመት የቡድኑ ቆይታ በኋላ የአድቫንስ ቡድን አባላት እያንዳንዳቸው ሌላ ዐሥራ ሁለት ሰው በማግኘት ይህንን የምክር ሥልጠና በተመሳሳይ ሁኔታ ይሰጣሉ። አድቫንስ መስካሪዎችን (ወንጌላውያን) ሌሎች ወንጌላውያንን እንዲያሳድጉ አላማ ያደረገ ሲሆን እርሱም በዕለታዊ ሕይወት ውስጥ ከቤተሰቦቻቸው፣ ጓደኞቻቸው እና ለሌሎች በሚያገኙት መድረክ ላይ ባለማፈር ወንጌልን የሚሰብኩ ሰዎችን በምድር ላይ ለማብዛት ይሠራሉ።

በዓለም ዙሪያ በሚበዛ ጊዜ፤ አድቫንስ ያለዕፍረት በፍቅር የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌልን ለመናገር የሚወዱትን ሁሉ ለማስታጠቅ፣ ለማበረታታት እና ለመደገፍ ላለው ፍላጎት የተሰጠ ቀጥተኛ ምላሽ ነው።

# የእንቅስቃሴው አምስት ዋና መርኾች

......................................................

የአድቫንስን ቡድኖችን በመመሥረት ሂደት ላይ እነዚህ አምስት መርኾች የማንደራደርባቸው መሆን አለባቸው

1. ***መደበኛ መሰባሰብ***
   በቡድን አባላት መካከል ያለው ወርሃዊ መሰባሰብ ማስታወሻ ላይ ቅድሚያ የሚሰጠው መሆን አለበት። ሰዎች ቡድኖችን ሲቀላቀሉ፣ በስብሰባዎች ላይ ለመገኘት መወሰናቸው አስፈላጊ ነው። እነዚህ ስብሰባዎች "መንፈሳዊ " እንደሆኑ በማስገንዘብ የሚቀላቀሉት ሰዎች የተጋበዙበት መድረክም ሆነ ስብሰባዎች "የበለጠ አስፈላጊ" መሆናቸው በበጎ እንዲታሰብ እንጂ ከስብሰባዎች ሊያሸሿቸው አይገባም። እግዚአብሔር ለጠራቸው ሥራ ራሳቸውን ለማዘጋጀት መሰጠታቸው ከምንም በላይ አስፈላጊ ነው።
2. ***መቀራረጽ***
   በእያንዳንዱ ወር ስብሰባ ላይ ወንጌልን በጥልቀት ለመረዳት ሲሉ የእግዚአብሔር ቃል ለማጥናት ያላቸው መሰጠት የስብሰባውን አብዛኛውን ሰዓት መውሰድ አለበት፤ ደግሞም፣ በውይይት ውስጥ እርስ በእርሳቸው ስለወንጌል እና አሰባበክ ያለቸው መረዳት እና አተገባበር ጤነኛ የሆነ መገማገምን መፍጠር አለበት።
3. ***ተጠያቂነት***
   ወንጌልን እንደሚገባ ለመኖር እና ለመስበክ፣ እንዲሁም ተጠያቂነት እና ቅድስና ያለበትን ኑሮ ለማረጋገጥ እውነተኛ የሆነ ግለ-ሂስ በግምገማ መጠይቅ እና በቡድን ስብሰባዎች ላይ ለማከናወን በምናደርጋቸው ግልፅ ውይይቶች አማካኝነት ተዘጋጅቷል። ግልጥነት እና እውነተኝን በቡድን ውስጥ ለማደግ ጊዜ የሚወስዱ ሲሆኑ የቡድኑ መሪ ሊያበረታታቸው እና በአርአያነት/ምሳሌነት ሊያሳያቸው ይገባል።
4. ***ተግባቦት***
   የቡድኑ አባላት የደረሱባቸውን የስብከት ጥሪዎች፣ የጸሎት ጥያቄዎች እና የድነት ምስክርነቶች ከሌሎች ጋር በኢሜል እና በፅሁፍ መልዕክት በመነጋገር በፈጠሩት የመስካሪዎች/ወንጌላውያን ቤተሰብነት ሊበረታቱ ይገባል። በስብሰባዎች መካከል ባሉት ጊዜያት በተለያየ መልኩ በመገናኘት ቤተሰባዊነታቸውን ሊያጠናክሩ ይገባል።
5. ***መባዛት***
   ባሉበት ቡድን ውስጥ ሆነው ሳለ፣ ሌሎች ሰዎችን በመያዝ በመጀመሪያዎቹ የአባልነት 12-18 ወራት ወስጥ የራሳቸውን ቡድን ለመያዝ የመባዛትን ሃሳብ መጀመር አለባቸው (ባሉበት ቡድን መሳተፋቸውን መቀጠላቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ማለት ነው)። በቡድኑ ውስጥ ያሉት አባላት በሙሉ የራሳቸው ቡድን ላይመሰርቱ ይችላሉ፤ ነገር

ግን ይህንን መምርያ በመጠቀም እና በሚገባ ስለጉዳዩ በማሰብ ብዙዎች ሌሎች ክርስቲያኖችን ለወንጌል ሥራ መሰጠታቸውን እንዲያድግ እና ቀጥሎ በምድር ዙሪያ ሁሉ እንዲሰፋ ሊያስታጥቁ እና ሊያበረታቱ ይችላሉ።

## ይህ ለእኔ ይሆናልን?

..............................................................

በመድረክ ላይ ወንጌልን የመስበክ ዕድል ያላችሁ ወይንም በዕለታዊ የግል ግንኙነት ውስጥ ወንጌልን ለመስበክ በልባችሁ  የሞላ ሆናችሁ እንደ ሆነ፣ እነዚህ ሦስት ቀላል ጥያቄዎች አድቫንስ ማጥኛ መጀመር እንዳለብህ/ሽ ለመወሰን ይጠቅሟችኋል።

**እምነት**

ወንጌል ጉልበቱን እንዳላጣ እና አሁንም ሰው እውነተኛ ሕይወት እና መዳንን ሊያገኝበት የሚችልበት መንገድ መሆኑን ታምናለህ/ሽ?

**ግልፅነት**

በመድረክ ስብከት ሆነ በግል ተግባቦት ወቅት ወንጌልን በግልጽ መናገር ትፈልጋለህ/ጊያለሽ?

**መጋበዝ**

ወንጌል ያለውን ተስፋ ሰዎች እንዲቀበሉ እና ከኢየሱስ ጋር ዘላለማዊ  ወደ ሆነ ግንኙነት ሲገቡ ለማየት እንድትጋብዟቸው ትናፍቃላችሁ?

ለእነዚህ ጥያቄዎች ምላሻችሁ አዎን ከሆነ፣ ሌሎች ምላሻቸው አዎ የሆኑ ሰዎችን በመሰብሰብ ይህንን የአድቫንስ የቡድን ማሳደግ መምሪያ በመጠቀም ጉዞውን አብራችሁን መጀመር ትችላላችሁ።

### የክፍለ--ጊዜው መምሪያ

....................................................................

የአድቫንስ ቡድን አባላት እንደመሆናችሁ፣ ይህ መምሪያ የመጀመሪያውን አመት የቡድን ጉዞ መጠቀም የሚያስችሉ 12 ክፍለ-ጊዜያት አሉት። በአገልግሎት ለብዙ ዘመን ልምድ ካለህ/ሽ እና ይህንን አይነት ክፍለ-ጊዜ የመምራት ልበ-ሙሉነት ሲኖርህ/ሽ ባለህ/ሽበት ቡድን ውስጥ ክፍለ-ጊዜን እንደ መንደርደሪያ መጠቀም፣ ባለው ይዘት ላይ መጨመር እና ላለህ/ሽበት ቡድን ፍላጎት በሚመጥን መልኩ በማመቻቸት ዕውቀትህ/ሽን እና ልምምድህ/ሽን ማካፈል ትችላለህ/ያለሽ። ለዚህ ሁሉ አዲስ ከሆንክ/ሽ ይህንን ይዘት ቃል በቃል እና መመርያ በመመርያ በመከተል ለማደግ የሚያስፈልግህ/ሽን በቡድን ውስጥ ማግኘት ትችላለህ/ያለሽ።
ዐሥራ ሁለቱ ክፍለ-ጊዜያት ወንጌል ሥርጭትን እና የወንጌላዊው ባሕርያትን የሚያስረዱ ናቸው። ክፍለ-ጊዜዎቹ የወንጌላዊን አምስት ባህርያትን ለማስረዳት በሚያስችል መልኩ የተከፋፈሉ ሲሆኑ ከመግቢያው በኋላ ይጀምራሉ።

### የወንጌላዊው መሠረታዊ ባሕርያት

....................................................

**መጽሐፍ ቅዱስን የሚያስተምሩ ወንጌላውያን፡- ወንጌልን በጥልቀት መረዳት** (**ሁለት፣ ሦስት፣ እና አራተኛ ክፍለ-ጊዜያት**)

የምንሰብከውን የወንጌል መልእክት በሚገባ እና በጥልቀት ማወቅ አለብን። የምንሰብከው ወንጌል ከራሳችን ሃሳብ ወይም አመለካከት የተወለደ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ቃል በትክክል የተማርነውን ለማድረግ የእግዚአብሔርን ቃል ለማንበብ እና ለማጥናት መሰጠት አለብን። ኢየሱስ ያስተማረንን ለሌሎች በማስተማር ደቀመዛሙርት ለማድረግ በማቴዎስ 28 የተሰጠንን ተልዕኮ ለመፈፀም መሥራት አለብን። መጠራታችን አመለካከቱን (Opinion) መሠረት አድርጎ የሚያስተምር  ወንጌላዊ እንድንሆን ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስን የሚያስተምር ወንጌላዊ ለመሆን ነው። እነዚህ ሦስት ክፍለ-ጊዜያት መጽሐፍ ቅዱስ ወንጌል እና ወንጌላዊነትን ከእግዚአብሔር አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ አንፃር ምን እንደሚያስተምርን የምንመለከትባቸው ክፍለ-ጊዜያት ናቸው።

**የሚጸልዩ ወንጌላውያን፡- በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚከናወን ተግባር (አምስት እና ስድስተኛ ክፍለ-ጊዜያት)**
*ሰዎችን ወደ ድነት የሚያመጣው የራሳችን ኃይል ሳይሆን የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ስለ ሆነ ለወንጌል ሥርጭት ሥራና ለመንፈስ ቅዱስ ኃይል ራሳችንን ማስገዛት ይኖርብናል። ስለሆነም፣ ወንጌልን የምንሠራበትን እና የሰዎችን ለውጥ ልናይበት የምንችልበትን ዕድል እንዲሰጠን በጸሎት ወደ እግዚአብሔር በሚተጋ ሕይወት መቅረብ ይኖርብናል። እነዚህ ክፍለ-ጊዜያቶች የወንጌላዊው የግል መንፈሳዊ ሕይወት ላይ በማተኮር ጠንካራ የግል መንፈሳዊ ሕይወት ያለውን ተፅዕኖ ይመረምራሉ።*

**ተጠያቂነት ያለው ወንጌላዊ፡- ቅድስና ያለው ሕይወት መኖር (ክፍለ-ጊዜ ሰባት እና ስምንት)**
*ቅድስና የወንጌል ማዕከል ነው። ተዐማኒነት ያለው እና ለውጥን ማምጣት በሚችል መልኩ ወንጌልን ለማካፈል ተጠያቂነት ያለበት ሕይወት አስፈላጊ ነው። መድረክ ላይ ያለው ሕይወታችን ከመድረክ በታች ካለው ሕይወት ጋር መመሳሰል አለበት። ይህንን ቅዱስ ሕይወት በመምራት ውስጥ ለማደግ ድሎቻችንን በጋራ የምናከብር እና በድካማችን ጊዜ አብረን የምንቆም በመሆን ማደግ አለብን። እነዚህ ክፍለ-ጊዜያት ኢየሱስን በሚያገለግሉት ወንጌላዊያን ሁሉ ቅድስና ላይ በማተኮር ተጠያቂነትን እና ትሕትናን ዋና ባሕርያት ለማድረግ ይሠራሉ።*

**የተሰጡ ወንጌላዊያን፡- ለሥራው የሚገባውን ትኩረት በእሳቤ መስጠት (ክፍለ-ጊዜ ዘጠኝ እና ዐሥር)**
*እሳቤ (አስቦበት ማድረግ) ለአገልግሎት አስፈላጊ ነገር ነው። ዕለታዊ የሆነ ሕይወታችን የእግዚአብሔርን ፍቅር እና የክርስቶስ ሕይወት ለማካፈል ብቻ ሳይሆን ሰዎች ይህንን መልእክት በመስማት የመልእክቱን ሕይወት እንዲቀላቀሉ ለመጋበዝ ጭምር መሆን አለበት። እነዚህ ሁለት ክፍለ-ጊዜያት ለወንጌላዊነት ያሉትን ሁለት መመዘኛዎች እንመለከትባቸዋለን። እነርሱም፡- በየዕለቱ ወንጌል በድፍረት ለመስበክ የሚያስችል እየጨመረ የሚሄድ ዕድል እና በእያንዳንዱ ወንጌልን የመስበክ ዕድል ማጠቃለያ ላይ ሰዎችን ወደ ወንጌል የመጥራት ፈቃደኝነት ናቸው።*

**የሚያነቃቁ ወንጌላዊያን፡- ቤተ ክርስቲያንን ለወንጌል ሥርጭት የሚያነሳሣ (ክፍለ-ጊዜ ዐሥራ አንድ)**
*ወንጌል ለሚያስፈልገው ዓለም ስንሰብክ ቤተ ክርስቲያንም ይህንን እንድታደርግ ልናነቃቃት ይገባል። ወንጌል ሥርጭት የሁሉም ክርስቲያን ሥራ ነው፤ ስለዚህም እያንዳንዱ ወንጌላዊ ቤተ ክርስቲያንን ለዚህ ሥራ የሚያነቃቃ መሆን አለበት። ይህ ክፍለ-ጊዜ ወንጌላዊው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን የክርስቲያን የወንጌል ምስክርነት ማነቃቃት ዋና አላማው መሆን አለበት።*

*በዐሥራ ሁለተኛው ክፍለ-ጊዜ አድቫንስ የዓመቱን ትምህርት የሚያጠናቅቅበት እና የቡድኑ አባላት የዕረፍት እና የምልከታ ጊዜ የሚወስዱበት ይሆንላቸዋል። ይህ ለራሳቸው በቂ ጊዜ ወስደው በዓመቱ ውስጥ የተማሩትን የሚመለከቱበት እግዚአብሔር በሕይወታቸው የሠራውን ሥራ የሚመለከቱበት እና አብረው ወደ ፊት የሚሆነውን የሚያቅዱበት ጊዜ ይሆናል።*

## ቡድን መምራት

**.........................................................................**

*ወርሃዊ በሆነ መልኩ ዐሥራ ሁለት አባላት ያሉበት ቡድን (አንድ አይነት ፆታ ያላቸው ሰዎች መደራጀታቸው ለተጠያቂነት ይጠቅማል) ለሁለት ሰዓታት ያክል እንዲገናኙ አበረታቷቸው። በእነዚህ የመገናኘት ጊዜያት ውስጥ የቡድን መሪው ክፍለ-ጊዜውን ያሳልጣል። ይህም ጸሎት፣ ትምህርት፣ ውይይት፣ እና ተጠያቂነትን ያካትታል። ይህ መምሪያ ለአንድ አመት ለቡድን ውይይት የሚያስፈልገው ሁሉ አለው።*

**የክፈለ-ጊዜያቱ አከፋፈል**
የእያንዳንዱ ክፍለ-ጊዜ መምሪያ በአጭር መግቢያ ይጀምራል። እንዲሁም **ክፍለ-ጊዜውን በአንድ ዐረፍተ-ነገር** ይዘረዝራል።

**የክፍለ-ጊዜው ዳራ ሰጪ** ክፍል የዕለቱ ይዘት የሚያተኩርበት ሀሳብ ላይ ትምህርት ይሰጣል። ስለ ክፍለ-ጊዜው የጠለቀ መረዳት እንዲሰጥህ/ሽ እና ክፍለ-ጊዜው ሁናቴ ለመረዳት፤ ክፍለ-ጊዜውን ከመምራታችሁ በፊት ይህንን

ቀድሞ ማንበብ ያስፈልጋል። አስፈላጊነቱ ከታመነበት እና በቂ ጊዜ ካለ ይህንን በዋናው ይዘት ላይ ማካተት ይቻላል። ነገር ግን በዋናነት ቀጣዩን ክፍለ-ጊዜ ለመምራት እንዲያስችል የተዘጋጀ ነው።

ከዚህ የእያንዳንዱን ክፍለ-ጊዜ መምሪያ መከተል ይቻላል። ከይዘት እስከ ሰዓት አጠቃቀም (ለእያንዳንዱ ክፍለ-ጊዜ ንዑስ ክፍል በኋላ በቅንፍ አጠገቡ ይቀመጣል) የክፍለ-ጊዜው ዋና ሃሳብ እስከተዳሰሰ ድረስ ይዘቱን መሪው በሚያስልገው መጠን መከተል ይችላል። ደግሞም አብሮ የመጸለይ እና የተጠያቂነት ቦታ አለ። ነገር ግን፣ ከመምሪያው የላቀ ጥቅም ለማግኘት የተሰጠውን መመሪያ በትክክል እና በቅርበት መከተል ያስፈልጋል።

እያንዳንዱ ክፍለ-ጊዜ **የከለሳ** ጊዜ አለው። የመጀመሪያዎቹ ክፍለ-ጊዜያት ላይ አንዳቸው ከሌላኛቸው ጋር ለመተዋወቅ እና ቡድኑ እንዴት አብሮ መሥራት እንደሚችል ለመለየት የሚወስድ ጊዜ ነው። ወደ ኋላ የሚመጡት ክፍለ-ጊዜያት ላይ የትምህርቶችን አጠቃቀም እና አተገባበር ግምገማ እና እርስ በርስ ያጋጠመውን ለመነጋገር መጠቀም ይቻላል።

ቀጠሎ **የጸሎት** ጊዜ ነው። ይህ ምን ያህል ሰዓት መጸለይ እንዳለበት እና በምን አይነት መንገድ መጸለይ እንዳለበት ቡድኑ ይወስናል እንጂ በእርግጥ ትክክለኛ ወይም የተሳሳተ የሚባል አካሄድ የለውም። ለአጭርም ሆነ ለረጅም ጊዜ፣ እንዲሁም በሙሉው ቡድንም ሆነ ከባልንጀራ ጋር መጸለይ ይቻላል።

ዋናው **የማስተማር** ጊዜ ይቀጥላል። ይህም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን፣ ሌሎች ሰዎች የተናገሩትን እና **የውይይት ጥቄዎችን** የያዘ ነው። ይህ ጊዜ የሚወስደውን ሰዓት በጥንቃቄ መመልከት ይኖርብናል ምክንያቱም ከዚህ በኋላ የውይይት እና በክፍለ-ጊዜው መጨረሻ የተጠያቂነት ጊዜ ይኖራል። በማያስፈልግ መልኩ ትምህርቱ ላይ ረጅም ሰዓት በማተኮር ለሌሎች መርሃ ግብሮች ሰዓት መውሰድ የለብንም (እንዲሁም ከአንደኛው ክፍለ-ጊዜ ሌላኛው ለትምህርት የሚያስፈልገው ጊዜ ስለሚለያይ፣ በጥቆማ የተሰጠውን ሰዓት መመልከት ተገቢ ነው)።

ከትምህርቱ በኋላ **የውይይት** ጊዜ ይኖራል። ይህም ጥቂት የውይይት ጥያቄዎች እና ከክፍለ-ጊዜው ጋር የሚዛመዱ የሰዎች አባባሎችን የሚያካትት ሲሆን ከትምህርቱ በኋላ የውይይት ጊዜ ይኖራል። ሁሉንም ጥያቄዎች ለመወያየት የምትችሉበት በቂ ጊዜ ላይኖር ይችላል። ነገር ግን ለይዘቱ ከሚያስፈልገው በላይ ጥያቄ ያካተትን ሲሆን፣ ያስፈልጋል ብላችሁ የምታምኑበትን ብቻ መጠየቅ ትችላላችሁ። ያለውን ሁሉ ለማካተት ከመሞከር ይልቅ ያስፈልጋል ብላችሁ የምታምኑትን ብቻ ተጠቀሙ።

እያንዳንዱ ክፍለ-ጊዜ በመጨረሻው ላይ **ማዛመድን** የሚያካትት ሲሆን፤ ይህም በትምህርቱ መሠረት ከአሁኑ ክፍለ-ጊዜ እና በሚቀጥለው ክፍለ-ጊዜ መካከል መሠራት ያለበት ነው። ቡድኑን የሚያሳድግ እና ከትምህርቱ ጋር የሚሄድ እስከ ሆነ ድረስ የማዛመድን ሃሳብ መሪው ከራሱ አፍልቆ ማስጠናት ይችላል።

ሌላ **የጸሎት** ጊዜ ይቀጥላል። ይህ፣ በትምህርቱ መሠረት የሚመራ ጸሎት ይሆናል። ነገር ግን፣ እንዴት እና ለምን ያህል ሰዓት እንደሚጸለይ መወሰን ይኖርበሃል/ሻል።

በመጨረሻ፣ እያንዳንዱ ክፍለ-ጊዜ **በተጠያቂነት** ጊዜ ይጠናቀቃል። ራስን-መገምገሚያ ቅጾች የሚሞሉ፣ የሚከፋፈሉ እና የሚጸለይባቸው ይሆናል። የግምገማ ቅጾችን ከገፅ ___ ላይ በመውሰድ ወይም advance2020.org/accountability በመሄድ የPDF ኮፒ ማውረድ ይቻላል።

ለሚቀጥለው ክፍለ-ጊዜ የመሰባሰቢያ ቀን ያልተወሰነ ከሆነ፣ ይህንን ክፍለ-ጊዜ ከመጨረሳችሁ በፊት ቀን ወስኑ። በመልዕክት ከመነጋገር እና መወሰን ይልቅ በአካል መወሰን የተሻለ ነው።

**በፈቃደኝነት የሚሠራ፡- የክፍለ-ጊዜያቱ ዋና ዋና ነገሮች**

**ልዩ የጸሎት ትኩረት**

በእያንዳንዱ ክፍለ-ጊዜ ላይ ለተለያዩ ግለሰቦች ለህይወታቸው፣ ለቤተሰባቸው፣ ለአገልግሎታቸው እንዲሁም ለሚሰጡት የትኛውም ርዕስ ቡድኑ ይጸልያል። በእያንዳንዱ ሦስት ስብሰባ ለሁሉም ለመጸለይ ይሞክር፤ ከዚያ በድጋሚ መጀመር።

**ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች**

የተሰጡትን ትምህርቶች እና በውይይት ጊዜ የነበረውን ሀሳብ ከጸሎት ጋር በመጠቀም በግል ወይም በቡድን ሆኖ ለአንድ ሰዓት ምስክርነት መውጣት። ቡድኖቹ ለምስክርነት እንድንዘጋጅ ሊያደርጉን የተቀረፁ ናቸው። ነገር ግን፣ ምስክርነትን መለማመድ ከተፈለገ ጊዜ መስጠት ይቻላል። ከእነዚህ እንቅስቃሴዎች በኋላ የውሎ ሪፖርት መግለጫ እና ግምገማ መስጠት አለበት።

**እንግዶች**

ለቡድኑ በትምህርት ወይም በውይይት ጊዜ የሚያውቁትን እንዲያካፍሉ ወይም የራሳቸውን የግል ልምምድ እንዲያጋሩ አሊያም የተለየ አዲስን ነገር ለማምጣት የሚፈልጉ ተናጋሪዎችን ወይም እንግዳ ማግኘት የምትችሉ ከሆነ ለቡድኑ መጋበዝ ትችላላችሁ።

**ቡድን ለመምራት የሚጠቅሙ ሃሳቦች**

የስብሰባ ጊዜን ከረጅም ጊዜ በፊት በመወሰን (ከተቻለ ከስድስት ወር በፊት) እነዚህን ጊዜያት በተቻለ መጠን እንዳይቀየሩ ለመሥራት **doodle.com**ን የመሰለ መሣሪያ በመጠቀም የስብሰባ ጊዜን ማቀድ ይቻላል።

**WhatsApp** ወይም ተመሳሳይ የጽሑፍ መልዕክት መላላኪያ መሣሪያዎች ለቡድን ተግባቦት፣ የጸሎት ርዕሶችን እና የዳኑ ሰዎች ምስክርነቶችን ለመመልከት አመቺ ናቸው። እንደ ቡድን መሪ የተቻላችሁን ያህል በማበርከት ለተግባቦት መሳለጥ የምትችሉትን አድርጉ። የራሳችሁን ታሪክ አካፍሉ፣ ሰዎችን የጸሎት ርዕስ ካላቸው ጠይቁ፣ እንደ ዩቲዩብ ያሉ ተጨማሪ ግብዓት መገኘት የሚችልባቸውን መንገዶች መጠቀምም ትችላላችሁ። እናንተ ለውጥን መምራት ከቻላችሁ ሌሎች በተሳትፎ ይከተሏችኋል።

ሰዎችን ለማሰባሰብ **ምግብ** በጣም ጥሩ የሆነ መንገድ ነው። በመሆኑም፣ ክፍለ-ጊዜዎቹን ከሻይ ቡና፣ ከዳቦ፣ ኩኪስ ጋር በማቀናጀት መሥራት ትችላላችሁ።

በተቻለ መጠን ቀደም ብላችሁ የቡድናችሁ አባላት **የራሳቸውን ቡድን መመሥረት** እንዲያስቡ አበረታቷቸው። እንዲሁም ሌሎች የእናንተ ቡድን አባላት የነበሩ ሰዎች የመጀመሪያዎቹ ጊዜያት ላይ አርፍደው መቀላቀል ካልቻሉ፣ አዳዲስ የቡድን አባላት የሚመሠርቱ ቡድኖችን እንዲቀላቀሉ አበረታቷቸው።

በተጠያቂነት ጊዜያት ላይ ለውይይት፣ ለጸሎት እና ለመከፋፈል አባላትን የሚመቻቸውን ቦታ ፈልጉ። ለአንዳንዶች ካፌ የሚመች ሲሆን፣ በአድቫንስ ጉዞ ላይ የራሳቸውን ሚስጢራዊ ቦታ የሚፈልጉ ስለሚኖሩ የተመቸ ቦታን በጥንቃቄ አመቻቹ።

# የክፍለ-ጊዜው መምሪያ

**ክፍለ-ጊዜ አንድ፡**

**እንኳን ወደ አድቫንስ በደህና መጣችሁ**

***የመጀመሪያው የቡድን ስብሰባ እርስ በርስ ለመተዋወቅ፣ ቡድኑ ሊሆን የሚገባውን ማንነቱን እና ቅርጹን ለመወሰን እና ወንጌላዊነት ምን እንደ ሆነ እና ባህርያቱን መነጋገር ለመጀመር መልካም እድል እንደ ሆነ ተደርጎ ልትጠቀሙበት ይገባል።***

**ክፍለ-ጊዜው በአንድ ዐረፍተ-ነገር ሲጠቃለል**

........................................................................

በአድቫንስ ትምህርት አማካኝነት በወንጌላዊው አምስቱ ባሕርያት ውስጥ አብረን እያደግን በመደጋገፍ እና ለመታነጽ ለሥራው በእግዚአብሔር ኃይል እየታመንን እናድጋለን።

**የክፍለ-ጊዜው ዳራ**

.......................................................................

ለወንጌል መጠራታችን ግላዊ እንደ ሆነ ማወቅ ይህንን የአድቫንስ ጉዞ እና ስለ ወንጌላዊነት ያለውን ውይይት ለመጀመር አስፈላጊ ቦታ ነው። በማርቆስ ወንጌል መጀመሪያ ላይ (ማር. 1፡16-18) ኢየሱስ እንድርያስን እና ጴጥሮስን እንዴት እንደጠራቸው ተመልከቱ። ኢየሱስ እነዚህን ወጣቶች ለአገልግሎት በባህር ዳርቻ ላይ ሆነው ሲጠራቸው መረባቸውን (ሥራቸውን) ትተው እንዲከተሉት ነው። ኢየሱስ ራሳቸውን እነዚህን ቃላት ተጠቅሞ ዛሬ ላይ ጠርቶን ይሆን? እንደ ጴጥሮስ ባለ የሕይወት መንገድ ላይ ካልሆንን፣ ምናልባት እንደዚያ ላይሆን ይችላል። ነገር ግን፣ ኢየሱስ እነ እንድርያስን ሲጠራቸው፣ የአሳ አስጋሪነት ምሳሌ በመጠቀም ለግል ሕይወታቸው በሚሆን መልኩ ነበር የጠራቸው።

ወንጌላውያን እንድንሆን እግዚአብሔር እያንዳንዳችንን ሲጠራን በየግላችን ነው። በውስጣችን ያለውን ጥማት ከዕድሎች ጋር በማገናኘት የራሱ ማንነት ምን እንደ ሆነ ያስረዳዋል። ሙዚቀኛ፣ አርቲስት፣ ሳይንቲስት፣ ነርስ፣ የንግድ ባለሙያ ብትሆን - ሙያህም ሆነ ስጦታህ ምንም ቢሆን ምን፣ እግዚአብሔር ወንጌልን እንድንሠራ ዕድሎችን ይሰጣል።

የወንጌል ግብ ሰዎችን ከእግዚአብሔር የምሥራች መልዕክት ጋር ማገናኘት ነው። (እንጂ የደረሰንን እንድናገለግል) በዋናነት ደግሞ፣ የወንጌል መልዕክት ሰዎችን በክርስቶስ ኢየሱስ ወዳለው እምነት መጥራት ነው። እርሱም ክርስቶስን በመታመን እና በመታዘዝ ከአመፀኝነታችን ተመልሰን የክርስቶስን ጌትነት ለመቀበል ነው። ለእግዚአብሔር ለራሱ እንደተፈጠርን ሲገባን አምልኮ ምን ማለት እንደ ሆነ እንገነዘባለን። እንዲሁም የመንፈስ ቅዱስን የመለወጥ ኃይል በሕይወታችን እንለማመዳለን። በፍቅር፣ በእምነት፣ ራስን በመሰዋት እና በመታዘዝ በሚገለጥ የአምልኮ ሕይወት ውስጥ ያለው ሙላት ሰዎች መመልከት ይችላሉ (ገላ. 5፡13-26)።

በዘፀ. 8፡1 ላይ፣ ሙሴ ወደ ፈርዖን ሄዶ "ህዝቤን ልቀቅ ...." እንዲል እግዚአብሔር ያዘዋል። ዛሬም የእግዚአብሔር ፍላጎት ሰዎች ከኃጢአት ነፃ እንዲወጡ ነው። እኛም እንደ ሙሴ ወደ ዓለም በመሄድ የነፃነትን መልዕክት እንድንናገር ተልከናል። ሰዎች በኃጢአት ባርነት እንዳይኖሩ፣ ነገር ግን በነፃነት እንድንኖር እግዚአብሔር መንገድን አዘጋጅቶልናል (ሮሜ 8፡2)። የወንጌል ዓላማ ዛሬም ለሙሴ እና ለእስራኤል የተሰጠው ያው ዓላማ ነው።

"ያመልከኝ ዘንድ ህዝቤን ልቀቅ"

ሌሎች መጥተው ያመልኩ ዘንድ የምንመሰክር አምላኪዎች መሆን አለብን።

**የክፍለ-ጊዜው መምሪያ**

**የከለሳ ጊዜ (20-30 ደቂቃ)**

ይህንን ጊዜ በመውሰድ እያንዳንዳቸው የቡድን አባላት ራሳቸውን የሚያስተዋውቁበት እና እርስ በርሳችሁ የምትቀራረቡበት ጊዜ ይሁን። ሰዎች ዝምታ ሰብረው መነጋገር እንዲጀምሩ እንቅስቃሴ ማዘጋጀት ወይም በቡድን እየዞራችሁ እያንዳንዳቸው ራሳቸውን እንዲያስተዋውቁ ዕድል መስጠት አለባችሁ። በራሳችሁ መንገድ ወይም በገፅ______ ላይ ያለውን መግቢያ በመጠቀም ቡድኑ ምን እንደሚሠራ እና በሚቀጥሉት ወራት እንዴት እንደሚሚቀጥል አስረዱ።

**ጸሎት**

ጊዜውን ለእግዚአብሔር በመስጠት እና በትውውቅ ጊዜ በተነሣ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ጉዳይ ላይ ጸልዩ።

**ትምህርት (20-30 ደቂቃ)**

ራሳችሁ ልታቀርቡበት በምትችሉበት መንገድ ወይም ቃል በቃል ይህንን ትምህርት ማቅረብ ትችላላችሁ።

ነገር ግን ሩጫዬንና ከጌታ ከኢየሱስ የተቀበልሁትን አገልግሎት እርሱም የእግዚአብሔርን ጸጋ ወንጌልን መመስከር እፈጽም ዘንድ ነፍሴን በእኔ ዘንድ እንደማትከብር እንደ ከንቱ ነገር እቆጥራለሁ።

**ሐዋ. ሥራ 20፡24**

---

በቀላሉ ሲቀመጥ፣ “ወንጌልን መስበክ” ማለት “የምሥራችን መናገር” ማለት ነው። ይህ የምሥራች የክርስቶስ ወንጌል ነው። ይህም አመፀኛው ሰው ከእግዚአብሔር ጋር በክርስቶስ የማዳን ሥራ ስለመታረቁ ይናገራል። እኛ ይገባን የነበረውን ሞት ኢየሱስ በመውሰዱ የዘላለምን ሕይወት መቀበል እና ከእግዚአብሔር ጋር ፍፁም የሆነ ግንኙነት ማድረግ ችለናል።

የሚከተሉትን የወንጌል ሥርጭት ሁለት ትርጉሞችን ተመልከቱ፡-

“ወንጌል ሥርጭት ማለት **ክርስቶስ ኢየሱስን ለኃጢአተኛ ሰዎች በማቅረብ እምነታቸውን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል** በእግዚአብሔር ላይ እንዲያደርጉ ማድረግ ነው።”

**ጄ. አይ. ፓርከር**

“**በታሪክ እና በመጽሐፍ ቅዱስ** ውስጥ **የተገለጠውን ኢየሱስ እንደ አዳኝ እና ጌታ በመስበክ** ሰዎች ከእርሱ ጋር **ለመታረቅ በግላቸው** ወደ እግዚአብሔር እንዲመጡ **ማሳመን** ነው።”

**ቢሊ ግርሃም**

ጥያቄ

ከእነዚህ አጣሬዎች ስለ ወንጌል ሥራ ምን መማር እንችላለን (የደመቁት ቃላት ለውይይት እንዲሆኑ የተቀመጡ ናቸው።)

ወንጌልን መስበክ ማለት ከሞት የተነሣውን ክርስቶስ ሰሚዎች እንዲቀበሉ ለማሳመን መልዕክትን መናገር ማለት ነው። እነዚህ ቃላት አስፈላጊ ቢሆኑም ከቃላት ያለፈ ተግባቦት ያስፈልጋል።

ዴቪድ ዋትሰን እንደተናገሩት፣ "የመንፈስ ቅዱስ ኃይል መገለጥ ከሌለበት፣ ወንጌልን መናገር ባዶ ነው። ይህ ወንጌል ሥርጭት አይደለም።" ወንጌል ሥርጭት መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ሲሆን፣ እግዚአብሔር ከሌለበት ግን ስኬታማ ሊሆን አይችልም። የሰዎችን አመለካከት በመቀየር ብቻ ወንጌልን መሥራት የምንችል ቢሆን ኖሮ፣ ሰዎችን ለማሳመን ገለጻ ማድረግ በቂ ይሆን ነበር። ነገር ግን፣ ወንጌል መናገር ስለ ሰዎች መዳን የሚደረግ ነገር ነው። ለዚህም በመልክታችን ውስጥ እግዚአብሔር ሰዎችን ስለ ኃጢአት በመውቀስ፣ እምነትን በመስጠት ልባቸውን መቀየር ይጀምራል። ወንጌል ሥርጭት ከመንፈስ ቅዱስ ኃይል ውጪ ለሽያጭ የቀረበ ዕቃ ይሆናል። በሌላ መልኩ፣ ሊዮናርድ ራቨንሂል እንደተናገረው "የትኛውም የወንጌል ሥርጭት መንገድ እግዚአብሔር ካለበት የሚሠራ ነገር ነው።"

የወንጌል ሥርጭት ዓላማ በእውነት እና በመንፈስ የሚያመልኩ (ዮሐ. 4፡23) ደቀ-መዛሙርት ማፍራት ነው። በመሆኑም ወንጌላውያን ራሳቸው እውነተኛ የአምልኮ ሰዎች መሆን አለባቸው። ወንጌል ሥርጭት እና ደቀ መዝሙርነት የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ ናቸው - ለዓለም የምናገረው ወንጌል ራሱ አምልኮ ነው። ለንጉሡ ያለን መታዘዝ እና መስጠት ነው።

እነዚህ የአድቫንስ ቡድን ክፍለ-ጊዜያት እውነተኛ የአምልኮ ሰዎች ለመሆን እንድናድግ በመሥራት እና አምስቱን የወንጌላዊ ባሕርያት እንድናሳድግ ይረዱናል።

**መጽሐፍ ቅዱስን የሚያስተምሩ ወንጌላውያን (መስካሪዎች)**
የምንሰብከውን ወንጌል በሚገባ እና በጥልቀት ማወቅ አለብን። የምንሰብከው ወንጌል ከራሳችን ሃሳብ ወይም አመለካከት የተወለደ ሳይሆን፣ ከእግዚአብሔር ቃል በትክክል የተማርነውን ይህንን ለማድረግ የእግዚአብሔርን ቃል ለማንበብ እና ለማጥናት መሰጠት አለብን።

**የሚፀልዩ መስካሪዎች**
በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚያከናውኑ ሰዎችን ወደ መዳን የሚያመጣው የእኛ ኃይል ሳይሆን የእግዚአብሔር ኃይል ነው። በመሆኑም፣ ራሳችንን ለእግዚአብሔር ኃይል ማስገዛት ይኖርብናል። ትጉ ለሆነ የጸሎት ሕይወት በመሰጠት የእግዚአብሔርን ወንጌልን የምንሰብክበት መንገድ እና የሰዎች ሕይወት ተቀይሮ የምናይበትን ዕድል መጠየቅ አለብን።

**ተጠያቂነት ያለባቸው መስካሪዎች**
ቅድስና የወንጌል ማዕከል ነው። ተዓማኒነት እና ለውጥን ማምጣት በሚችል መልኩ ወንጌልን ለማካፈል ተጠያቂነት ያለው ሕይወት አስፈላጊ ነው። መድረክ ላይ ያለው ሕይወታችን ከመድረክ ውጪ ካለው ሕይወት ጋር መመሳሰል አለበት። ይህንን ቅዱስ ሕይወት በመምራት ውስጥ ለማደግ ድሎቻችንን በጋራ የምናከብር እና በድካማችን ጊዜ አብረን የምንቆም በመሆን ማደግ አለብን።

**የተሰጡ መስካሪዎች**
ታስቦበት በዓላማ መንቀሳቀስ ለአገልግሎት አስፈላጊ ነገር ነው። ዕለታዊ የሆነ ሕይወታችን የእግዚአብሔርን ፍቅር እና የክርስቶስን ሕይወት ለማካፈል ብቻ ሳይሆን ሰዎች ይህንን በመስማት ይህንን ሕይወት እንዲቀላቀሉ በመጋበዝ የደቀ መዝሙር ጉዞ እንዲጀምሩ ለመርዳት እድሎች ያሉባቸው መሆናቸውን መገንዘብ ይኖርብናል።

**የሚያነቃቁ መስካሪዎች**
ወንጌል ለሚያስፈልገው ዓለም ስንሰብክ፣ ቤተ ክርስቲያንም ይህንን እንድታደርግ ልንነቃቃ ይገባል። ወንጌል ሥርጭት የሁሉም ክርስቲያን ሥራ ነው። ስለዚህም፣ እያንዳንዱ ወንጌላዊ ቤተ ክርስቲያንን ለዚህ ሥራ የሚያነቃቃ መሆን አለበት።

***ጥያቄ - እነዚህን አምስት ባሕርያትን በመመልከት፣ እያንዳንዳችን ጥንካሬያችን እና ድካማችን የት ጋር እንደ ሆነ እንለይ።***

**ውይይት (15 ደቂቃ)**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች/አባባሎች ተወያዩባቸው**

- በወንጌል ሥርጭት ውስጥ የእኛ ኃላፊነት ምንድነው፣ የእግዚአብሔር ኃላፊነትስ ምንድነው?
- እውነተኛ ወንጌላውያን እና እውነተኛ የአምልኮ ሰዎች መሆናችንን በምን ማረጋገጥ እንችላለን
- በዚህ የአድቫንስ ቡድን ውስጥ በሚቀጥሉት ወራት እንዴት ማደግ ታስባለህ/ያለሽ?

"ኃጢአተኞች በፍርድ ኩነኔ ውስጥ ካሉ፣ ቢያንስ በእኛ ሰውነት ላይ በመዝለል ወደ ሲዖል እንዲገቡ እናድርግ። የሚጠፉ ከሆነ፣ በእጆቻችን ጉልበታቸውን ይዘን እንዳይሄዱ እየለመንናቸው ይጥፉ። ሲዖል የሚሞላ ከሆነ፣ ሕይወትን ለመስጠት ጥርሳችንን ነክሰን ለማትረፍ መትጋታችንን አልፎ ይሙላ። ስለዚም፣ ማንም ሳይነገረው እና ሳይጸለይለት አይግባ።"

**ቻርለስ ስፐርጀን**

**ትግበራ** (5 **ደቂቃ** )

*መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ (የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ማጣቀሻዎች ያሉበት ጭምር ቢሆን ይመረጣል) የወንጌል ሥርጭት ትርጉም ለሚቀጥለው ሳምንት የቡድን ውይይት እና ግምገማ ለማምጣት አዘጋጁ። የተጠቆሙትን ምንባቦችን መሠረት ማድረግ ትችላላችሁ።*

**ጸሎት**

እግዚአብሔር ስለ ሰጠን እስደናቂ ወንጌል አመስግኑት። በዚህ አስደናቂ ዓለምን የማዳን የወንጌል ሥራ አጋሮች ስላደረጋችሁ አመስግኑት። በእውነት እና በመንፈስ እያመለካችሁ፣ በሥራ እና በተግባር መልዕክተኞቹ መሆን እንድትችሉ ኃይልን እንዲያስታጥቃችሁ ለምኑት። እንዲሁም በዚህ የአድቫንስ ቡድን ውስጥ ስትቀጥሉ፣ በአምስቱ የወንጌላዊ ባሕርያት እንዲያሳድጋችሁ ለምኑት።

**ተጠያቂነት** (15 **ደቂቃ**)

የተጠያቂነት ቅጽ በመሙላት ለአጋራችሁ እና ለአነስተኛ ቡድናችሁ አካፍሉ፤ እንዲሁም አንዳችሁ ለሌላችሁ ጸልዩ።

**መልዕክቶች እና ቀናትን መወሰን** (10 **ደቂቃ**)

ይህንን ክፍለ-ጊዜ ሁሉም ሰው ሊጠቀምበት የሚችል የመልዕክት መላላኪያ መሣሪያ ማውረድ እና መጠቀም እንዲጀምሩ አበረታቱ። ኧትስአፕ/WhatsApp እንዲሁም የፌስ ቡክ ሜሴንጀር ይህንን ለማድረግ አመቺ ናቸው። እነዚህ ላይ አዳዲስ መረጃዎች፣ የጸሎት ጥያቄዎች፣ ምስክርነቶች እና ሌሎች መልዕክቶችን መላላክ ትችላላችሁ።

እንዲሁም፣ ለሚቀጥሉት ስብሰባዎች የምትገናኙባቸውን ቀኖች ወስኑ። በተቻለ መጠን ለሁሉም በሚያመች መልኩ ለስድስት ወራት ያህል መገናኘት የምትችሉባቸውን ቀናት አስቀድማችሁ በመወሰን በአጀንዳ ላይ ቅድሚያ ስጧቸው።

**ማስታወሻ**

**<u>ክፍለ-ጊዜ ሁለት</u>**

**<u>የወንጌላዊው ማንነት</u>**

**በሁለተኛው የቡድን ውይይት የወንጌላዊው ማንነትን ከእግዚአብሔር ማንነት እና የወንጌል ታሪክ ጋር በማዛመድ የምንዳስስ ይሆናል።**

**ክፍለ-ጊዜው በአንድ ዐረፍተ-ነገር ሲጠቃለል**

.............................................................................

የወንጌላዊው ማንነት በእግዚአብሔር ማንነት ውስጥ የተሰወረ ነው፤ እኛ በእርሱ የተላክን ልጆቹ ነን።

**የክፍለ-ጊዜው ዳራ**

.............................................................................

በቢሊ ግርሃም የአገልግሎት ዘመን ማገባደጃ ላይ ብዙ ወጣት ክርስቲያኖች የመልካሙ ዜና ሰባኪዎች ለመሆን ተነሳሥተው ነበር። ባለፉት ሃያ አመታት ውስጥ ወጣቶች የሚፈልጉት ነገር ላይ የምንመለከተው ለውጥ ተፈጥሯል። የወንጌል ሠራተኝነት በአንድ ወቅት በወጣቶች ዘንድ የሚፈለግ ቢሆንም፣ አሁን ግን ክርስቲያን ወጣቶች በዋናነት የወጣት አገልጋይ፣ የአምልኮ መሪ ወይም የቤተ ክርስቲያን መጋቢ መሆን ዋና ፍላጎታቸው ሆኗል።

በግልም ሆነ በቡድን አምልኮ ውስጥ በሙዚቀኝነት፣ በፊልም ሥራ እና ሌሎች የፈጠራ ሥራዎች በኩል አገልግሎቶችን አስተባብረዋል። በእነዚህም ታማኝ አገልጋዮች ሥራ እግዚአብሔር እጅግ ተወድሷል፣ ተከብሯልም። ነገር ግን፣ አንድ ሰው እውነተኛ አምልኮ፣ በመንፈስ እና በእውነት የሆነ አምልኮ ከማምለኩ (ዮሐ. 4፡3) በፊት፣ ወንጌልን ሰምቶ፣ ለሰማው ወንጌል ምላሽ መስጠት አለበት (ሮሜ 10፡14-17)።

በተመሳሳይ፣ የመጋቢው እና የአስተማሪው ደቀመዝሙር የማድረግ ሥራ ወደ ጎን ሊተው አይገባም። ነገር ግን፣ ወደ ዓለም ከሚወጣ ጠንካራ የወንጌል ሥርጭት እጥረት የተነሣ፣ የቤተ ክርስቲያኒቱ ወንበሮች ባዶ ቢሆኑ፣ መጋቢው የሚያስተምራቸው ሰዎች አይኖሩትም ማለት ነው።

ሰዎችን ወደ እውነተኛ የአምልኮ ማንነት ለማምጣት እውነተኛ የሆነውን ወንጌል ልናስረዳቸው ይገባናል። ይህንን በማሰብ እያንዳንዳችን የምንኖረውን የእምነት ሕይወት መሠረት የክርስቶስን የማዳን ወንጌል በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ከመመስከር ወደኋላ ልንል አይገባም (ሐዋ. ሥራ 1፡8)። ሁሉም አማኝ የወንጌልን ሥራ ለመሥራት እንደተጠራ መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል (ማቴ. 28፡19 እና 2 ጢሞ. 4፡5)። እንዲሁም ደግሞ ሌሎች ለወንጌላዊነት ሥራ ብቻ የተጠሩ አሉ (ኤፌ. 4፡11)። እነዚህ ሰዎች ወንጌል የእለት ተእለት እንቅስቃሴያቸው አካል ብቻ ሳይሆን፣ የሕይወታቸው ዋና ትኩረት ነው።

**የክፍለ-ጊዜው መምሪያ**

**(ከለሳ 10-20 ደቂቃ)**

.............................................................................

ሰዎች የደረሱበትን ለማወቅ እና ለመበረታታት ጊዜ ውሰዱ። እርስ በርስ ታሪክ በመከፋፈል፣ ስለተገኙ ዕድሎች ያላችሁን ሃሳብ መከፋፈል እና ሌላ የትኛው ነገር በማንሣት እርስ በርስ ተነጋገሩ። ስለ ወንጌል ሥርጭት መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነውን ትርጉም (የክፍለ-ጊዜ አንድ ትግበራ) ላይ ተወያዩ። ትንሽ አባላት ላሉት ቡድን በአንድ ላይ ተወያዩ። ነገር ግን ትልቅ ቁጥር

ያለውን ቡድን ወደትንንሽ ቡድን በመከፋፈል ተወያዩ። ላመለጠው ሰው በመጀመሪያው ክፍለ-ጊዜ ባለፈው የተነጋገራችሁትን ቡድኖች እንዴት እንደሚሠሩ ተወያዩ።

**ጸሎት**

………………………………………………………………………………

ጊዜውን ለእግዚአብሔር በመስጠት እና በትውውቅ ጊዜ በተነሣ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ጉዳይ ላይ ጸልዩ።

**ትምህርት (20-30 ደቂቃ)**

ራሳችሁ ልታቀርቡበት በምትችሉበት መንገድ ወይም ቃል በቃል ይህንን ትምህርት ማቅረብ ትችላላችሁ።

*"በእግዚአብሔር ፊት እንዲሁም በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድ ባለው በክርስቶስ ኢየሱስ ፊት፣ መገለጡና መንግሥቱን በማሰብ ይህንን ዐደራ እልሃለው፤ ቃል ስበክ፤ ጊዜው ቢመችም ባይመችም ዝግጁ ሁን፤ በታላቅ ትዕግሥትና በማስተማር. አቅና፣ ገሥጽ፣ አበረታታም። ምክንያቱም፣ ሰዎች ትክክለኛ የሆነውን ትምህርት የማይቀበሉት ጊዜ ይመጣል። ከዚህ ይልቅ ለገዛ ምኞቶታቸው የሚስማማው፣ የሚያሳክክ ጆሮአቸው ሊሰማ የሚፈልገውን እንዲነግሯቸው በዙሪያቸው ብዙ አስተማሪ ይሰበስባሉ። እውነትን ከመስማት ጆሮአቸውን ይመልሳሉ፤ ወደ ተረትም ዘወር ይላሉ። አንተ ግን በሁኔታዎች ሁሉ የረጋህ ሁን፣ መከራን ታገስ፣ የወንጌል ሰባኪን ተግባር አከናውን፣ አገልግሎትህን ፈፅም።"*

**2 ጢሞ. 4፡1-5**

ወንጌላዊ ሆኖ መጠራት ማለት ምን ማለት ነው? ሁሉም ክርስቲያኖች የክርስቶስን መልካም ዜና ለዓለም እንዲሰብኩ የተጠሩ አይደሉምን? በማቴዎስ 28 ላይ ያለው የክርስቶስ ኢየሱስ የታላቁ ተልዕኮ ትዕዛዝ ለሁሉም ተከታዮቹ ወደ ዓለም መሄድ እና ሰዎችን ደቀመዝሙር ማድረግን ያካተተ ነው። ነገር ግን፣ በኤፌ. 4፡11-12 ላይ ከሐዋርያነት፣ መጋቢነት፣ አስተማሪነት እና ነብይነት ጋር የክርስቶስን አካል ይገነቡ ዘንድ የወንጌላዊነት ጥሪን እንመለከታለን። እንዲሁም በሐዋርያት ሥራ ላይ ፊሊጶስ የተባለው ሰው የወንጌላዊነት ማዕረግ ተሰጥቶት እንመለከታለን (ሐዋ. ሥራ 21፡8)። ስለዚህ፣ ይህ የወንጌላዊነት ጥሪ ለማን የተሰጠ ነው። ለሁሉም አማኞች ወይንስ ለተመረጡ ጥቂቶች?

ሐዋርያው ጳውሎስ በ2 ቆሮንቶስ 5፡17 ላይ በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት እንደ ሆንን የሚያስተምረውን ክፍል እናውቀው ይሆናል፤ እንደውም ሰብከንበት ሊሆን ይችላል። ነገር ግን፣ ቀጥሎ ያለውን ሃሳብ ብዙ ተመልክተነው ላይሆን ይችላል።

*"ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል እነሆ አዲስ ሆኖአል። ይህ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው፣ እርሱ በክርስቶስ አማካኝነት ከራሱ ጋር አስታረቀን፤ የማስታረቅንም አገልግሎት ሰጠን። እግዚአብሔር በክርስቶስ ዓለምን ከራሱ ጋር ሲያስታርቅ የሰዎችን በደል አይቆጥርባቸውም ነበር። ለእኛም ደግሞ የማስታረቅን ቃል ሰጠን። ስለዚህ እኛ የክርስቶስ እንደራሴዎች ነን፤ እግዚአብሔር በእኛ አማካኝነት ጥሪውን ያቀርባል። እኛም ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን በክርስቶስ እንለምናችኋለን።"*

**2 ቆሮ. 5፡17-20**

እግዚአብሔር ፍጥረትን ከራሱ ጋር በማስታረቅ ሥራ ላይ ነው ያለው። እኛም ከእርሱ ጋር የታረቅን እንደራሴዎቹ ይህንን እንድናደርግ ይፈልጋል። ይህ ለሙሉ ጊዜ አገልጋዮች ብቻ ሳይሆን ለሁሉም አማኞች የተሰጠ ሥራ ነው። ነገር ግን ይህ እንደራሴነት ለተለያዩ ሰዎች የተለያየ ጥሪ ነው።

በዚህ መንገድ አስቡት፡- በእግር ኳስ ቡድን ውስጥ ያለው ተጫዋች ዓላማው ጨዋታውን ማሸነፍ ነው። ነገር ግን አጥቂዎች በቡድን ውስጥ በዋናነት ጎል በማግባት ላይ እንዲያተኩሩ የሚጠበቅባቸው ተጫዋቾች ናቸው። ይህ ማለት ግን ሌሎች የቡድኑ ተጫዋቾች በተለያየ ጊዜ ላይ ጎሎችን ማስቆጠር አይችሉም ወይም የለባቸውም ማለት ሳይሆን ጎል ማስቆጠሩ በዋናነት የአጥቂው ኃላፊነት ነው ማለት ነው። እንደዚሁ እንደ ቤተ ክርስቲያን የፍጥረትን ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ እንፈልጋለን። በዚህም ውስጥ ሁላችንም አማኞች ኃላፊነት አለብን። ነገር ግን ወንጌል ማሠራጨትን ከሌሎች ነገሮች በፊት

በማስቀደም እንዲሠሩ የተጠሩ ደግሞ አሉ። እነርሱም፣ ሐዋ. ሥራ 21፡8 ላይ እንደምንመለከተው፣ እንደ ፊሊጶስ ያሉ ወንጌላውያን ናቸው።

የሚከተሉት ሃሳቦች በሕይወታችሁ ውስጥ ያሉ እና ትርጉምን የሚሰጧችሁ ከሆኑ፣ የወንጌላዊነት ጥሪ በሕይወታችሁ እንዳለ ሊያመላክቱ ይችላሉ።

- የጠፉት እንዲድኑ ትናፍቃለህ/ያለሽ፤
- በጊዜውም አለጊዜውም ወንጌልን ለመስበክ ትገፋፋለህ/ያለሽ፤
- በሚመጣ የትኛውም መከራ ውጥስ ፅንተህ/ሽ ተግባርህ/ሽን ትከውና/ኛለህ/ሽ፤
- አድማጭህ/ሽ ጆሮውን የሚያሳክክ ወግ እንድታወራ/ሪለት ቢሻም፤ የያዝከውን መልዕክት በምንም አትሸቅጥ/ጭም፤
- ኃይለኛና መቀየር በሚችለው የማዳን ወንጌል መልዕክት የጠፉትን ለመድረስ የጨከነ ዐቅም አለህ/ሽ፤
- ወንጌላዊ እንሆንክ/ሽ በሕይወትህ/ሽ የመጣ ትንቢታዊ ቃል አለ፤
- ወንጌልን መሥራት ሊወስድህ/ሽ ወደሚችለው ወደየትኛውም ቦታ ለመሄድ ፈቃደኛ ነህ/ሽ፤

***ጥያቄ***

***ከላይ ከተጠቀሱት ሃሳቦች መካከል አንዳንዶቹ ወይንም ሁሉም በሕይወታችሁ እውነት ሆነው የምትመለከቱበትን ሁኔታ አብራችሁ ተወያዩ (ወይም አንድ ወይም ሁለት ሰዎችን ጠይቅ/ቂ)። የወንጌላዊነትን ጥሪ በሕይወታችሁ እንዴት እንደተረዳችሁ ለቡድኑ አካፍሉ።***

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በዓለም ላይ ማንም እንዲጠፋ እንደማይፈልግ ይነግረናል (2 ጴጥ. 3፡9)። ይህ በእግዚአብሔር አባት ዘንድ ያለው ልብ በወንጌላዊው ውስጥ ሊኖር ይገባል። ወንጌልን የምንሰብከው ከግዴታ በሆነ ከፍርሃት በሆነ መገደድ ሳይሆን ከሰማዩ አባታችን ጋር ልባችን ተመሳሳይ ጥማት ስላለው መሆን አለበት። ማንነታችን በወንጌላዊነታችን ውስጥ የሚገኝ ሳይሆን የእግዚአብሔር ልጆች እና ወራሾች በሆንበት በምንስብከው ወንጌል ነው (ዮሐ. 1፡12)።

ማንኛውም ጸጋው የተሰጠውም ሆነ የተጠራ ሰው ራሱንም ሆነ ሌላን ሰው ማዳን አይችልም። ማዳን የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው። እኛ የእግዚአብሔር መልዕክተኞች እንድንሆን ብቻ ነው የተጠራነው። ስለጠፉት ያለውን ልብ በመካፈል እንሚወደን አባት እርሱን በማወቅ እንድናድግ እና የማዳኑን ኃይል ለሰዎች እንድንገልጥ ይጋብዘናል።

**ውይይት (20 ደቂቃ)**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች/ሃሳቦች ተወያዩባቸው፡-

- በግል የወንጌል ምስክርነት እና በወንጌላዊነት መካከል ልዮነት አለ?
- ሁሉም ሰው ወንጌልን የመመስከር ኃላፊነት ካለበት፤ ሰዎች ተለይተው ለወንጌላዊነት የሚጠሩት ለምንድን ነው?
- በግላችን ስለ ጠፉት ሰዎች እግዚአብሔር አባት ያለውን ዓይነት ልብ እንዴት ልናሳድግ እንችላለን?

*"ወንጌልን እንዲያገለግል ብቻ የተጠራ ሰው፣ በሙሉ ልብ ለዚህ ሥራ ጉልበቱን እና ጊዜውን መስጠት አለበት። ከዚህ ሥራ ሊያደናቅፉት በሚችሉ በማንኛቸውም ነገሮች መዘናጋት የለበትም። ግልፅ ከሆነ ከእግዚአብሔር ድምፅ ውጪ መከራም ሆነ የሰዎች ማባበል አገልግሎቱን ሊያስቀይሩት አይችሉም። "*

ቢሊ ግርሃም

**ትግበራ (5 ደቂቃ)**

ወንጌልን የምንሰብከው “ወንጌላውያን” ስለሆንን ሳይሆን፣ የእግዚአብሔር አብ ፍቅር ስለቀየረን እና ዓለምም የምናውቀውን እርሱን እንዲያውቀው ነው።

ለሚቀጥለው ወር የማርቆስን ወንጌል በግል የጥሞና ጊዜያችሁ ውስጥ በማካተት የማርቆስ ወንጌል ዋና መልዕክት የሆነውን የክርስቶስ ኢየሱስን የእግዚአብሔር ልጅነት እና የአባቱን ፈቃድ ለማድረግ የመጣ ባርያ ላይ ትኩረት በመስጠት አጥኑ። ይህንን ወንጌል ደጋግማችሁ ስታነቡ፣ እግዚአብሔር በእርሱ ውስጥ ያላችሁን ማንነት እንዲገልጥላችሁ ለምኑት።

**ጸሎት**

ማንም እንዳይጠፋ የሚፈልገው እግዚአብሔር በልጁ በኢየሱስ በማመን የመዳንን መንገድ ስላዘጋጀ አመስግኑት። እርስ በርሳችሁ እግዚአብሔር ለወንጌላዊነት መጠራታችሁን እንዲያጠራላችሁ፣ ወንጌልን የምትሰብኩባቸውን ዕድሎች እንዲሰጣችሁ፣ እንዲሁም የመስበክን ድፍረት እንዲያበዛላችሁ ጸልዩ።

**ተጠያቂነት (15 ደቂቃ)**

የተጠያቂነት ቅጽ በመሙላት ለአጋራችሁ እና ለአነስተኛ ቡድናችሁ አጋሩት፤ እንዲሁም አንዳችሁ ለሌላችሁ ጸልዩ።

**ማስታወሻ**

**ክፍለ-ጊዜ ሦስት**

***የወንጌላዊው መልዕክት***

*በዚህ ክፍለ-ጊዜ የወንጌል መልዕክት ምን እንደ ሆነ እንመለከታለን። ወንጌል ምንድን ነው? የምናስተላልፈው መልዕክት*

*ግልፅ እንዲሆን የምንሰብከውን ወንጌል በትክክል ተረድተነዋል?*

---

**ክፍለ-ጊዜው በአንድ ዐረፍተ-ነገር ሲጠቃለል**

.......................................................................................

*የወንጌላዊው መልዕክት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ የመጣው ክርስቶስ፣ የተሰቀለው ክርስቶስ፣ የተነሣው ክርስቶስ እንዲሁም ተመልሶ የሚመጣው ክርስቶስ።*

**የክፍለ-ጊዜው ዳራ**

.......................................................................................

*ቅዱስ አውግስጦስ ከሚታወቁበት ንግግሮች መካከል "ጌታ ሆይ፣ ለራስህ ብቻ ፈጥረኸናል፤ ልባችን አንተን እስኪያገኝ ድረስ እረፍት የለውም።"*

*ወንጌል ሰዎችን ከጥፋት፣ ከጨለማ፣ ከስብራት እና ከተስፋ መቁረጥ ወደ ደስታ፣ ብርሃን፣ ፍቅር እና ተስፋ ያመጣል። ወንጌል እረፍት ያጣውን ሕይወት በፈጣሪ ወዳለው እረፍት ያመጣል። ዛሬ ላይ በሚያሳዝን መልኩ በርካታ ክርስቲያኖች በዚህ የወንጌል ኃይል መታመን አቅቶአቸዋል። ሰዎች ወንጌልን ለሌሎች የማይሰብኩበት ብዙ ምክንያቶች አሉ። እነርሱም፡- ፍርሃት፣ ብቁ ያለመሆን ስሜት ወይም ሌላ ሰው እንደሚያከናውነው ማሰባቸው ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ወንጌል ላለመስበክ የሰዎች ምክንያቶች ሁሉ ምንጭ አንድ ነው፤ ይህም እውነተኛ የሆነውን የወንጌልን ትርጉም አለመረዳት እና በወንጌል ውስጥ ባለው ኃይል አለመታመናቸው ነው።*

*በሮሜ 1 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ "በወንጌል አላፍርም?" ይልና፣ ወዲያውኑ ቀጥሎ፣ ለምን እንደማያፍር ያስረዳል። "ምክንያቱም ለሚያምን ሁሉ ለድነት የሚሆን የእግዚአብሔር ኃይል ነው"* (ሮሜ 1፡16)። *ወንጌል በመማርያ ክፍሎች ውስጥ የምንከራከርበት የአዕምሮ ፍልስፍና ሳይሆን፣ ሰዎችን ወደ መዳን የሚያመጣ የእግዚአብሔር ኃይል እንደ ሆነ መረዳት፣ የእግዚአብሔር ማንነት፣ ምን እንዳደረገልን እና ዓለም የሠራው ሥራ ምን ማለት እንደ ሆነ ከመረዳት ጋር ይዛመዳል። ይህም በክርስቶስ ማንነት ውስጥ የተጠቀለለ ነው። ወንጌል መረዳት ስለመኖራችን እና የፈጠረን እግዚአብሔር ማንነትን ለመረዳት ከሚነሡ ዋነኛ ጥያቄዎች መካከል፡-*

***እኔ ማን ነኝ?***

*በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ሁሉም ሰው ይህንን ጥያቄ ይጠይቃል። የሕይወት ትርጉም ምንድን ነው? አላማ አለው ወይ? ማንነቴ ምንድነው? መልሱም በእግዚአብሔር የተወደድን እና የተፈጠርን ልጆቹ ነን።*

**እግዚአብሔር ማን ነው?**

*ዓለም ላይ በርካታ ኃይማኖቶች አሉ። እግዚአብሔር ቢኖር እንኳን በምን መንገድ ልናውቀው እንችላለን፣ የምናመልከውስ እውነተኛው አምላክ መሆኑን በምን ልናውቅ እንችላለን? እግዚአብሔር ራሱን በፍጥረት ውስጥ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፣ በእያንዳንዱ አማኝ ሕይወት እንዲሁም በክርስቶስ ኢየሱስ ገልጦአል። እርሱ የሕይወት ፈጣሪ እና ደጋፊ፣ የዓለም ንጉሥ፣ ፍፁም እና አፍቃሪ የሆነ አባት ሲሆን በእርሱ ላይ ያመፀበትን እና የተሰበረውን የሰው ዘር ሁሉ ከእርሱ ጋር እንዲታረቅ ይናፍቃል።*

**ኢየሱስ ክርስቶስ ማን ነው?**

ኢየሱስ ክርስቶስ በሰው ታሪክ ውስጥ የሚያስፈልገን ነው። ጥቂት የታሪክ ምሁራን የእርሱን በእርግጠኝነት መኖር ቢጠራጠሩም፣ መጠየቅ ያለብን ግን ማን ነው? ብልኅ አስተማሪ? ውሸታም ነው? እብድ ሰው ነው? ብለን ነው። ነገር ግን፣ ኢየሱስ ያልነውን ነው፡- የዓለም መድህን፣ በሕይወቱ፣ በሞቱ እና በትንሣኤው ለሰዎች የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ መንገድን አዘጋጅቶአል።

እነዚህ ጥያቄዎች ከሰዎች ጋር ስለወንጌል ውይይት ሊያስጀምሩን ይችላሉ። ነገር ግን፣ ወንጌልን በሙላት ለመረዳት አይጠቅሙንም። ነገር ግን፣ መነጋገርን እና ግንኙነትን ለመጀመር መንገድ ሊከፍቱልን የሚችሉ ናቸው። በመሆኑም፣ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በጥልቀት በመመለስ በእነዚህ ጥያቄዎች በኩል ወደ ሙሉ እና ኃይለኛው የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ሰዎችን ማመላከት አለብን።

**የክፍለ-ጊዜው መምሪያ**

**(ክለሳ 10-20 ደቂቃ)**

..........................................................................................

ሰዎች ያሉበትን ለማወቅ እና ለመበረታታት ጊዜ ውሰዱ፤ እርስ በርስ ታሪክ በመከፋፈል፣ ስለተገኙ ዕድሎች ያላችሁን ሃሳብ መከፋፈል እና ሌላ የትኛውንም ነገር በማንሣት እርስ በርስ ተነጋገሩ። የቡድኑ አባላት በባለፈው ወር በማርቆስ ወንጌል ጥናታቸው (የክፍለ-ጊዜ ሁለት ትግበራ) ላይ ያገኙትን መረዳት ተወያዩ። ይህንን ጊዜ በመውሰድ የአገልጋይን ማንነት ከኢየሱስ ክርስቶስ የሚያገለግል የእግዚአብሔር ልጅነት ጋር ፈልጋችሁ እርስ በርሳችሁ ተበረታቱ።

**ጸሎት**

..........................................................................................

ጊዜውን ለእግዚአብሔር በመስጠት እና በትውውቅ ጊዜ በተነሣ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ጉዳይ ላይ ጸልዩ።

**ትምህርት (20-30 ደቂቃ)**

..........................................................................................

ራሳችሁ ልታቀርቡበት በምትችሉበት መንገድ ወይም ቃል በቃል በማንበብ ይህንን ትምህርት ማቅረብ ትችላላችሁ።

*“ወንድሞች ሆይ ወደ እናንተ በመጣሁ ጊዜ የእግዚአብሔር ሚስጥር በረቀቀ የንግግር ችሎታ ወይም በላቀ ጥበብ ልገልጥላችሁ አልመጣሁም። በመካከላችሁ ሳለሁ ኢየሱስ ክርስቶስ ያውም የተሰቀለውን እርሱ ብቻ እንጂ ሌላ እንዳላውቅ ወስኜ ነበር።”*

**1 ቆሮ. 2፡1-2**

ጳውሎስ ለኢየሱስ ክርስቶስ ታሪክ እውነተኝነት እና ኃይል ያለውን መሠጠት *“በመካከላችሁ ሳለው ኢየሱስ ክርስቶስ ያውም የተሰቀለውን እርሱ ብቻ እንጂ ሌላ እነዳላውቅ ወስኜ ነበር”* በማለት ያውጃል። እግዚአብሔር ወደተበላሸው ዓለም ራሱ በኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ፍፁም ህየወት በመኖር፣ በመስቀል ላይ ለእኛ በሚገባውን ሞት በመሞት፣ እና ከሞት በመነሳት ለአነዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ የሞትን እርግማን መስበሩ  የወንጌል ልብ ነው። ድነት እና እውነተኛ ሕይወት የሚገኘው በኢየሱስ ክርስቶስ ባለእምነት ብቻ ነው። ይህንን እውነት የምንናገረው የተለወጠን አዕምሮ ለማግኘት ብቻ ሳይሆን በክርስቶስ ኢየሱስ ባለ እምነት ብቻ የሚገኘ የሕይወትን ለውጥ ለማምጣት ጭምር ነው።

ጥያቄ

የዚህ ክፍለ-ጊዜ አብዛኛው ሰዓት የወንጌልን ምንነት በመዳሰስ ላይ የሚያተኩር ይሆናል። የሚከተሉትን ክፍሎች በመከተል (በተጨማሪ የንባብ ክፍሎች ላይ ይገኛል) ስለ ወንጌል ስለምናምነው ውይይት መጀመር ይቻላል።

**ስለ ወንጌል አስተምሮ (ገጽ --)**

የወንጌል ሥልታዊ አቀማመጥ

**የወንጌል ትረካ** (ገጽ --)

በዚህ ክፍል ላይ በሥልታዊ አቀማመጥ የቀረበውን ወንጌል መጀመሪያ ቀርቦበት በነበረው ታሪካዊ አጻጻፍ ለማስቀመጥ ይሞከራል።

**የወጣት- ወንጌል ንግግር ምሳሌ፣**

**የ4ነጥብ ምሳሌ፣**

**የሦስት ክቦች ምሳሌ** (ገፅ ----)

እነዚህ ምሳሌዎች ወንጌል የምንሰብክባቸውን መንገዶች ልንገመግምባቸው የምንችልባቸው ምሳሌዎች ናቸው። ከእነዚህ ምሳሌዎች መካከል አንዱን መርጣችሁ (ጊዜ ካላችሁ ሁሉንም መመልከት ትችላላችሁ) ወንጌል እንዴት እንደሚያስረዱ ተመልከቱ። በጥሩ ሁኔታ የሚሠሩትን እና ጥቂት የሚጎድላቸውን ተወያዩ።

ፍራክ ተርክ የተባለው ሰው እንደተናገረው “ልጆችን በምታሸንፉበት መንገድ፣ የምታሸንፏቸው ለዚያው ነገር ይሆናል። በስሜት የምታሸንፋቸው ከሆነ፣ ለስሜት የተሸነፉ ነው የሚሆኑት።” መልዕክቱ የቀጠነ እና ሰዎች ሊሰሙት ብቻ የሚፈልጉት የተቀየጠ ወንጌል የምናቀርብ ከሆነ ብዙ ምላሾችን ልንመለከት እንችላለን። ይህ ምላሽ ግን እውነተኛ ለሆነው ወንጌል የሚሰጥ ሳይሆን ለተቀየጠው ወንጌል የሚሰጥ ነው።

የወንጌል መልዕክት አብሮ የሚያመጣቸው ከባድ ሃሳቦች አሉ። እያንዳንዳቸን ኃጢአተኞች እንደሆንን እና ሞት የሚገባን የጠፉን ፍጥረቶች እንደ ሆንን ያስረዳል። የወንጌል ዜና መልካም የሆነበት መንገድ ከሰው የጠፉ የክፋት ሁኔታ አንጻር ስንመለከተው ነው።

የእግዚአብሔርን አፍቃሪነት እና መልካምነት በሚገባ ልንረዳው የምንችለው የሰው ኃጢአት ምን ያህል አስቸጋሪ እንደ ሆነ መረዳት ስንችል ብቻ ነው። ብዙ ሰዎች መልካም የሆነ፣ ነገር ግን ሰዎቸን ስለ ኃጢአታቸው የሚቀጣ እና ወደ ሲዖል በሚልክ እግዚአብሔርን ማስታረቅ ያቅታቸዋል። ይህንን የወንጌል ክፍል ብዙ ሰዎች መናገር አይፈልጉም። ይህንን ክፍል ግን ከደበቅነው ሙሉውን መልዕክት መናገር አንችልም። የማይገባንን የእግዚአብሔር ፀጋ በፍቅር ለልጆቹ የተሰጠበት እና የሰው ልጆች ሁሉ ተስፋ የሆነው የክርስቶስ ሞት እና የትንሣኤው ተስፋ በሚገባ ለማስረዳት የኃጢአትን ሙሉ ችግር በሚገባ መረዳት ይኖርብናል።

የእግዚአብሔርን ትልቅነት በሚገባ ልናስረዳ የምንችለው፣ የኃጢአትን አስከፊነት በሚገባ ስንናገር ነው። የኃጢአትን ትልቅ ችግርነት በሚገባ ማስረዳት ካልቻልን የእግዚአብሔርን ትልቅነት በሚገባ መረዳት አንችልም። በዚህ ምክንያት ነው ኃጢአትን ስናስረዳ ምንም ያህል ችግር ቢኖርም ችግሩን እና አስከፊነቱን በሚገባ መናገር ይገባናል።

ሌላ ልንዘነጋው የማይገባን የወንጌል መልዕክት ራስን ለመካድ መጠራታችንን ነው። ለራሳችን መሻቶች አየሞትን የክርስቶስን መስቀል ተሸክመን ዕለት ዕለት ባለን ነገር ሁሉ እርሱን ለመከተል ነው መጠራታችን (ማቴ. 16፡24)። ይህንን የወንጌል አስፈላጊ መልዕክት “እግዚአብሔር ደስተኛ እና ብሩክ ያደርግሃል” በሚል መሸቀጥ የለብንም። ማት ቻንድለር የተባለ ሰው እንዲህ ያስቀምጠዋል፡-

*“የወንጌልን መልዕክት ሲካድ፣ ከሌላ ሃሳብ ጋር ሲጋባ ወይም ሲቀየጥ ወንጌል መሆኑ ይቀራል። የወንጌል መልዕክት ብቻ የማዳን ኃይል እንደ ሆነ ስንረሳ፣ የራሳችንን መረዳት እና የመናገር መንገድ በመደባለቅ ልንጨምርበት ወይም ልንቀንስበት እንሞክራለን።”*

ወንጌል በሙላት ልናቀርብ ይገባናል፤ **የጎደለ ወንጌል ሙሉ ያልሆኑ ክርስቲያኖችን ያፈራል**።

መደበኛ እና ዕለታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ለእያንዳንዱ አማኝ አስፈላጊ ነው። በተለይ ደግሞ የቅዱስ ቃሉን መልዕክት መደበኛ በሆነ መልኩ ለሚያቀርቡት እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው። በየዕለቱ ሕይወታችንን እንዲመግብ ካልፈቀድንለት፣ ከቅዱሱ ቃል መገለጥን መቀበል እንችላለን ብለን ልንሰብክ አንችልም። መጠራታችን ለወንጌላዊነት ብቻ ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስን የሚሰብክ ወንጌላዊነት/መስካሪነት ነው።

**ውይይት (20 ደቂቃ)**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች/የመወያያ ሃሳቦች ተወያዩባቸው**

- የራስህን/ሽን የወንጌልን እውነት መረዳት እንዴት ትገልጸዋለህ/ትገልጪዋለሽ?
- ወንጌልን ለማስረዳት ዛሬ የሚገጥሙን ችግሮች ምንድን ናቸው?
- በዚህ ዘመን ካሉ አድማጮች ጋር የግንኙነት ቦታዎች እንዴት መፍጠር ይቻላል?
- “መጽሐፍ ቅዱስን የሚሰብክ” ወንጌላዊ ማለት ምን ማለት ነው?

*“የክርስትና ልብ ትርታ ወንጌል ነው፤ ወንጌል ባህልን የሚጋፈጥ እውነት ነው። በወንጌል እውነት ስናምን፣ ወንጌል ያለንበትን ማኅበራዊ ሁኔታ የሚጠይቅ እና ክርስቲያኖች ያሉበትን ባህል የሚጋፈጡ እንዲሆኑ ያደርጋል። ወንጌል በዙሪያችን እና በውስጣችን ካለው ባህል ጋር ግብግብ እንድንገጥም ያስገድዳል።”*

**ዴቪድ ፕላት**

**ትግበራ (5 ደቂቃ)**

በቡድን ውስጥ ያሉት በሙሉ የተለያዩ መሣሪያዎችን (YouVersion app ወይም ሌሎች መጽሐፍ ቅዱስ የማንበቢያ መተግበሪያዎችን) በመጠቀም የማንበብ ዕቅድ እንዲጀምሩ ያበረታቱ። ወንጌልን በሚገባ እና በግልፅ ማስረዳት እንድንችል እና ኢየሱስ ክርስቶስን በመከተላችን እንድንበረታ ለመጽሐፍ ቅዱስ ያለን መሰጠት መጨመር አለበት።

ለሚቀጥለው የጥናት ጊዜ ይህንን የማጥኛ መሣሪያ እና መጽሐፍ ቅዱሳችሁን በመጠቀም በመጽፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተደገፈ በአጭር (3-5 ነጥቦች ብቻ ያሉት) መንገድ ወንጌልን አብራሩ። በሚቀጥለው ስብሰባ ላይ ይህ ምላሽ ስለ-መለኮታዊ እና የተግባቦት መንገዶቹ ለግምገማ ይቀርባሉ።

**ጸሎት**

በሞቱ እና በትንሣኤው በኩል አዲስን ሕይወት ስላገኛችሁት ሕይወት እግዚአብሔርን አመስግኑት። በእርሱ እንድትታመኑ እና በእርሱ ማደግ እንድትችሉ፤ የቃሉን እውነት እንዲበራላችሁ፣ የወንጌል መጥራትን ለይታችሁ እንድታውቁ እና በዙሪያችሁ ላሉ ለጠፉት በግልጽ እና በእውነት መናገር እንድትችሉ እንዲረዳችሁ ለምኑ። በጸሎት እና በእርሱ መገኘት ውስጥ መሆን እንድትችሉ ስላገኛችሁት ዕድል እግዚአብሔርን እያመሰገናችሁ፣ የተሰጣችሁ ዕድል ሳትጠቀሙበት እንዳያልፍ እግዚአብሔር እንዲረዳችሁ ጸልዩ።

**ተጠያቂነት (15 ደቂቃ)**

የተጠያቂነት ቅጽ በመሙላት ለአጋራችሁ እና ለአነስተኛ ቡድናችሁ አጋሩት እንዲሁም አንዳችሁ ለሌላችሁ ጸልዩ።

**ማስታወሻ**

**ክፍለ-ጊዜ አራት**

**የወንጌላዊው ተግባር**

***ወንጌልን መስበክ ለወንጌላዊው ምን ያህል አስፈላጊ ነው? ይህ ክፍለ-ጊዜ ወንጌል መስበክ ያለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጭብጥ እና የመስበክ እና የመግባባት ክህሎቶችን የምናዳብርበት ዕድል ለመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይህንን ተግባር የምናስገዛበትን ዕድል ለመዳሰስ ነው።***

**ክፍለ-ጊዜው በአንድ ዐረፍተ-ነገር**

**...................................................................................**

የወንጌላዊው *ሥራ* በቅዱስ ቃሉ የተገለጠውን ወንጌልን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ማወጅ ነው።

**የክፍለ-ጊዜው ዳራ**

**...................................................................................**

በታሪክ እንደሚወሳው የአሲሱ ቅዱስ ፍራንሲስ እንዲህ ብለዋል፡-

*"ወንጌልን ሁል ጊዜ ስበኩ፤ አስፈላጊ ከሆነ ቃላትን ተጠቀሙ፤"*

ይህ ትክክለኛ ጥቅስ ወንጌል ሕይወትን በሚገባ በመኖር የሚገለጥ የመሆኑን አስፈላጊነት የሚያመላክት ነው። ነገር ግን፣ ሁለት ዋና ችግሮች አሉ፡- የመጀመሪያው ቅዱስ ፍራንሲስ ይህንን ለመናገራቸው ምንም ማስረጃ የለንም። ጽፈውትም አያውቁም።

ሁለተኛው ዋና ችግር የጥቅሱ እውነተኛነት ላይ ነው፤ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት በአኗኗራችን መመስከር መልካሙን ዜና የቃል ስብከታችንን ያክል ቢሆንም፣ ወንጌል መስበክ የሚባለውም ነገር በዋናነት ቃላትን ተጠቅመን የምንሰብክበት መሆኑ መዘንጋት የለበትም። ዐረፍተ-ነገሩ እንዲህ ተብሎ በጠቃሚ ሁኔታ መሻሻል ይገባዋል፡-

*"ወንጌልን ሁል ጊዜ ስበኩ፤ አስፈላጊም ስለሆነ ቃላትን ተጠቀሙ"*

'መስበክ' እና 'ማወጅ' የሚሉት ቃላት በውስጣቸው ከንግግር ቃላት ጋር ጥምረት አላቸው - በንግግር አዋጅነት መገለጥ አለባቸው። ለዚህ ምክንያቱ ወንጌልን ማዕከል ያደረገ ሕይወት ብንኖርም ለሚመለከቱን የዘላለም ተስፋችን ከምን የመነጨ እንደ ሆነ በሚገባ ካልነገርናቸው በምን ሊያውቁ ይችላሉ፤ ሕይወት በዚህ መንገድ ለምን እንደምንኖረው በምን ያውቃሉ?

*"ዝም ብሎ ሰዎች ሕይወታችንን የምንኖርበትን መንገድ እንዲተረጉሙ ዕድል መስጠት የለብንም፤ እግዚአብሔር ራሱ ይህንን አላደረገም. በእግዚአብሔር የታሪክ ውስጥ ያሉት ቁልፍ ክስተቶች ሁሉ በንግግር የተገለጡ ናቸው።"*

ዊል ሜትዘርግ

በአዲስ ኪዳን መሠረት ለወንጌል ሥርጭት ስብከት አስፈላጊ ነበር (ሐዋ. ሥራ 2፡14)፤ ነገር ግን ዛሬ ላይ ወንጌልን መስበክ ያለፈበት እና ለዚህ ዘመን ምቹ ያልሆነ መንገድ እንደ ሆነ ያስባሉ። ወንጌልን በምንሰብክበት መንገድ ፈጠራ ያለበት መሆን አለበት እንዲሁም ንግግራችን በተለያዩ መንገድ የተደራጀ መሆን አለበት (በፊልሞች እና ሙዚቃ የመሳሰሉ የተለያዩ መንገዶችን መጠቀም አለብን)፤ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ወንጌልን መስበክ የወንጌል ሥርጭት ማዕከል እንደ ሆነ ያስተምረናል (1 ቆሮ. 1፡21፣ 2 ጢሞ. 4፡1-2)

ለወንጌልዊ ወንጌልን መስበክ የመጠራታቸው ማዕከላዊ ተግባር ነው፤ ይህ የወንጌል ስብከት የክርስቶስ ኢየሱስን ወንጌል የሚያስረዳ እንዲሁም ኢየሱስን በመከተል ለሰሙት ወንጌል ምላሽን እንዲሰጡ ዕድልን የሚሰጥ መሆን አለበት (ማር. 1፡17፣

ሉቃስ 9፡23)። ቃላት ብቻቸውን ግን ትርጉም አልባ ናቸው፤ ለክርስቶስ ራሱን ካልሰጠ ሕይወት የሚወጡ ቃላቶች ግብዝ እና ባዶ ናቸው እንዲሁም ከመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሌላቸው ንግግሮች መዳንን ሊያመጡ አይችሉም።

**የክፍለ-ጊዜው መምሪያ**

**(ክለሳ 10-20 ደቂቃ)**

......................................................................................

ሰዎች ያሉበትን ለማወቅ እና ለመበረታታት ጊዜ ውሰዱ፤ እርስ በርስ ታሪክ በመከፋፈል፣ ስለተገኙ ዕድሎች ያላችሁን ሃሳብ መከፋፈል እና ሌላ የትኛው ነገር በማንኛት እርስ በርስ ተነጋገሩ። ከቡድኑ ውስጥ ፈቃደኛ የሆኑ ሰዎች የባፈው ወር ትግበራ የነበረውን ስለወንጌል የሰሩትን እንዲያካፍሉ ዕድል ስጡ፤ ለሚቀርቡት ሃሳቦች አዎንታዊነት በጠበቀ መልኩ ምላሽ ስጡ።

**ጸሎት**

............................................................................................

ጊዜውን ለእግዚአብሔር በመስጠት እና በትውውቅ ጊዜ በተነሣ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ጉዳይ ላይ ጸልዩ።

**ትምህርት (20-30 ደቂቃ)**

............................................................................................

ራሳችሁ ልታቀርቡበት በምትችሉበት መንገድ ወይም ቃል በቃል ይህንን ትምህርት ማቅረብ ትችላላችሁ።

""ኢየሱስ ጌታ ነው።" በለህ በአፍህ ብትመሰክር፣ እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህ። የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና። ታድያ ያላመኑበትነን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? ስለ እርሱስ ሳይሰሙ እንዴት ያምኑበታል? ሰባኪ ሳይኖር እንዴት እንዴት መስማት ይችላሉ? ካልተላኩስ እንዴት መስበክ ይችላሉ? ይህም፣ "የምሥራችን የሚያመጡ እግሮች እንዴት ያማሩ ናቸው" ተብሎ እንደተጻፈው ነው።"

መጽሐፍ ቅዱሳችን ወንጌልን ስለማወጅ ደጋግሞ ይናገራል፣ ቲም ኬለር 53 የተለያዩ የግሪክ ቃላት ለዚህ ውለዋል- እነዚህም "ማወጅ" እና "መስበክ" በሚሉ ቃላት ተተርጉሟል። በዚህ በሮሜ መልዕክት ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን ቃል መልካምን ዜና ስለመስበክ ተጠቅሞበታል፤ እንዲሁም በ2 ጢሞ. 4፡1-2 ላይ ጢሞቴዎስ ወንጌል መስበክን ያሳስበዋል፤ ለእርሱም ወንጌልን መስበክ ዋና ነገር ነው። እግዚአብሔር ይህንን በጴንጤቆስጥ ቀን ተጠቅሞታል፣ ከተገለጡት የመለኮታዊ ምልክቶች እና ታዕምራቶች (በምላስ አምሳል እሳት ሲወርድ፣ በሌላ ልሳን መናገራቸው) ሳይሆን የሰዎችን መዳን ያመጡት እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ ሙላት ያወጀበት ንግግር ሰዎችን ወደ መዳን መመለስ ችሏል።

ወንጌል መስበክ ዛሬ ላይ ፈተና ላይ ወድቋል፤ ብዙዎች ለሰዎች ወንጌልን መስበክ መልካሙን የምሥራች የምንሰብክበት መንገድ መሆኑን አያምኑም። ግጭቶን በሚያስነሳ መልኩ የግል ምስክርነት፣ በጓደኝነት የሚደረግ ምስክርነት፣ እና በማኅበራዊ ዕርዳታዎች ውስጥ የሚደረጉ ወንጌልን የምንሰብክባቸው መንገዶች በብዙዎች ዘንድ ተመራጭ እየሆኑ መጥተዋል። ነገር ግን ወንጌልን በመስበክ ውስጥ ያለውን ኃይል መካድ አንችልም፤ መመስከር የሚለው የግሪክ ቃል ዋና ትርጉም "መልካም ዜና ማወጅ" የሚል ነው - ንግግርን መሠረት ያደረገ እንደ ሆነ እንመለከታለን። ስለምንኖርበት መንገድ ሆነ ስላለን ተስፋ ለሰዎች የማንናገር ከሆነ ስለ- ኢየሱስ ያለውን የዘላለም ሕይወት በምን ያውቃሉ (1 ጴጥ. 3፡15)?

ጥያቄ ፡ ወንጌልን መስበክ እንደ- ወንጌላውያን አስፈላጊ እንደ ሆነ የምናምን ከሆነ፤ የወንጌልን መልዕክት የምንሰብክበት መንገድ ለአድማጮቻችን ግልጽ እንዲሆን እና ለዚህም ጥሪ የሚስፈልገውን ምላሽ የሚሰጡበትን ዕድል እንዴት መስጠት እንችላለን?

የምናካፍለውን ወንጌል ለምንሰብካቸው ሰዎች ጋር በሚገባ ማዛመድ እንድንችል እና መልዕክታችን በሚገባ እንዲተላለፍ፣ የሰዎቹን ማንነት እና አውድ መረዳት ይገባላል። ወንጌልን ለታዳጊ ወጣቶች የምንሰብክበት መንገድ ለአዋቂዎች

ከምንሰብክበት መንገድ ይለያል። የወንጌል መልዕክት ሳይቀየር ነገር ግን የምናቀርብበት እና የምንጠቀማቸው መንገዶች መለያየት አለባቸው። የምንሰብከው ወንጌል መልዕክት ሳይለወጥ፣ የምንሰብክበት መንገድ ግን መለያየት አለበት።

ለዚህ ነው ወንጌላውያን መዘጋጀት ያለባቸው። የምናውቃቸው እና የተለመዱ ወንጌልን የምንሰብካቸው መንገዶች ሳንለውጥ ከተጠቀምናቸው የተዘናጋን እና ሰነፍ ወንጌላውያን እንሆናለን። ዝግጅታችን መጀመር ያለበት በመንፈሱ እንዲናገረን እና ልንሰብክ ስንነሳ የምንናገራቸውን ቃላት እንዲሰጠን እግዚአብሔርን በመለመን ነው። የሚያደምጡንን ሰዎች መሠረት ያደረጉ ስብከቶች እና ንግግሮችን ማዘጋጀት አለብን።

ጥያቄ: የሚከተሉትን ስድስት የወንጌል ስብከቶችን ተመልከታችሁ፤ በራሳችሁ አገልግሎት ውስጥ ልትጠቀሙባቸው የምትችሉበትን ሃሳብ ለይታችሁ አውጡ

መስበክ ያለብን

- በቀላሉ- በመልካም ተግባቦት ውስጥ በቀላሉ መናገር አስፈላጊ ነው፤ በቀላሉ ለማስረዳት የምንሰብከውን መልዕክት በሚገባ መረዳት አለበት።
- በድፍረት - የመልዕክታችንን እውነት በድፍረት እና በሙሉ ልብ መስበክ አለብን።
- በመንፈስ - ልቦች መልዕክታችንን ሰምተው ወደ መዳን እንዲመጡ- የእግዚአብሔር መንፈስ በሥራ ላይ መሆን አለበት። የስብከታችን ተግባር ለመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተገዛ መሆን አለበት።
- የተለዩ- ክርስቶስ ከሁሉም የተለየ ሆኖ እንዲሁም የስብከቱ ማዕከል መሆን አለበት።
- በፍቅር - ወደራሳችን ሃሳብ እና እውቀት ሳይሆን ወደ ኢየሱስ ማዕከላዊነት ማምጣት ነው ያለብን። በትሕትና መስበክ አለብን፣ እንዲሁም ስለምንሰብከው እግዚአብሔር አክብሮት እንዲሁም ለምንሰብክላቸው ሰዎች ርህራሄ ሊኖረን ይገባል።
- በግል - ለሰዎች ወንጌልን ስናካፍል፣ የወንጌል እውነት በራሳችን ሕይወት ያመጣውን ለውጥ በማሳየት በሚሰሙም ባሉበት ሁኔታ ጋር ማዛመድ ይቻላል።

እነዚህ ጠቃሚ ምክሮች አስፈላጊ ቢሆኑም፤ የፈለገውን ያህል በሚያምር መንገድ የምናቀርብበት ክህሎት ብናዳብርም ማንንም ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊያፈልስ አይችልም

*"ወንጌልን የምንሰብክበት የተለያዩ መንገዶች እና ስልቶችን ማዳበር አንድ ነገር ቢሆንም፤ ነገር ግን እግዚአብሔርን የሚከለለውን መሸፈኛ እና እንቅፋቶች ማንሣት መቻል ሌላ ነገር ነው። "*

ዴቪድ ዋትሰን

ስብከታችን መንፈስ ቅዱስ በሃል እንዲሠራ እና እንዲቀሳቀስ ቦታ መስጠት አለብን። ወንጌል እንዴት እንደምንሰብክ በሚገባ ማስተዋል ሲኖርብን በንግግራችን ውስጥ እግዚአብሔር የዘላለም ሕይወትን ተዓምራት እንዲያመጣ መጸለይ አለብን። በባለፈው ክፍለ-ጊዜ ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ በ፤ ቆሮንቶስ 2 ላይ ወንጌልን ለማወቅ እና ለመስበክ ያለውን መሰጠት እንመለከታለን። ሐዋርያው ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በመመራት አዲስ የሆነ እምነት በሰው ምክንያታዊነት ላይ ሳይሆን በእግዚአብሔር ላይ ለማሳረፍ የተሰጠ መሆኑን ያስረዳል።

*"ወደ እናንተ የመጣሁት በድካምና በፍርሃት፣ እንዲሁም በብዙ መንቀጥቀጥ ነበር። ቃሌም፣ ስብከቴም የመንፈስን ኃይል በመግለጥ እንጂ፣ በሚያባባል የጥበብ ቃል አልነበረም። ይኸውም እምነታችሁ በእግዚአብሔር ኃይል እንጂ በሰው ጥበብ ላይ እንዳይመሠረት ነው"*

2 ቆሮ. 2፡3-5

እግዚአብሔርን በእውነት እና በመንፈስ ለማምለክ እንገናፍቃለን (ዮሐ. 4፡23)፤ የወንጌል ምስክርነታችንም ከዚህ የተለየ መሆን የለበትም፤ ሌሎች እኛ የምናመልከውን እንዲያመልኩ የእግዚአብሔርን እውነት በመንፈስ ማወጅ መጋበዝ አለብን።

**ውይይት (20 ደቂቃ)**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች/ ሃሳቦች ተወያዩባቸው

- ስብከት ዛሬም ተገቢነት ያለው ነው?
- ልዩነት ባለው ዓለም ላይ እንደ ሰባኪዎች እንዴት ጠቃሚ በሆነ መልኩ መገለፅ አለበት?
- እንደ ሰባኪ ጥንካሬ እና ድካማችን ምንድን ነው?
- ለወንጌል ስብከት እንዴት ነው የምትዘጋጁት?

*"በጥሩ ስብከት እና በድንቅ ስብከት መካከል ያለው ልዩነት የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው. . .፤ ንግግራችን ጥሩ ማድረግ ላይ መሥራት አለብን፤ ለሰሚዎች እንዴት እና መቼ ድንቅ የማድረግን ሥራ ግን ለመንፈስ ቅዱስ መተው አለብን"*

ቲም ኬለር

**ትግበራ (5 ደቂቃ)**

በዩቲዩብ ላይ የወንጌል ስብከቱን መገምገም የምትችሉትን ሰባኪ ቪዲዮ ፈልጋችችሁ፣ ለቡድኑ አባላት ስጡ። ለሚቀጥለው ክፈለ-ጊዜ ቪድዮውን ተመልክተው፣ ማስታወሻ ወስደው እና ለውይይት ተዘጋጅተው እንዲመጡ አሳስቡ።

**ጸሎት**

እግዚአብሔር ወንጌልን በትሕትና በምትናገሩበት መንገዶች ሁሉ ላይ በኃይል እንዲሠራ ጠይቁት። የወንጌልን መልዕክት እንድትናገሩ እግዚአብሔር መልዕክኞቹ ስላደረጋችሁ እያመሰገናችሁ፣ የምትኖሩት ሕይወት ከምትሰብኩት ወንጌል ጋር እንዳይጣረስ ኃይል እንዲሆናችሁ ጠይቁት። ወንጌልን ለምትሰብኩላቸው ሰዎች የሚሰሙት ወንጌል እንዲበራላቸው እና እግዚአብሔርን እንዲታመኑ ጸልዩላቸው።

**ተጠያቂነት (15 ደቂቃ)**

የተጠያቂነት ቅጽ በመሙላት ለአጋራችሁ እና ለአነስተኛ ቡድናችሁ አጋሩት እንዲሁም አንዳችሁ ለሌላችሁ ጸልዩ።

**ማስታወሻ**

**ክፍለ-ጊዜ አምስት**

**የወንጌላዊው ኃይል**

**እንደ ወንጌላውያን መንፈሳቸው ሙት የሆኑ ሰዎች ህያዋን ሲሆኑ ማየትን እንመኛለን። በዚህ ክፍለ-ጊዜ በጸሎት ውስጥ ያለን መንፈሳዊ መነቃቃትን፣ ይህም ደግሞ ወደ ጠፋው ዓለም ሊደርስ የሚችል እውነተኛ የሆነ የልብ መነሳሣት ማለት ምን እንደ ሆነ እንመለከታለን።**

**ክፍለ-ጊዜው በአንድ ዐረፍተ-ነገር**

**.................................................................................**

ጸሎት የወንጌል ሥርጭት መሠረት ነው፤ ከሰው ጥረት ሳይሆን ከእግዚአብሔር እጅ ብቻ ሊመጣ የሚችለውን ኃይል በጸሎት ወደሚገባው ቦታ እንመልሳለን።

**የክፍለ-ጊዜው ዳራ**

**.................................................................................**

"በጋራ ጸሎት ውስጥ ያልተወለደ መንፈሳዊ መነቃቃት በየትኛውም ሀገርም ሆነ መንደር ውስጥ ኖሮ አያውቅም" ይህንን የሚያስደንቅ ንግግራቸው በአሜሪካ ትልቁ ቤተ-እምነት የሆነው የ 'ፕሬስባይቴሪያን' ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ እና ሚስዮናዊ የነበሩት አርተር ታፓን በመናገራቸው ይታወቃሉ።

ይህንን ጥቅስ የሚቃረን ሃሳብ ለማግኘት ይቸግራል። ይህ እግዚአብሔር በቅዱስ ቃሉ የሰጠውን ተስፋ እና የሚከተለውን የተስፋ ቃል የምናገኝበት ነው። ለምሳሌ ያህል እግዚአብሔርን አመፀኛ ለነበሩት እስራኤል ልጆች በሰለሞን ዘመን የሚመጣውን ተስፋ እና የኃጢአታቸውን ውጤት ያስረዳቸዋል

*"በስሜ የተጠራው ህዝቤ ራሱን አዋርዶ ቢፀልይ፣ ፊቴንም ቢፈልግ እና ከክፉ መንገዱ ቢመለስ፣ ከሰማይ እሰማዋለሁ፣ ኃጥያቱንም ይቅር እላለው፣ ምድሩንም እፈውሳለው "*

2 ዜና 7፡14

እንዲሁ በክርስቶስ ኢየሱስ ማመን ማለት በራሳችን ላይ ያለንን ጌትነት በትሕትና በመተው፣ ለክርስቶስ በመስጠት፣ ጌትነቱን በሕይወት ላይ በማወጅና ወደ ሕይወታች ፈውስን እና አዲስን ሕይወት እንዲያመጣልን መፍቀድ ነው። በመዳን ሕይወት ውስጥ ጉዟችን የሚሆነው ከአመፅ (ኃጢአታችን) ወደ መገለጥ (የእግዚአብሔር እውነት)፣ ወደ መመለስ (በእግዚአብሔር ላይ በመታመን)፣ ወደ መነቃቃት (ሌሎችን ወደመለወጥ የሚጠራ ለውጥ) ነው።

በሁለተኛ ዜና ላይ የምንመለከተው '*መመለስ*' የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ '*መናዘዝ/መመለስ*' ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይ ነው። ኢየሱስ የስብከት አገልግሎቱን የሚፈፅመው ይህንን ለማምጣት ነው (ማር. 1፡15)። የእስራኤላውያን የዛን ዘመን ችግር ዛሬ ላይ ያለን ክርስቲያኖች ችግር ነው። ሕይወታችንን ለመምራት በተደጋጋሚ ወደ ተለያዩ አማልክት (ራሳችንን ጨምሮ) እንዞራለን። ይህ አለመታዘዝ ወደ ሞት፣ ስብራት እና አመጽ ብቻ ነው ሊወስደን የሚችለው። ከእርሱ ዘወር ካልንበት ጊዜ ጀምሮ እግዚአብሔር ወደ እርሱ እንድንመለስ ይጠራናል። ወንጌል ይህንን ነው የሚነግረን፤ እንደ አመፃችን ሳይሆን ዛሬም በእግዚአብሔር ፀጋ ውስጥ እና እኛ ለእርሱ ባለን ምላሽ ውስጥ ተስፋ አለን።

በዳኛ ፊት ነፃ መውጣት ከፈለግን ወንጀለኛ አለመሆናችንን በመናገር ከፍርድ ነፃ ለመሆን እንለምናለን። አሁን ግን ዘላለማዊ ዳኛ በሆነው በእግዚአብሔር ፊት ወንጀለኛ መሆናችንን በማመን ብቻ የሚሰጥ ነፃ መውጣት ነው የተሰጠን። ፍትህ ቅዱስ በሆነው በእግዚአብሔር ፊት ስለ ፈፀምነው በደል ቅጣትን ይፈልግብናል። እግዚአብሔር ግን በመስቀሉ በሆነ ፍፁም ፅድቅ ምሕረትን ሰጥቶናል። በሞት ፈንታ በክርስቶስ ፈውስን፣ ዳግም ወደ ነበርንበት መመለስን እና ሕይወት ቀርቦልናል፤ እግዚአብሔር ትሁቱን ያድሰዋል።

በኢዮብ ሕይወት ውስጥ በጸሎት እና አንድነት (ከእግዚአብሔር እና እርስ በርሳችን) ኃይል የሆነ መታደስን እንመለከታለን። የኢዮብ መመለስ የመጣው ከእግዚአብሔር በተሰጠው ምላሽ ውስጥ ሳይሆን መጀመሪያውኑ እይታው እንዲበላሽ ምክንያት ለሆኑት ለወዳጆቹ ሲፀልይ ነው። ኢዮብ ከራሱ ችግር ላይ ዓይኖቹን አንሥቶ ለሌሎች ለበደሉት በልግስና ሲጸልይ መታደሱን እንመለከታለን።

*መታደስ የሚጀምረው ሰው ለሰማያዊ አባቱ መታዘዝ ሲጀምር እና ከሠላም መንግሥት ጋር አንድነትን ሲፈልግ ነው። ኢየሱስ ጌታ መሆኑን በንግግር እና በተግባር ማወጅ፣ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መታመን ለአንድ ሰው ዳግም ውልደትን ያመጣለታል። በእግዚአብሔር ፀጋ በሕይወታችን ውስጥ መታደስ ይመጣል። እንዲሁም ሰዎች በአንድ ልብ ሆነው ከአመፃቸው ተመልሰው የእግዚአብሔርን ኃይል ለምድራቸው ፈውስ በሚፈልጉበት በዚያ መታደስ ይሆናል።*

**የክፍለ-ጊዜው መምሪያ**

**(ክለሳ 10-20 ደቂቃ)**

..........................................................................................

ሰዎች ያሉበትን ሁኔታ ለማወቅ እና ለመበረታታት ጊዜ ውሰዱ። እርስ በርስ ታሪክ በመከፋፈል፣ ስለ ተገኙ ዕድሎች ያላችሁን ሃሳብ መከፋፈል እና ሌላ የትኛውንም ነገር በማንሣት እርስ በርስ ተነጋገሩ። ባለፈው ሳምንት የተመለከታችሁትን ቪድዮ ላይ በማውራት ይህንን ክፍለ-ጊዜ ጀምሩ። ግብታዊ የሆነ ግምገማ ሳይሆን፣ ሰዎች ምን እንደተማሩ፣ ምን ያክል ጠቃሚ ሆኖ እንዳገኙት፣ ምን ደግሞ ጠቃሚ ሳይሆን እንዳገኙ፣ ከተመለከቱት የስብከት ወንጌል በመነሣት ለስብከት አገልግሎታቸው ምን ያክል ጠቃሚ ሆኖ እንዳገኙ እንዲናገሩ ዕድል ስጧቸው። በሚገባ በሀሳቡ ላይ ተነጋገሩ፤ ወንጌልን በሚገባ ማስረዳቱ ላይ ተነጋገሩበት፤ ለተሰበሰበው አድማጭ በሚገባ መልዕክቱ በትክክል መተላለፉ ላይ ተወያዩበት።

**ጸሎት**

..........................................................................................

ጊዜውን ለእግዚአብሔር በመስጠት እና በትውውቅ ጊዜ በተነሡ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ጉዳይ ላይ ጸልዩ።

**ትምህርት (20-30 ደቂቃ)**

..........................................................................................

ራሳችሁ ልታቀርቡበት በምትችሉበት መንገድ ወይም ቃል በቃል ይህንን ትምህርት ማቅረብ ትችላላችሁ።

*"እንግዲህ ከሁሉ አስቀድሞ ልመናና ጸሎት፣ ምልጃ እና ምስጋና ለሰዎች ሁሉ፣ ለነገሥታት እና ለባለ ሥልጣናት ሁሉ እንዲደረግ አሳስባለሁ። ይህም በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወትና በቅድስና ሁሌ በሰላምና በጸጥታ እንድንኖር ነው። ይህ በእግዚአብሔር በአዳኛችን ፊት ደስ የሚያሰኝ ነው። እርሱ ሰዎች ሁሉ እንዲድኑና እውነትን ወደማወቅ እንዲደርሱ ይፈልጋል"*

1 ጢሞ. 2፡1-4

ሐዋርያው ጳውሎስ ለተማሪው ለጢሞቴዎስ በ1 ጢሞቴዎስ መልዕክት ላይ በኤፌሶን ባለችው በቤተ ክርስቲያን ሊኖር የሚገባው የአምልኮ መንገድ ላይ መመርያን ይሰጠዋል። ለጸሎት እና ስለ ሰዎች ስለሚደረግ ልመና ቅድሚያ መስጠት እግዚአብሔርን የሚያስደስት እንደ ሆነ ይናገራል። እግዚአብሔር የሰዎች ሁሉ ወደ ሰላሙ መንግሥት መምጣት ያስደስተዋል፤ ጸሎትም በተተራመሰ ዓለም ሰላምን እና በሞት መካከል ሕይወትን ሊያመጣ የሚችለውን እግዚአብሔር ብቻ እንዲሠራ እርሱን የምንጠራበት መንገድ ነው።

***ጸሎት የወንጌል ሥርጭት መሠረት ነው፤*** በጸሎት ከሰው ጥረት ሳይሆን ከእግዚአብሔር እጅ ብቻ ሊመጣ የሚችለውን ኃይል ወደ ሚገባው ቦታ እንመልሳለን።

ኤድመንድ ፒ. ክሎውኒ እንደጻፉት

*"መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው፤ በአመጽ የጠፉትን ሰዎች ወደ ራሱ የሚመልስበት የራሱ የእግዚአብሔር ታሪክ ነው። ታሪኩ ሰው የጠፋበትን አምላክ የሚፈልግበት ሳይሆን፣ እግዚአብሔር የጠፋን ሰው የሚፈልግበት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የጸሎትን ክህሎት ሳይሆን የጸሎትን አምላክ ነው የሚያወራልን፤ ጸሎትን የሚሰማ አምላክ ነው ያለው - ገና ሳንጣራ የሚመልስ፣ ተናግረን ሳንጨርስ የሚሰማ አምላክ ነው (ኢሳ. 65፡24-25)።"*

የአሜሪካ መሥራች ከነበሩት መካከል አንዱ ቤንጃሚን ፍራንክሊን *"ለመዘጋጀት መውደቃችን፤ ለመውደቅ መዘጋጀታችን ነው"* (By failing to prepare you are preparing to fail) ማለታቸው ይታወሳል። በእግዚአብሔር ፊት በልመና፣ በመሰጠት እና ጸሎት በማዋረድ ለወንጌል ሥርጭት ልባችንን ልናዘጋጅ ይገባናል። *"ለወንጌል ሥራ በጸሎት ባለመዘጋጀት መውደቃችን፤ ወንጌልን ላለመመስከር ውድቀት እየተዘጋጀን ነው"*

በታማኝነት፣ በጸሎት እና በመንፈሳዊ መነሳሣት ወንጌል በምንመሰክርባቸው ጊዜያት ሁሉ የሰማን ሰው ሁሉ ወንጌል ላይቀበል ይችላል። የማዳን ኃይል ግን የእግዚአብሔር ብቻ ነው፤ በምንፈልገው እና በጠበቅነው ጊዜ ሁሉ ውጤትን ባናገኝም፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ፍሬን እንደሚሰጠን በጸሎት መታመን አለብን (ኤፌ. 6፡18-20)። **የወንጌል ስርጭታችን ውጤት በእግዚአብሔር እና መልዕክታችንን በሚሰሙ ሰዎች እጅ ነው። የወንጌል ሥርጭት አገልግሎታችን ውጤት የሚለካው በሚድኑ ሰዎች ሳይሆን እግዚአብሔርን በጸሎት እና በምስክርነት በመታዘዛችን ነው።**

ለጸሎት ያለን መነሣሣት ዋነኛው ምክንያታችን እግዚአብሔር አንድንጸልይ ማዘዙ ነው። ይህም ትዕዛዝን ከመከተል፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት ሲያድግ ማደግ አለበት። መሻታችን እግዚአብሔርን በፍቅር ማክበር እና መልካምነቱን እና በረከቱን ለሕይወታች እንዲሁም ለሌሎች እንዲገለጥ መሆን አለበት። በጸለይን ቁጥር እግዚአብሔርን እናውቀዋለን፤ እግዚአብሔርን ባወቅነው ቁጥር ፈቃዱን እንዲገልጥልን የበለጠ መጸለይን እንፈልጋለን።

ስለዚህ የጸሎት ሕይወታችን ምን ይመስላል? ለአንዳንዶች ጸሎት በቀላሉ ይመጣላቸዋል፣ ለሌሎች በጥረት ይመጣል። በቀላሉም ሆነ በጥረት ቢመጣም፣ የጸሎት ጊዜያችን ቢለያይም፣ ከልብ መሆን ግን አለበት። እግዚአብሔርን ከልባችን በራሳችን እና በሌሎች ሰዎች ሕይወት ውስጥ ለውጥ እንዲያመጣ በምንጠይቅባቸው የጸሎት ጊዜያቶች በፊቱ የምናሳልፈው ጊዜ እየጨመረ ይመጣል፤ ይህም እርሱን የሚያከብር፣ ለእኛ ጥቅም እና ለሌሎች በረከት የሚሆን ይሆናል።

ጥያቄ፡- የዌስትሚኒስቴር ካታኪዝም በእጣሬው ላይ ጸሎትን "እንደ ፈቃዱ የሆኑ መሻታችንን ለእግዚአብሔር በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፣ ከኃጢአት ኑዛዜ እና ስለ ምሕረቱ ካለው ምስጋና ጋር የምናቀርብበት ነው" ይለዋል። ይህ ትርጉም ካላችሁ የጸሎት ጊዜ ጋር እንዴት ይዛመዳል፣ በተለይም ከወንጌል ሥርጭት ጋር በማያያዝ መልሱ?

በወንጌል ሥርጭት ላይ ራሳችንን ወንጌልን ለመስበክ መዘጋጀትን በተመለከተ ለሌሎች ሰዎች ከመጸለይ በተጨማሪ ጸሎትን በሚከተሉት ሦስት መንገዶች ልንረዳው እና ልንተገብረው አንችላለን፡-

- አንደኛ፣ እንደ ወንጌላውያን አንደ እግዚአብሔር ልጆች እና ታዛዥ የክርስቶስ ደቀ-መዛሙርት የምናደርግበት መንገድ ነው።
- ሁለተኛ፣ ለወንጌል ሥራ የሚያነቃቃን ይሆናል። ክርስትናን ለምርጫ የምናቀርበው ሳይሆን የጠፉ ሰዎች ግድ የሚሉን (ቆላ. 4፡2-6) እና ለወንጌል ሥራ እግዚአብሔር ዕድልን እንዲሰጠን የምንጠይቅበት መንገድ ነው።
- ሦስተኛ፣ በመንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ ከፊት የጦር ዕቃችንን ለብሰን በመቆም ጠላትን የምንረታበት መንገድ ነው።

እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ እና ጢሞቴዎስ እርስ በርሳችን ለሰዎች ለመጸለይ የምንበረታታ እና ዓለም እርሱን ወደማወቅ እና ለእርሱ ወደመገዛት እንድትመጣ በተስፋ ለእግዚአብሔር ኃይል እየተገዛን እርሱን የምናስደስት እንድንሆን እንበረታታ።

**ውይይት** (10 ደቂቃ)

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች/ሃሳቦች ተወያዩባቸው**

- ወንጌልን ከመመስከራችሁ በፊት ወይም የመመስከር ዕድል ከማግኘታችሁ በፊት ያላችሁ የጸሎት ልምምድ ምንድን ነው?
- በወንጌል የመስበክ ተግባራችሁ ውስጥ ጸሎትን ትጠቀማላችሁ? ከተጠቀማችሁ እንዴት?
- "ስላልተመለሱ ጸሎቶች" ያላችሁ መረዳት ምንድን ነው? እና ካልተመለሱ ጸሎቶች ጋር የምንኖረው እንዴት ነው? ወንጌልን በመመስከር ሂደት ይህንን ጥያቄ ሰዎች ቢያነሡላችሁ በምን መንገድ ትመልሳላችሁ?

*" የሚመጣው መነቃቃት መጀመር ያለበት ከጸሎት መነቃቃት ነው። የዝናቡ መጨመር የሚሰማን በቤት ውስጥ፣ በድብቅ በራችንን ዘግተን ነው። ይህ የአገልጋዮች ድብቅ ጸሎት መጨመር የበረከት ምንጭ በር ነው።"*

አንድሪው ሙሬ

**ጸሎት** (20-30 ደቂቃ)

ለዚህ ክፍለ-ጊዜ የበለጠ ጊዜ ለጸሎት ለዩ፤ በሦስት የተለያዩ መንገዶች ጸልዩ፡-

እርስ በርሳችሁ ጊዜ ወስዳችሁ ጸልዩ። ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት እንዲያድግ ለጸሎት በትሕትና የተሰጠን ሰዎች አንድንሆን እግዚአብሔርን እንለምን።

**ለማኅበረሰባችሁ፣ መንደራችሁ እና ከተማችሁ በመጸለይ ጊዜ አሳልፉ። እግዚአብሔር የጠፉትን እንዲያድን እና ምድራችንን እንዲፈውስ እንፀልይ** (በሰፊው - ወንጌልን ዛሬ የምናውጅበትን ዕድል እግዚአብሔር እንዲሰጠን እና ልቦችን ወደ ሕይወት እንዲጠራ እንጸልይ)።

ለራሳችን ጊዜ ወስደን እንፀልይ - ወደ መንፈሳዊው ጦርነት የፊት ግንባር ስንወጣ፣ በጸሎት ትጥቃችንን በሚገባ ለመልበስ።

**ትግበራ** (5 ደቂቃ)

ክርስቶስን በማወቅ እንዳልዳኑ የምታውቋቸውን አምስት ሰዎች ከጓኞቻችሁ፣ ቤተሰቦቻችሁ፣ ከሥራ ባልደረቦቻችሁ ወይም ከማታውቋቸው ሰዎች መካከል መርጣችሁ ስማቸውን ዘርዝራችሁ ፃፉ። ሁልጊዜ ልታገኙት የምትችሉበት ቦታ ስልካችሁ፣ ቦርሳችሁ ወይም መጽሐፍ ቅዱሳችሁ ውስጥ አስቀምጡት። እግዚአብሔር ልባቸውን ወደ ወንጌል እንዲመልስ በታማኝነት ጸልዩላቸው።

**ተጠያቂነት** (15 ደቂቃ)

**የተጠያቂነት ቅጽ በመሙላት ለአጋራችሁ እና ለአነስተኛ ቡድናችሁ አጋሩት፤ እንዲሁም አንዳችሁ ለሌላችሁ ጸልዩ።**

**ማስታወሻ**

**ክፍለ-ጊዜ ስድስት**

**የወንጌላዊው ጥሞና**

***ወንጌላዊው “የመድረክ ላይ” እና “ከመድረክ ውጪ” ያለው ሕይወቱ ተመሳሳይ መሆን ይኖርበታል። በሕይወታችን እና በወንጌላዊነት ውስጥ እውነተኝነትን ልንጠብቅ ይገባል። በዚህ ክፍለ-ጊዜ ላይ ካለፈው የጸሎት ትምህርት ተነሥተን የሕይወታችን እና ወንጌላዊ አገልግሎታችን ውስጥ ጥሞና የሚያስፈልገው ለምን እንደ ሆነ እንመለከታለን።***

**ክፍለ-ጊዜው በአንድ ዐረፍተ-ነገር**

...............................................................................

በልባችን መለወጥ የሚታይ የመንግሥቱን ተስፋ መልዕክት በከንፈሮቻችን ላይ ይዘን ስንኖር፣ ከቅዱሱ ሰማያዊ አባታችን ጋር በጥሞና የምናሳልፈው ጊዜ የመንግሥቱ ውጤታማ እንደራሴዎችን እንድንሆን ይረዳናል።

**የክፍለ-ጊዜው ዳራ**

...............................................................................

ዮሴፍ እና ማርያም በየዓመቱ ከሚያደርጉት የፋሲካ በዓል ወደ ወደ ኢየሩሳሌም ጉዞ ሲመለሱ፣ ኢየሱስ አብሯቸው እንዳልነበረ ተገነዘቡ። ከሦስት ቀን ፍለጋ በኋላ፣ በመቅደስ ከመምህራን ጋር ተቀምጦ አገኙት። ኢየሱስ በ12 ዓመቱ ከጠቢብ መምህራን ጋር ተቀምጦ ሲያዳምጣቸው፣ እንዲሁም ሲጠይቃቸው እና ስለ ቅዱስ ቃሉ ባለው መረዳት ሲገረሙበት አገኙት። እነ ማርያም ኢየሱስን ለምን እንዳስጨነቃቸው ሲጠይቁት፣ ኢየሱስ በጥያቄዋ ሲገረም እንመለከተዋለን።

ኢየሱስ ሲገረም የምንመለከተው፣ ሰው የሚጠፋው የሚፈልጉት ሰዎች የት መፈለግ እንዳለባቸው ስለማያውቁ ብቻ ነው። መኖር ባለበት በአባቱ ቤት መሆኑን እንዴት ማወቅ አይችሉም ነበር? ይህ የሀገሪቱን ፕሬዝዳንት ከቤተ-መንግሥት ውጪ ፈልገን አጥተን፣ በቤተ-መንግሥት ቢሮው ውስጥ ስናገኘው “የት ነበርክ?” ብለን በመገረም ስንጠይቀው እንደማለት ነው?

ሉቃስ በወንጌሉ ኢየሱስ ለማርያም በአባቱ ቤት ስለ መሆኑ በሚገርም መንገድ ይመልሳል፣ “*ስለ ምን ፈለጋችሁኝ?* በአባቴ ቤት እሆን ዘንድ እንደሚገባኝ አላወቃችሁምን? አላቸው”(ሉቃ. 2፡49)። ይህ ንግግር የሚገልጸውን እውነት ያህል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚስተካከለው የለም። የኢየሱስ የመጀመሪያ የተናገራቸው ቃላት የእግዚአብሔር ልጅነቱን የሚገልፅ ነው።

የመስቀሉ ሥራ ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብነት በጸጋው ተቀላቅለን - የእግዚአብሔር ልጆች የመባል መብት ሰጥቶናል - ስለዚህ ጥያቄው መሆን ያለበት በእግዚአብሔር ቤት ጊዜን ስናሳልፍ ቤተኝነት ይሰማናል ወይ የሚል ነው።

በጥሞና ጊዜያቶቻችን ውስጥ ማን እንደ ሆነን እንገነዘባለን፤ እናድጋለን፤ እንለወጣለን፣ እንደፍራለን፣ ስለ ስህተቶቻችን እንገሠፃለን፤ በመኖራችን ውስጥ ሙሉ ትርጉም እናገኛለን፤ እርሱ ቅዱስ እንደ ሆነ ቅዱሳን እንሆናለን። በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ቅድስናን ለመገንባት ጥሞና ማዕከላዊ ነው። ይህ በቅድስና ሕይወት መመላለስ ላለበት መስካሪ አስፈላጊ ነው።

እግዚአብሔር በብስጭት ሳይሆን በደስታ “*የት ነበራችሁ?*” ብሎ ይጠይቀናል።

**የክፍለ-ጊዜው መምሪያ**

**(ከለሳ 10-20 ደቂቃ)**

...............................................................................

ሰዎች ያሉበትን ለማወቅ እና ለመበረታታት ጊዜ ውሰዱ። እርስ በርስ ታሪክ በመከፋፈል፣ ስለተገኙ ዕድሎች ያላችሁን ሃሳብ መከፋፈል እና ሌላ የትኛውንም ነገር በማንሣት እርስ በርስ ተነጋገሩ። በታማኝነት ልትጸልዩላቸው ለዘረዘራችኋቸው ሰዎች (የክፍለ-ጊዜ አምስት ትግበራ) የነበራችሁን የጸሎት ጊዜ እና የተገኘ የትኛውም ለውጥ ላይ ተነጋገሩ።

**ጸሎት**

**..........................................................................................**

ጊዜውን ለእግዚአብሔር በመስጠት እና በትውውቅ ጊዜ በተነሣ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ጉዳይ ላይ ጸልዩ።

**ትምህርት (20-30 ደቂቃ)**

**..........................................................................................**

*ራሳችሁ ልታቀርቡበት በምትችሉበት መንገድ ወይም ቃል በቃል ይህንን ትምህርት ማቅረብ ትችላላችሁ።*

*"ማለዳም ተነሥቶ ገና ሌሊት ሳለ ወጣ፤ ወደ ምድረበዳም ሄዶ በዚያ ጸለየ"* ማር. 1፡35

በሕይወት ውስጥ ለብዙ የተለያዩ ነገሮች ራሳችንን እንሰጣለን፤ ለቤተሰብ፣ ለጓደኞች፣ ለጤነኛ እሴቶች፣ ህልማችንን ለማሳካት እንሰጣለን። ወይም፣ ለምንወዳቸው ነገሮች፣ ለምንደግፈው ቡድን፣ ወይም በሞባይላችን ላይ ለምንጫወተው ጨዋታ ትልቅ ውጤት ለማምጣት እንሰጣለን።

ኢየሱስ በትምህርቱ ላይ ቤተሰብን ከቤተሰብ ልለይ (ሉቃ. 12፡53) ያለው ለምንድን ነው? ይህንን መገንዘብ የሚገባን ኢየሱስ ዋነኛ መሰጠቱ ለሌሎች መልካም ከሆኑ መሰጠቶች ሁሉ በላይ በሰማይ ላለ አባቱ እንደ ሆነ ይናገራል። ኢየሱስ የሕይወት አጋራችንን አለመውደድም ሆነ ቤተሰቦችን እንዲሁ ለመከፋፈል ሳይሆን እግዚአብሔር መሰጠታችሁን የሚወስድ የትኛውንም ነገር ከቅድስና የሚለየን እንደ ሆነ ለማሳየት ነው። ለእግዚአብሔር ባለን መሰጠት ውስጥ ነው በቅድስና ለመኖር የምንችለው።

*ጥያቄ፡- ከጥምና ጊዜያቶቻችን የሚወስዱን/የሚያስቀሩን ነገሮች ምንድን ናቸው? በራሳቸው መጥፎ/ኃጢአት ሳይሆኑ፣ ነገር ግን ሀሳብ/ጊዜን በመውሰድ ወይም ለእግዚአብሔር እንደሚገባ ላለመስጠት የሚከለክሉን ነገሮችን ምንድን ናቸው?*

**ከኢየሱስ ይልቅ ለወንጌል ሥራ አብዝተን እንሰጥ ይሆን?** ንጉሡን ኢየሱስን እንድናመልክ እንጂ አገልግሎታችንን እንድናመልክ አልተጠራንም። በሚገባ በመንፈሳዊ ሕይወታችን ውስጥ ተተክለን እግዚአብሔርን እንደሚገባ መስማት አለብን።

ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ፣ ከነበረው አገልግሎትም ሆነ ማኅበራዊ ግንኙነቶች ሁሉ በላይ ጊዜ በመውሰድ፣ በመጸለይ እና በማዳመጥ ከአባቱ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን የግል ግንኙነት ላይ ያተኩራል። ለኢየሱስ እጅግ አስፈላጊው እና ዋነኛው ቦታ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነት ነው። የማርቆስ ወንጌል ይህንን በሦስት የተለያዩ ቦታዎች ላይ ኢየሱስ ተለይቶ ጊዜ ሲወስድ እንመለከታለን፤ የሚከተሉት ክፍሎችን ጊዜ ወስዳችሁ ተወያዩባቸው፡-

- ማር. 1፡3-39 - በማለዳ ተነሥቶ ብቻውን ጊዜ በመውሰድ ይጸልያል - ይህ ከእግዚአብሔር መመሪያን ስለመቀበል ምን ያስተምረናል?
- ማር. 6፡45-46 - ወደ ተራሮች በመውጣት ጊዜን መውሰድ - መታደስን ከእግዚአብሔር ስለ መቀበል ይህ ክፍል ምን ያስተምረናል?
- ማር. 14፡ 32-41 - ከመያዙ በፊት በጌተ-ሰማኔ መጸለዩ - የሚከብደንን ነገር ወደ እግዚአብሔር ስለማምጣት ይህ ክፍል ምን ያስተምረናል?

በቀን ውሎአችን ውስጥ ድንገተኛ እና ያላቀድናቸው ጸሎቶች መልካም ናቸው። ነገር ግን፣ መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ እና ለመጸለይ ጊዜን መለየት አስፈላጊ ናቸው። አንዳንዶች መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ ጎበዞች ሲሆኑ፣ ጸሎት ላይ ግን አይበረቱም። ሌሎች ግን የጸሎት ሕይወታቸው አስደናቂ ሆኖ መጽሐፍ ቅዱስን የማንበብ ልምምዳቸው ግን ደካማ ነው። እነዚህን ሁለት ልምምዶች አብሮ ማካሄድ ይጠቅማል። አንድ ወይም ሁለት ምዕራፎችን በማንበብ በዚህ ላይ መጸለይ፤ በዚህ ጸሎት ላይ ምስጋናን እና ልመናን አብረን ማቅረብ ይኖርብናል።

ኢየሱስ የሚናዘዘው ኃጢአት አልነበረም። ነገር ግን፣ ንስሃ አስፈላጊ ስለ ሆነ ለደቀ መዛሙርቱ ያስተምራቸዋል፣ *"ኃጢአታችንን ማረን"* (ማቴ. 6፣ ሉቃስ 11)። መዝሙር 51 ለንስሃ እና ለልመና ልንጠቀምበት የምንችለው ክፍል ነው።

ቅድስናን በሕይወታችን ለመለማመድ የመጀመሪያ ርምጃችን መሆን ያለበት እግዚአብሔር ቅዱስ እንደ ሆነ እና እኛ ኃጢአተኞች እንደሆንን መረዳት ነው። እግዚአብሔር ለሕይወታችን ያስፈልገናል - ወደ ፊቱ በቀረብን ቁጥር ሕይወታችንን በሚያድሰው ፍቅር ይለውጥልናል። ይህ የሕይወታችን ለውጥ የወንጌልን እውነተኝነት እና የማዳን ኃይል የሚያሳይ ነው። የእግዚአብሔርን መልካምነት እና የኢየሱስን ታሪክ ስንሰብክ፣ በሙላት የተሰጠው ሕይወታችን የምንሰብከውን ወንጌል እውነተኝነት እና የምንሰብክበት ድፍረት ይሰጣል።

ኢየሱስ በመስቀሉ ሥራ ቅዱሳን የምንሆንበትን መንገድ አዘጋጅቶልናል። ይህም የድሮ ማንነታችንን እንድንጥል እና መታመናችንን ወደ እርሱ እንድናደርግ ይጠራናል። ወደዚህ አዲስ ሕይወት ስንገባ፣ መደበኛ በሆነ የጥሞና ሕይወታችን ወደ ቅድስና እንዴት እንደምንደርስ ኢየሱስ በምድር ላይ በኖረው ሕይወቱ አስተምሮናል።

**ውይይት (10 ደቂቃ)**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች/ሃሳቦች ተወያዩባቸው፤**

- የጸሎት እና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችሁን እንዴት ትገልጹታላችሁ?
- የጥሞና ሕይወታችሁ ጤነኝነት እና የወንጌላዊነት አገልግሎት ጥራት መካከል ያለውን ትስስር አስተውሉ እና ተወያዩ?
- በሚቀጥሉት ሳምንታት ውስጥ ራሳችሁን ለበለጠ ምሪት፣ መታደስ፣ እይታ እና ንሰሃ እንዴት ማዘጋጀት ትችላላችሁ?

*"የመንፈሳዊ ልምምድ አላማ ነፃነት ነው፤ ግባችን ነፃነት ነው እንጂ ልምምድ አይደለም። ልምምዱን ዋና አላማ ስናደርገው በዚያ ሰዓት ስርዓት ሆኖብን ነጻነታችንን እናጣለን. . .፤ ትኩረታችንን ሁልጊዜ ኢየሱስን በማድረግ መንፈሳዊ ልምምዶቻችን ወደ እርሱ ልብ የምንቀርብባቸው ይሁኑልን"*

*ሪቻርድ ፎስተር*

**ትግበራ (5 ደቂቃ)**

መዝሙረ ዳዊትን ተከትለን መጸለይ እንጀምር፣ በየቀኑ ለጥቂት ሰዓታት ከሌላው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና የጸሎት ጊዜ በተጨማሪ፣ በማንበብ እና በጸሎት ጊዜ እናሳልፍ። ከተቻለ፣ ይህንን ለሙሉ ወር ወይም አመት ተለማመዱት። ይህንን ለማድረግ በየቀኑ አንድ የመዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ በማንበብ መሥራት ትችላላችሁ፤ ወይም የተለያዩ የአመት የመጽሐፍ ቅዱስ ማጥኛዎችን መጠቀም ትችላላችሁ (እንደ Tim Keller's My Rock, My Refugee: A Year of Daily Devotion in the Psalms ያለውን ተጠቀሙ)።

**ጸሎት (20-30 ደቂቃ)**

ከልጆቹ ጋር ግንኙነት ማድረግን የሚሻ የሰማይ አምላክ ስላለን እግዚአብሔርን እናመስግን። በመገኘቱ እና በቤቱ ውስጥ እንደ ልጆች የሚያኖር የእግዚአብሔር ልጅነት በሙላት እንዲገኝባችሁ እና ከመንፈሳዊ ባዳነት የምትወጡበትን ሕይወት ለማዳበር የምትችሉበትን የጥሞና ጊዜ እንዲሰጣችሁ ጸልዩ። እግዚአብሔር ቅዱስ እንደ ሆነ የቅድስናን ሕይወት እንዲሰጣችሁ እና ይህ የሕይወታችሁ ለውጥ የወንጌላዊነት አገልግሎታችሁ የሚገነባበት እንዲሆን ጸልዩ።

**ተጠያቂነት (15 ደቂቃ)**

የተጠያቂነት ቅጽ በመሙላት ለአጋራችሁ እና ለአነስተኛ ቡድናችሁ አጋሩት እንዲሁም አንዳችሁ ለሌላችሁ ጸልዩ።

**ማስታወሻ**

**ክፍለ-ጊዜ ሰባት**

***የወንጌላዊው መገዛት***

**ካለፈው ክፍለ-ጊዜ ላይ ስለ ቅድስና ያነሣነው ሃሳብ ላይ በመጨመር የምንማርበት ክፍለ-ጊዜ ነው። ከእግዚአብሔር ማንነት፣ የወንጌል ተስፋ እና የወንጌላዊው ሕይወት ጋር በተለየ እናዛምዳለን። በደቀመዝሙሩ የሕይወት ጉዞ ውስጥ የተጠያቂነት አስፈላጊነትን እንመለከታለን።**

**ክፍለ-ጊዜው በአንድ ዐረፍተ-ነገር**

**..................................................................................**

እግዚአብሔር ቅዱስ እንደ ሆነ፣ ህዝቡ ቅዱሳን እንዲሆኑ ይፈልጋል። በቅድስና ማደግ የምንችለው ለመንፈስ ቅዱስ ስንገዛ እና ለመንፈሳዊ ማኅበር ተጠያቂነት ሲኖረን ነው።

**የክፍለ-ጊዜው ዳራ**

'ቅድስና' እና 'ቅዱስ' የሚሉት ቃላት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከ900 ጊዜ በላይ ተጠቅሰዋል። ፍቅር፣ እምነት፣ ይቅርታም ሆነ ጸሎት የሚሉት ቃላት ሁሉ ተደምረው 'ቅዱስ' የሚለውን ያህል አልተጠቀሱም። ቅድስና የመጽሐፍ ቅዱስ ዋና ሃሳብ ሲሆን እግዚአብሔር ለሕይወታችን ያለው ዋና አላማ ነው።

እግዚአብሔር ቅዱስ ነው፤ ይህ ማለት እግዚአብሔር የተለየ ነው ማለት ነው። እግዚአብሔር ፍፁም፣ ሉዐላዊ እና ልዩ ነው፤ እርሱን የሚመስል ማንም የለም ማለት ነው። ማንም ከመካከላችን ቅዱስ የለም! ቅዱስ ከሆነው የእግዚአብሔር መለኪያ ጎድለናል። የዕብራውያን ጸሐፊ ቅዱሳን የሆኑት ብቻ እግዚአብሔርን እንደሚመለከቱት ይነግረናል (ዕብ. 12፡14)። እንዲሁም፣ ኢየሱስ ልባቸው ንፁህ የሆኑ እግዚአብሔርን እንደሚያዩት አስተምሮናል (ማቴ. 5፡8)። ከእግዚአብሔር ጋር ማንኛውም አይነት ግንኙነት እንዳይኖረን የሚጋርደን በሕይወታችን ውስጥ የቅድስና አለመኖር ነው። ኃጢአተኞች የሆኑ ቅዱሳን፣ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያላቸውና በመንግሥቱ ውስጥ የሚኖሩ መሆን እንዴት ይችላሉ?

መልካሙ ዜና ኃጢአተኞች ወደ ፍፁም እና ቅዱስ ወደ ሆነው የእግዚአብሔር መገኘት እና ከእርሱም ጋር ዘላለም የሚኖሩበትን መንገድ ኢየሱስ አዘጋጅቶላቸዋል (ኤፌ. 5፡25-26)። መታመናቸውን በኢየሱስ የሚያደርጉ ሰዎች ቅድስናን ከእርሱ ስለሚካፈሉ አዲስ ሕይወት ይኖራቸዋል። እውነተኛ ሕይወት ቅድስና ያለበት ሕይወት ነው።

የኢየሱስ ክርስቶስ የምድር ጨውነት ትምህርት ላይ ቅድስና ዋናው ጭብጥ ነው። ጨው ጣዕሙን ካጣ፣ ጥቅም አልባ እንደ ሆነ ሁሉ የሚለየን ቅድስና ከሌለበት የምንሰብከው መልዕክትም ተስፋ-ቢስ ይሆናል። በሚመጣው የዘላለም ሁኔታ ውስጥ ሕይወታችን ያላለቀ ታሪክ አካል ቢሆንም፣ መጠራታችን ግን በልዩነት በመኖር የምንሰብከውን ወንጌል እውነተኝነት ለዓለም መናገር ነው።

ወንጌል ቅዱስ መልዕክት ነው። ቅዱስ የሆነ አምላክ ቅድስና ያልነበራቸውን ሰዎች ቅዱስ በሆነ መንገድ ወደ እውነተኛ ማንነታቸው - የቅዱስ መንግሥት ቅዱስ ህዝቦች እንዲሆኑ የሚጠራበት መልዕክት ነው።

**የክፍለ-ጊዜው መምሪያ**

**(ከለሳ 10-20 ደቂቃ)**

**............................................................................................**

ሰዎች ያሉበትን ለማወቅ እና ለመበረታታት ጊዜ ውሰዱ፤ እርስ በርስ ታሪክ በመከፋፈል፣ ስለተገኙ ዕድሎች ያላችሁን ሃሳብ መከፋፈል እና ሌላም የሚጠቅማችሁን ነገር በማንሣት እርስ በርስ ተነጋገሩ። የቡድኑን አባላት በመዝሙረ ዳዊት ጥናት የተመራ የጸሎት ጊዜያችሁ ላይ ተወያዩ (ክፍለ-ጊዜ ስድስት - ትግበራ)

**ጸሎት**

.................................................................................

ጊዜውን ለእግዚአብሔር በመስጠት እና በትውውቅ ጊዜ በተነሣ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ጉዳይ ላይ ጸልዩ።

**ትምህርት (30-40 ደቂቃ)**

.................................................................................

ራሳችሁ ልታቀርቡበት በምትችሉበት መንገድ ወይም ቃል በቃል ይህንን ትምህርት ማቅረብ ትችላላችሁ።

1. እግዚአብሔር ብቻውን ቅዱስ ነው፤
   *"ቅዱሱ ስሜ በሕዝቤ በእስራኤል መካከል ይታወቅ ዘንድ አደርጋለሁ፣ ቅዱሱንም ስሜን ከእንግዲህ ወዲህ አላስረክስም፤ አህዛብም እግዚአብሔር የእስራኤል ቅዱስ እኔ እንደሆንኩ ያውቃሉ"* ሕዝ. 39፡7

እግዚአብሔርን በእውነት እና በመንፈስ እንድናመልከው መጽሐፍ ቅዱስ ማን እንደ ሆነ ይነግረናል። መጽሐፍ ቅዱሳችንን ባነበብን ቁጥር እግዚአብሔር አንዱ እውነተኛ አምላክ እንደ ሆነ ይነግረናል። በሥሉስ ማንነት ሳይከፋፈል ያለ እንደ ሆነ (አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ)። እርሱ ፍፁም ነው። እርሱ ዘላለማዊ ነው። እርሱ ንጉሥ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ከእነዚህ የእግዚአብሔር ማንነቶች በበለጠ ግልጥ አድርጎ የሚያሳየን ማንነቱ - ቅዱስ መሆኑን ነው። ቅድስና የእግዚአብሔር ዋነኛ ማንነቱ ነው። ይህ ማለት እግዚአብሔርን የሚመስል ማንም እንደሌለ እና እርሱ ከሁሉ ተለይቶ የሚኖር፤ ማንም በማንነት፣ በባህርይም ሆነ እግዚአብሔር በሆነው ሁሉ ሊስተካከለውም ሆነ ሊመሳሰለው የማይችል ነው ማለት ነው። እግዚአብሔር ይህንን ባህርይ ነው ለህዝቡ የሚፈልገው - ቅዱስ ህዝቦች እንድንሆን - በአምልኳችን እና በመታዘዛችን እርሱን የምንመስል፣ ጽድቅ እና ንጽህና በሕይወታችን ያለ የተለየን ቅዱስ ህዝብ እንድንሆን ይፈልጋል (ዘሌ. 11፡45)። ቅድስና በእኛ ውስጥ አለመኖሩ እንዲሁም የእግዚአብሔርን ቅድስና መካዳችን በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ትልቅ ቀውስ አስከትሏል። የእግዚአብሔር መንግሥት ፍጹም መንግሥት ነች፤ ሰው ግን ለእግዚአብሔር ከመገኘት ይልቅ አመጽን እና ከእርሱ መለየትን መርጧል።

2. የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስነት የእርሱ ለሆኑት ሁሉ ቅድስናን የሚያስገኝበትን ዕድል ሰጥቶታል

*"ኢየሱስ ግን ለዘለዓለም የሚኖር በመሆኑ፣ ክህነቱ የማይሻር ነው። ስለዚህ ስለ እነርሱ እየማለደ ሁልጊዜ በሕይወት የሚኖር በመሆኑ፤ በእርሱ በኩል ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል። እንግዲህ ለእኛ የሚያስፈልገን፣ ቅዱስ፣ ነቀፋ የሌለበት፣ ንጹሕ፣ ከኃጢአተኞች የተለየና ከሰማያት በላይ የከበረ እንደነዚህ ያለ ሊቀ ካህናት ነው። እርሱ እንደ ሌሎቹ ሊቀ ካህናት፣ መጀመሪያ ስለ ራሱ ኃጢአት ከዚያ ስለ ህዝቡ ኃጢአት በየቀኑ መሥዋት ማቅረብ አያስፈልገውም፣ ራሱን በሰጠ ጊዜ፣ ስለ ኃጢአታቸው ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ መሥዋትን አቅርቦአልና። "*

ዕብራውያን 7፡24-27

ሰዎች በእግዚአብሔር አምሳል ስለተፈጠርን እንደ እርሱ ቅድስናን መለማመድ እንችላለን፤ ነገር ግን የሰው አመጸኝነት ይህ እንዳይሆን ከልክሎአል። የእግዚአብሔር መንግሥት ፍጹም ነው። በዚህ መንግሥት ውስጥ የትኛውም አይነት ትንሽ የሆነ አመፅን ቢፈቅድ፣ መንግሥቱ ፍጹም አይሆንም። በመሆኑም ቅድስናን አለመፈለጋችን ፍጹም ከሆነው የእግዚአብሔር እና ከመንግሥቱ በረከት ያጎድለናል።

ኢየሱስ ክርስቶስ በእኛ ፈንታ በመሆን በመስቀል ላይ ሞታችንን እንደሞተልን ወንጌል ይነግረናል፤ ኢየሱስ ሞታችንን ሊወስድልን የቻለው እርሱ ፍፁም ቅዱስ እና ያለ ነቀፋ ስለ ሆነ ነው። በፍጹም መታዘዝ ሞትን በወሰደልን ክርስቶስ ኢየሱስ ሊከፈል የማይችለውን የዓለም አመጽ ሊወስድልን ችሏል። ይህም ሊከፈል የቻለው ሊጠፋ በማይችለው የክርስቶስ ቅድስና ውስጥ የሰውን ኃጢአት ደሞዝ ከፍሎበታል። በመሆኑም፣ እግዚአብሔር አሁን በክርስቶስ ኢየሱስ እምነታቸውን ያደረጉትን ሰዎች ሲመለከት ነቀፋቸውን/ከቅድስና መጉደላቸውን ሳይሆን የክርስቶስን ቅድስናና ፍጽምና ነው የሚመለከተው።

ይህንን አስቡ - በለበሳችሁት ልብስ ምክንያት በራስ መተማመን የተሰማችሁን ጊዜ አስታውሱ፤ ለተለየ ፕሮግራም በጥሩ ሁኔታ ለብሳችሁ ይሆናል - ከቤት ስትወጡ ለሌላው ጊዜ በተለየ መልኩ በራሳችሁ ተደስታችሁ ሊሆን ይችላል። እምነታችንን በክርስቶስ ኢየሱስ ላይ ስናደርግ፣ እግዚአብሔር የክርስቶስ ኢየሱስን ቅድስና ሰጥቶ ይመለከተናል፤ ይህም ማለት፣ እኛ የክርስቶስን ፍጽምና ለብሰናል ማለት ነው (ሮሜ 5፡18፣ ፊል. 3፡9 እና 1 ቆሮ. 1፡30)።

ሐዋርያው ጳውሎስ በስጋችን መሻት ከመፈጸም ይልቅ፣ "ክርስቶስን መልበስ" እንዳለብን ይነግረናል - ይህም ማለት የክርስቶስን መልካምነት መልበስ አለብን ማለት ነው (ሮሜ 13፡14)። ይህንን ከሐዋርያው ያዕቆብ መልዕክት ጋር ስናነጻጽረው እርኩሰትን ሁሉ እንዲያስወግዱ አንባቢዎችን ያሳስባቸዋል (ያዕ. 1፡21)። ከእግዚአብሔር ጋር ጠላትነትን ያመጣብንን አሮጌ ማንነት ጥለን በክርስቶስ የተዘጋጀልንን የእርሱን ቅድስና መልበስ አለብን።

የማይመጥን ልብስ ስለ ለበሳችሁ ወደ ተለያየ ቦታ እንዳትገቡ ተከልክላችሁ ታውቁ ይሆን? ፍጹም ወደሆነው የእግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት የሚጠበቅብን በእኛ ዘንድ የሌለ ፍጹም ቅድስና ብቻ ነው። አሁን ግን ወደዚህ የማይገባን መንግሥት በክርስቶስ ኢየሱስ ከለበስነው ቅድስና የተነሣ መግባት ችለናል፤ ይህ መንግሥት ከቅድስና ውጪ ተቀባይት አይኖረንም በክርስቶስ ኢየሱስ የተሰጠንም ፍጹም ቅድስና ይህንን አስችሎናል። የእግዚአብሔርን መንግሥት በሙላት ስንገባበት፣ የራሳችንን ኃጢአት ሳይሆን በክርስቶስ የለበስነውን ቅድስና ይዘን ነው።

3. ለመንፈስ ቅዱስ መገዛት እና ራስን መግዛት ቅድስና ያለበትን ሕይወት ያፈራል

*"ደግሞም በአእምሯችሁ መንፈስ እንድትታደሱ እውነተኛ በሆነው ጽድቅ እንዲሁም ቅድስና እግዚአብሔርን እንዲመስል የተፈጠረውን አዲሱን ሰው እንድትለብሱ ነው።"*

ኤፌ. 1፡23-24

እግዚአብሔር በመደበኛ እና ዕለታዊ ሕይወታችን ኃጢአትን እንድንለማመድ ሳይሆን በመብሰል እንድናድግ ይፈልጋል። በጸጋው ተሸፍነናል፤ የእውነተኛ እና የተሰጠ እምነት ማስረጃ ለውጥ እና ዕድገታችን (ደቀ-መዝሙርነት) ነው። በክርስቶስ ያገኘነውን የእርሱን ቅድስና ኃጢአትን ለመለማመድ የምንጠቀምበት ሳይሆን በመታዘዝ በመኖር የተከፈለልንን የቅድስና ዋና በሚገባ በማክበር መኖር ይገባናል። ይህ የደቀ መዝሙርነት ጉዟችን ነው - ጌታን ካገኘንበት የመጀመሪያው የድነት ሁኔታ ተነሥተን ወደ ቅድስና ፍጻሜ ድረስ መለወጥ አለብን። ይህ ወደፊት የሚጠብቀንን ዘላለማዊ የሆነ ፍጽምናን ብቻ ሳይሆን ዛሬ ላይ ትርጉም ባለው መልኩ የምንኖርበትን መንገድ ያሳየናል።

በእውነተኛ የክርስቶስ አማኝ ሕይወት ውስጥ ያለውን ለውጥ ሐዋርያው ጳውሎስ በሕይወቱ በሚታዩ መንፈሳዊ ፍሬዎች ውስጥ ያሳየናል (ገላ. 5፡22-23)፤ ከተዘረዘሩት የመንፈስ ፍሬዎች የመጨረሻው ራስን መግዛት ነው፤ እግዚአብሔር በመንፈሱ ራሳችንን እንድንገዛ ያስችለናል። እኛም ከእርሱ ጋር የዚህ ሥራ ባልደረቦች መሆን ይገባናል (ፊል. 2፡12-13)።

ይህንን በሃሳባችን በመያዝ የሚከተሉትን አራት ተግባራዊ ልምምዶችን በመከተል በቅድስና እና መታዘዝ ልናድግ እንችላለን፡-

<u>ጥሞና</u>

በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ጊዜን ባሳለፍን ቁጥር፣ እግዚአብሔር እንድንሆን የሚፈልገውን እናውቃን። እንዲሁም በጸሎት በምናሳልፈው ጊዜ ውስጥ ድካማችንን እና ፈተናዎችን የሚያሳልፍ ኃይል ከእግዚአብሔር መጠየቅ እንችላለን። ከኢየሱስ ጋር ጊዜ ማሳለፍ ማለት ቅድስና ምን እንደ ሆነ መረዳት እና ለመቀደስ ዐቅምን ማግኘት ነው።

<u>ራስን ማወቅ</u>

ቅዱስ ቃሉን ባነበብነው ልክ፣ ቅዱስ ቃሉ እኛን ያነብበናል - ራሳችንን እንድንመረምር እና የበለጠ ራሳችንን እንድናውቅ ዕድል ይሰጠናል። ይህ ራስን ማወቅ ድካማችንን በመረዳት ጉዳትን/ችግርን በእኛ ላይ ለሚያመጡብን ነገሮች ራሳችንን እንድንክድ ያደርገናል።

<u>ኅብረት/ኅብረተሰብ</u>

ለምንኖረው ሕይወት ንቁ የምንሆነው ራሳችንን በማወቅ ብቻ ሳይሆን፣ ግልጽ ለሆነ፣ በፍቅር ለሆነ ግምገማ ራሳችንን ለክርስቲያናዊ ኅብረት ስንሰጥ ነው። በኅብረት ውስጥ መሰጠት ማለት ሌሎች በሕይወታችን ላይ እንዲሠሩ እኛም ደግሞ

በሌሎች ላይ የመሥራት ዕድል እንዲኖረን ያደርጋል። ለሰዎች ግልጽ መሆን የሚያመጣቸው ችግሮች ቢኖሩም፣ ይህ ግን በግል እንዲሁም እንደ እግዚአብሔር ቤተሰብ ልናድግባቸው ከምንችላቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ከሆኑ ርምጃዎች ሊለየን አይገባም።

<u>ንስሃ</u>

ያዕቆብ ኃጢአታችንን እርስ በርሳችን እንድንናዘዝ የሚነግረን ኃጢአታቸን እንዲማርልን ሳይሆን ለእርስ በርስ ለሆነ ተጠያቂነት ነው (ያዕ. 5፡16)። ስለ ውድቀታችሁ፣ የሕይወት ፈተናዎቻችሁ እንዲሁም የሚያስቸግራችሁ ነገሮች የምታካፍሉት ኅብረት በሕይወት ውስጥ አስፈላጊ ነው። ጠላታችን ትግላችን በግላችን ጨለማ ውስጥ በእፍረት እንድንሸማቀቅ ነው፤ እግዚአብሔር ግን እርስ በርሳችን እየተደጋገፍን፤ ውድቀታችንን እየተናዘዝን አንዳችን ለአንዳችን ተጠያቂዎች በመሆን ወደ ብርሃን የመጣውን ሕይወታችንን ሊምር እና ሊያድስ ስለሚፈልግ ነው። **በእግዚአብሔር ዘንድ ውድቀት መጨረሻ አይደለም።** ነገር ግን ተጠያቂነት ከድካማችን ጋር በትሕትና እና ለእርሱ ፀጋ በመሰጠት የምንለወጥበት መንገድ ነው።

አንደ ወንጌላውያን፣ መጠራታችን ሰዎቸን ለወንጌል ምላሽ እንዲሰጡ ብቻ ሳይሆን፣ ሰዎች ደቀ-መዝሙር ለመሆን አንዲያድጉ እና ወደ ቅዱስ ህዝብነት እንዲለወጡ ነው (ቆላ. 1፡28-29)። እውነተኛ ደቀ-መዛሙርት ብቻ ናቸው ይህንን መልዕክት ተቀብለው በእውነት፣ በኃይል እና በታማኝነት ወደ ዓለም መሮጥ የሚችሉት - ይህ ለቅዱስ ሰዎች የተሰጠ ቅዱስ ሥራ ነው።

**ውይይት (15 ደቂቃ)**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች/ሃሳቦች ተወያዩባቸው**

- እግዚአብሔርን ለማያውቅ ሰው የእግዚአብሔርን ቅድስና እንዴት ታስረዳዋለህ/ጂዋለሽ?
- ክርስቶስን መልበስ የምንችለው እንዴት ነው?
- ለሌሎች በእውነተኛ ተጠያቂነት እንዳይኖርህ/ሽ የሚገድብህ/ብሽ ምንድን ነው?

"ከክርስቶስ ርቀን በቅድስና እየኖርን ነው ብለን ብናስብ፣ ታላቅ ስህተት ተሳስተናል፤ ቅዱስ ለመሆን ወደ ክርስቶስ የቀረበ ሕይወት ያስፈልገናል"

ቻርልስ ስፐርጀን

**ትግበራ (5 ደቂቃ)**

በግልጽ የምታወቃቸው እና በመደበኝነት እየተገናኛችሁ አንዳችሁ ለሌላችሁ ተጠያቂነት ያለበት የጓደኛ ኅብረት (ለዚህ የአድቫንስ ቡድን የተመሠረተው የተጠያቂ ቡድን ውጪ) ከሌላችሁ፣ ይህንን አብራችሁ ማድረግ የምትችሏቸውን ሰዎችን ፈልጋችሁ በተቻለ ፍጥነት ኅብረትን ለመመሥረት ሞክሩ። ይህ አይነት ቡድን ካላችሁ፤ ለሌለው አንድ ሰው አስፈላነቱን አስረድታችሁ እንዲመሠርት የሚያስፈልገውን ምክር በመስጠት አበረታቱት።

**ጸሎት**

የእግዚአብሔርን ቅድስና የምትመለከቱበት እና ስለ ቅድስናው የምታመሰግኑበት ጊዜ በጸሎት ውሰዱ። ስለ አመጻችሁ ንስሃ በመግባት በክርስቶስ ኢየሱስ ስላገኛችሁት ጽድቅ እግዚአብሔርን አመስግኑት። እንዲሁም እግዚአብሔር በሕይወታችሁ የጀመረውን የጽድቅ ሥራ እንዲጨርስ እየጠየቃችሁ ለቅዱስ ሥራ የተዘጋጁ ቅዱሳን ሰዎች የሚያደርጋችሁን ራስን መግዛት ያለበት መታዘዝ በሕይወታችሁ እንዲያድግ ለምኑ።

**ተጠያቂነት (15 ደቂቃ)**

የተጠያቂነት ቅጽ በመሙላት ለአጋራችሁ እና ለአነስተኛ ቡድናችሁ አጋሩት፤ እንዲሁም አንዳችሁ ለሌላችሁ ጸልዩ።

*በዚህ ክፍለ-ጊዜ በተጠያቂነት ቅጽ ላይ ያሉትን ጥያቄዎችን ጊዜ ወስዳችሁ በሚገባ ተመልከቱ፤ ምላሽን በመስጠት በጸሎት ጊዜ ውሰዱባቸው።*

**ማስታወሻ**

**ክፍለ-ጊዜ ስምንት**

**የወንጌላዊው ባሕርያት**

**ክርስቲያኖች በሕይወታቸው ትሕትና ያለባቸው ክርስቲያኖች ናቸው። ለመሆኑ ትሕትና ያለበት ወንጌላዊነት ምን ይመስላል?**

**ክፍለ-ጊዜው በአንድ ዐረፍተ-ነገር**

**..............................................................................**

ከክርስቶስ ኢየሱስ የተመለከትነው መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን የሠራው እና የታጠቅነው ለእግዚአብሔር ክብር የሆነው የወንጌላዊው ዋና ባህርይ ትሕትና ነው።

**የክፍለ-ጊዜው ዳራ**

**..............................................................................**

መልአኩ ገብርኤል ኢየሱስን መጸነሷን ከነገራት ጊዜ ጀምሮ በኢየሱስ ሕይወት ውስጥም የምንመከተው ዋና ሃሳብ - ይጀምራል - ትሕትና። ማርያም እግዚአብሔር ከሁሉ የምታንሰውን ባርያ ስላሰባት ታመሰግነዋለች። በሌላ በኩል ማርያም "እኔ ከሌላ ሰው የተለየሁ አይደለሁም፤ እግዚአብሔር ሊጠቀምብኝ የወደደው እንዴት ነው?" ማለቷ ነው።

እግዚአብሔር ለምን እንደሚጠቀምብህ/ሽ አስበህ ታውቃለህ/ሽ?

በራሳችን ስጦታዎች እና ችሎታዎች ላይ በመተማመን እግዚአብሔር ለሥራው የመረጠን በእነዚህ ምክንያቶች ይመስለናል። የእግዚአብሔር መጥራት ትሕትናን ዋና ማዕከሉ ካደረገው ባህርይ ጋር እንጂ ከችሎታዎቻችን ጋር አይገናኝም። ማርያም በምስጋና ዝማሬዋ ላይ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን እንደሚያዋርድ ለትሑታን ግን ፀጋን እንደሚጨምር ትናገራለች - ይህንን የምትናገረው ወጣት አይሁዳዊት በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከተመለከተችው የእግዚአብሔር ማንነት እና ሥራ ላይ በመነሣት ነው። ይህንን በድፍረት የተናገረችውን እውነት አሁን በሕይወቷ እየተለማመደችው ነበር። እግዚአብሔር በማይጠበቅ መንገድ የዓለምን ጥበብ እና ኃይል ሁሉ በመገልበጥ፣ በትሑታን በመሥራት ሃይሉን እና ፀጋውን በሚጠብቁ ሰዎች ውስጥ ይገልጣል። እግዚአብሔር በእኛ ታላቅን ሥራ እንዲሠራ የምንፈልግ ከሆነ የመጀመሪያው ርምጃ ሙሉ በሙሉ በእርሱ መታመን አለብን።

የኢየሱስ ክርስቶስ ውልደት ታላቅ ትሕትና ማሳያ ነው፤ የነገሥታት ንጉሥ በከብቶች ማደርያ በበረት ውስጥ ነበር የተወለደው - የታላቅ ንጉሥ ውልደት ሃብቶች ሁሉ እንደ ማንም በተወለደው ድህነት ተተኩ - የሁሉ ባለቤት የሆነው እግዚአብሔር ጋር ያለን መታረቅ የተጀመረው በታላቅ ትሕትና ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጠበት አገልጋይ - ንጉሥነት፣ ማንነት በኢሳያስ 53 ላይ ያለው የሚሰቃየው ባርያም ሆነ በመስቀል ላይ ስለ በደላችን መወጋቱም ሆነ ደቀመዛሙርቱን እግር ማጠቡ እና ሊያገለግል እንጂ ሊገለገል አለመምጣቱ እስከ ጌቴሰማኔ ድረስ የአባቱን ፈቃድ ለመፈጸም መትጋቱ እና በአንድ ቃል ሊያጠፋቸው የሚችላቸው ሰዎች እያፌዙ ሲያሰቃዩት ሊገልጥልን የወደደው ይህንን ነው - ክርስቶስ በቅዱስ ትሕትናው የሰውን የእርግማን ኩራት መስበሩን ነው።

እግዚአብሔር ህዝቡን ያዳነበት መንገድ ልንኖርበት የሚያስፈልገው መንገድ ነው። የትዕቢት ውጤት ጥፋት ብቻ ነው ትሕትና ግን ያቀናናል።

*"የጌታን የኢየሱስ ክርስቶስን ፀጋ ታውቃላችሁና፤ በእርሱ ድህነት እናንተ ባለጠጎች ትሆኑ ዘንድ እርሱ ሀብታም ሆኖ ሳለ ለእናንተ ሲል ድሃ ሆነ፤"*

2 ቆሮንቶስ 8፡9

**የክፍለ-ጊዜው መምሪያ**

**(ከለሳ 10-20 ደቂቃ)**

.....................................................................................

ሰዎች ያሉበትን ለማወቅ እና ለመበረታታት ጊዜ ውሰዱ፤ እርስ በርስ ታሪክ በመከፋፈል፣ ስለተገኙ ዕድሎች ያላችሁን ሃሳብ መከፋፈል እና ሌላ የትኛውንም ነገር በማንሣት እርስ በርስ ተነጋገሩ። ለትንንሽ ቡድን እያንዳንዱ የቡድን አባላት ካለፈው የቡድን ስብሰባ በኋላ ያጋጠማቸውን አንድ ድል እና አንድ የተቸገሩበትን ነገር እንዲያካፍሉ ዕድል ስጡ፤ ለትልቅ ቡድን አራት/አምስት የሚሆኑ የቡድን አባላት ከባለፈው ስብሰባ በኋላ ያላቸውን ምስክርነት እንዲያካፍሉ ዕድል ስጡ።

**ጸሎት**

.............................................................................................

ጊዜውን ለእግዚአብሔር በመስጠት እና በትውውቅ ጊዜ በተነሣ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ጉዳይ ላይ ጸልዩ።

**ትምህርት (25-35 ደቂቃ)**

.............................................................................................

ራሳችሁ ልታቀርቡበት በምትችሉበት መንገድ ወይም ቃል በቃል ይህንን ትምህርት ማቅረብ ትችላላችሁ።

*"ሌሎች ከእናንተ እንደሚሻሉ በትሕትና ቁጠሩ እንጂ፣ በራስ ወዳድነት ምኞት ወይም ከንቱ ውዳሴ ለማግኘት አንዳች አታድርጉ። ለእያንዳንዳችሁ ሌሎችን የሚጠቅመውን እንጂ ራሳችሁን የሚጠቅመውን ብቻ አትመልከቱ። በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረው ያ አስተሳሰብ በእናንተ ዘንድ ይሁን*

*እርሱ በባህርይው አምላክ ሆኖ ሳለ*

*ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን ሊለቀው እንደማይገባ አድርጎ አልቆጠረውም፤*

*ነገር ግን የባርያን መልክ ይዞ በሰው አምሳል ተገኝቶ ራሱን ባዶ አደረገ*

*ሰው ሆኖ ተገልጦም ራሱን ዝቅ አደረገ፤ ይኸውም መስቀል ላይ እስከመሞት ድረስ ታዛዥ ሆነ።"*

**ፊል. 2፡3-8**

በትሕትና ላይ ሲፅፉ ታዋቂው ሲ. ኤስ. ሉዊስ እንዲህ ብለው ነበር **"እውነተኛ ትሕትና ራሳችንን ዝቅ አድርጎ ማሰብ ሳይሆን ስለ ራሳችን ብዙ አለማሰብ ነው።"** መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ትሕትና ሲያወራ፣ ራስን ስለመጣልም ሆነ በራሳችን አለመተማመን ሳይሆን በእግዚአብሔር እንደተወደዱ እና የእርሱ ልጆች ለመሆን እንደተጠራን በዚህ መካከል የሚገባ ቦታ ላይ መቆም አለብን። ስለ ራሳችን ከሚገባው በላይ ማሰብ የሰውን ልጅ ወደ ውድቀት የመራው የትዕቢት ኃጢአት ውስጥ እንዲሁም የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት እና ንግሥና ወደ መካድ ያመራናል። ስለ ራሳችንም አሳንሰን ማሰብ እንዲሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የተከፈለልንን ዋጋ ያራክስብናል።

ትዕቢት የኃጢአት ማዕከል ነው። ምሳሌ መጽሐፍ 11፡2 ላይ ሲናገር፣ *"ትዕቢት ስትመጣ ውርደት ትከተላለች፤ በትሑት ዘንድ ግን ጥበብ ትገኛለች"* በማለት ያስተምረናል። በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ያሉት የጥበብ መጻሕፍት በሙሉ ትሕትናን የሚፈለግ ባህርይ እንደ ሆነ እና ከትዕቢት በተቃራኒ እያስቀመጡት ከውስጡ የሚፈሰውን በረከት ያሞግሳሉ።

የምንኖርበት ዘመን አፍቅሮተ-ራስ የነገሠበት ዘመን ነው። ዳዊት በዚህ ዘመን እየኖረ ጎልያድን ገድሎት ቢሆን ኖሮ ምናልባትም ከሰውነቱ ገና እንደተለየ የጎልያድን ጭንቅላት ይዞ ፎቶ የመነሣት ፍላጎት ይኖረው ይሆን? ብዙዎቻችን ስለ ሠራናቸው ሥራዎች እና ስላገኘናቸው ድሎች ቅኔ ቢዘረፍልን፣ መጽሐፍት ቢፃፉልንም ሆነ ፊልሞች ቢሠሩ ያስደስተናል። ነገር ግን፣ ዲ. ኤል. ሙዲ የተባለ ሰው ስለ ዳዊት በጻፈው መጽሐፍ ላይ **ዳዊት በመዝሙሮቹ ላይ አንድም ጊዜ ስለ ድሉ እንዳልጻፈ ያስተምረናል።** ዛሬ በምናገኘው ትንሽ ስኬት ላይ ራሳችንን እና ስማችንን አንድንሰብክ እንመክራለን፤ እግዚአብሔር ግን ራሳችንን እንድናወድስም ሆነ እንድናገለግል አልጠራንም። ነገር ግን ስለ ባህርያችን እና በትሕትና ውስጥ ለጠራን አገልግሎት ምን ያህል መሥራት እንደምንችል ነው ማየት የሚፈልገው (ሉቃስ 14፡11)።

ኢየሱስ ዝቅ ያለውን መንገድ ነበር የወሰደው፤ የባርያን መልክ ያዘ። ሊያገለግል እንጂ ሊገለገል የመጣ ንጉሥ አልነበረም (ማር. 10፡45)። ዮሐንስ በወንጌሉ ላይ ኢየሱስ የደቀመዛሙርቱን እግር ከማጠቡ በፊት ስለ እርሱ የጻፈውን ተመልከቱ፦

***"ኢየሱስም አብ ሁሉን ነገር ከስልጣኑ ስር እንዳደረገለት** ከእግዚአብሔርም እንደ ተላከ ወደ እግዚአብሔርም እንደሚመለስ **አውቆ**፤ ከእራት ተነሣ፣ መጎናጸፊያውን አስቀመጠ፣ ወገቡንም በፎጣ ታጠቀ።"*

(ዮሐንስ 13፡3-4፣ ማድመቂያው በደራሲው የተጨመረ ነው)

ሁሉም በስልጣኑ ውስጥ እንደ ሆነ እና ማንነቱን ያውቅ ስለ ነበረ፣ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈፀም ባርያ ለመሆን መረጠ። ይህንን ክፍል እግር ማጠብ ባለበት ልምምድ ውስጥ አጥንታችሁት ሊሆን ይችላል። ነገር ግን በዚያን ጊዜ ደቀመዛሙርቱ መምህራቸው እና መሲሃቸው እግራቸውን ሲያጥባቸው ያለውን ያህል የተግባሩ አስፈላጊነት ዛሬ እኛ ላይሰማን ይችላል። እንዲህ ብላችሁ አስቡት፣ በሃገራችሁ ያለ ንጉሥ ወይም ገዥ ቤታችሁን አንኳኩቶ በመግባት የትንሽ ልጃችሁን የቆሸሸ እና የሞላ የሽንት ጨርቅ/ዳይፐር ቢቀይር፣ ይህ ሽታ ያለው እና የሚያስቀይም፣ ግን አስፈላጊ የሆነን ሥራ ንጉሣችሁ በደስታ ከልጃችሁ ጋር እየተጫወተ ቢሠራ እንደማለት ነው።

አስተውሉ፣ ኢየሱስ እያጠበ ያለው የደቀ መዛሙርቱን እግር ነው። ይሁዳ አሳልፎ እንደሚሰጠው፣ ጴጥሮስ እንደሚከዳው፣ ደቀመዛሙርቱ ደካሞች እና ኩራተኞች እንደ ሆኑ አያወቀ፣ ከነክብሩ እና ግርማው እግራቸውን አጥቦ ሊከተሉት የሚገባቸውን ምሳሌ ጥሎላቸው አለፈ። አንዳቸው የሌላቸውን እግር እንዲያጥቡ ብቻ ሳይሆን በሁሉም ነገር እርስ በርሳቸው በትሕትና እንዲመላለሱ ነበር። **ስለ ቻርልስ ስፐርጀን የሚታወቅ አንድ ታሪክ አለ - ከስብከት ተማሪዎቹ መካከል አንዱ ለስብከት ወደ ምስባኩ በኩራት እየተጀነነ ወጥቶ፣ ጥሩ ባልነበረ ስብከቱ አፍሮ ሲወርድ መምህሩ "በወረድክበት መንገድ ብትወጣ ኖሮ፤ በወጣህበት መንገድ ትወርድ ነበር" ብሎ አስተማረው።**

መጠራታችን ምንም ያህል ትልቅ ቢሆን፣ የተሰጠን የጸጋ ስጦታ አስገራሚነት፣ የዕድሎቻችን ስፋት እና የአገልግሎታችን ግዝፈት አንድም ሰው ለማዳን ኃይል የለንም ነበር (ሮሜ 6፡23)። ነገር ግን የትሕትና ዋጋው ሕይወት ነው (ምሳሌ 22፡4)። ሞታችንን በመስቀል ሞት በወሰደልን ትሑት ባርያ ምክንያት ሕይወትን አግኝተናል። እኛም ትዕቢተኛ ለሆነው አመፀኛ ማንነታችን በትሕትና እየሞትን ዕለት ዕለት መስቀሉን በመሸከም፣ በክርስቶስ በመታመን ያገኘነውን ሕይወት ልንኖረው ይገባናል። ከሞት ወደ ሕይወት ተሻግረናል። በመሆኑም በዚህ ሕይወት ውስጥ የክርስቶስን ጌትነት የምንመክትበት ትክክለኛው ምላሽ ትሕትናን መልበስ ነው።

*"እግዚአብሔር በሕዝቡ ደስ ይለዋልና፤ የዋሐንንም በማዳኑ ውበት ያጎናጽፋል፤"* መዝሙር 149፡4

በወንጌል ስብከት ውስጥ ትሕትና ማለት ሰዎች መስማት የሚፈልጉትን ብቻ መናገር፣ ወንጌልን መሸቀጥም ሆነ ሰዎችን የሚያሳዝኑ ከመሰሉን ነገሮች መሸሽ አይደለም (በነገራችን ላይ፣ ወንጌል ሰዎችን የሚያበሳጫቸው ነገር ነው)፤ እንዲሁም፣ በወንጌል ያለን ድፍረት ማለት ወንጌል የሰዎችን ሁኔታ ሳንመለከት የሚሰጠውንም ተሰፋ በሚገባ ሳናስረዳ መናገር ማለት አይደለም። ወንጌልን በመስበክ ውስጥ ያለው ትሕትና ቢያንስ የሚከተሉትን አራት ሃሳቦች ይይዛል፦

ጥያቄ - የሚከተሉትን አራት መርኾች ከተመለከታችሁ በኋላ በወንጌል ሥርጭት ውስጥ እንዴት መተግበር እንደሚችሉ ተወያዩ።

በትሕትና እግዚአብሔርን ማገልገል - ምንም ያህል አስቸጋሪ፣ የማይመችም ሆነ ዋጋ የሚያስከፍል ቢሆንም፣ የመጀመሪያው ሃላፊነታችን እግዚአብሔርን ማገልገል ነው። የባርያን ማንነት ለመያዝ እና በመታዘዝ ጌታችንን ለማገልገል ፈቃደኞች ነን?

በትሕትና ራስን ማዋረድ - ትሕትና ራሳችንን ባዶ በማድረግ፣ በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት ቦታ መስጠትን ያካትታል። ይህ በራሱ ትሕትና ነው፤ መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን እንዲሞላን ስንፈቅድ ራሳችንን ለትሕትና እየሰጠን ብቻ ሳይሆን ለትሕትና እየታጠቅን ነው።

በትሕትና ቃሉን መቀበል - በእግዚአብሔር ቃል ፊት ራሳችንን ማዋረድ አለብን፤ ሊለን የፈለገውን በሚገባ አንብበን መረዳት እና መቀበል አለብን እንጂ ለፍላጎቶቻችን ማሚያ አድርገን መጠቀም የለብንም። የእግዚአብሔር ቃል ከምናስበውም ሆነ ባህላችን ከሚለው የተለየ ሃሳብ ቢኖረውም፣ ልንቀበለው ይገባል። የእግዚአብሔርን እውነት ማወቅ እና ጥበቡን በሕይወት መተግበር ትሕትናን ይሻል።

ወንጌል የምንሰብክላቸውን በትሕትና ማገልገል - ትሕትናንም ማወጅ አስፈላጊ ነው። ነገር ግን ወንጌልን የምንነግራቸውን ሰዎች መውደድ አለብን - ሰዎች ስንወዳቸው ደግሞ ልንሰማቸው ይገባል። ብቻችንን የምናወራ እና የማናዳምጥ ከሆነ ሰዎችን ከወንጌል ጋር የምናገናኝበትን ቦታ ልናጣው እንችላለን፤ ደግሞም፣ ትርጉም ያለው ግንኙነትን መመሥረት አንችልም።

እግዚኣብሔርን በመፍራት፣ መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን እንዲሠራ በመፍቀድ እና በቃሉ እውነት ላይ ተመሥርተን በዓለም ያሉ ሰዎችን ችግር በሚገባ በማድመጥ እና መፍትሔ እየፈለግን፣ ሰዎች ወደ ክርስቶስ ኢየሱስ የምንጠራ ውጤታማ አገልጋዮች መሆን እንችላለን። በወንጌል ሰባኪነት ስኬታማ መሆን ከፈለግን፣ ትሕትና ዋና ነገር ነው። ይህንንም ዲ. ኤል. ሙዲ እንዲህ አስቀምጠውታል፦

*“በግቢዬ ውስጥ የለውዝ ዛፍ አለኝ። በግቢዬ ውስጥ ካሉት ዛፎች ሁሉ እጅግ የሚያምረው ዛፍ ያ ነው። ይህ ዛፍ እጅግ የሚያምር፣ ቅጠሎቹ የተንዠረገጉ እና ቅርጫፎቹ በሚገባ ብርሃን ለማግኘት ያህል የረዘሙ ናቸው። ነገር ግን ከዚህ ዛፍ አንድም ቀን ፍሬውን አግኝቼበት አላውቅም። በባለፈው አመት ሙሉ ፍሬ የሰጠኝ ሌላ ዛፍ አለ። ይህ ዛፍ ቅርንጫፎቹ መሬት ለመንካት የደረሱ ናቸው። ዝቅ ባልን ቁጥር ወገኖቼ እግዚአብሔር እያንዳንዳችንን ለሥራው ይፈልገናል።”*

*ዲ. ኤል. ሙዲ*

**ውይይት** (15 **ደቂቃ**)

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች/ሃሳቦች ተወያዩባቸው**

- ትሕትና በማጣት የምንቸገርበት የሕይወት ክፍሎች አሉን?
- ወንጌልን በድፍረት በመስበክ እና በትሕትና በመስበክ መካከል የሚጋጭ ሃሳብ ያለ ይመስላችኋል?
- በሌሎች ውስጥ የምንመለከተውን ትሕትና ማጣትም ሆነ ውሸት ስላለበት ትሕትናን እንዴት በፍቅር መነጋገር እንችላለን?

*“በክርስቶስ ትምህርት ቤት ውስጥ ትልቁ የምንደርስበት መዳረሻ ጌታችን እንደ ሆነው ልክ ብሩህ የፍቅር እና የትሕትና ሕይወት እንዲኖረን እንደ ሆነ ተረድቻለሁ”*

*ጆን ኒውተን*

**ትግበራ** (5 **ደቂቃ**)

በዙሪያችሁ ያሉትን ሰዎች ባልጠበቁት አዲስ እና የራሳችሁ በሆነ ሁኔታ ልታገለግሉ እና ልትባርኩ የምትችሉበትን መንገድ ፈልጉ። ቤተ ክርስቲያናችሁ የጽዳት ሠራተኛ ካላት፣ ሠራተኛዋን ከቤተሰብ ጋር ወይም በምሽግ ጊዜ እንድታሳልፍ ቀን መስጠት። በቢሮ ውስጥ ሻይ ወይም ቡና መጀመሪያ ገብታችሁ ለሌሎች አፍሉ ወይም ላስተናጋጅ እግዚአብሔር እንደሚወድዳቸው ከሚናገር መልዕክት ጋር ጠቀም ያለ ጉርሻ በመስጠት ሊሆን ይችላል።

በአንድ መንገድ ይህ ኢየሱስ ክርስቶስ የደቀመዛሙርቱን እግር ከማጠብ ጋር አይስተካከልም፤ በሌላ መንገድ ደግሞ ያልታሰበበት እና ድንገተኛ የሆነ የመልካምነት ሥራ መሆን የለበትም። እነዚህ የታሰበባቸው የአፍቃሪ እና ትሑታን የሆኑ ሌሎችን ለመባረክ የተዘጋጁ ሰዎች ተግባሮች ናቸው። እነዚህ ሰዎች የሌሎችን ይሁንታም ሆነ ከእግዚአብሔር ሞገስን ለማግኘት ሳይሆን፣ ትሕትናን ለመማር እና በውስጣችን እያደገ ላለው ትሕትና ተፈጥሮዓዊ ውጤቶች ናቸው።

**ጸሎት**

በክርስቶስ ውስጥ ላለነው ትሕትና እና በባርያ መልክ ስላሳየን ምሳሌነት አመስግኑት። እግዚአብሔር እርሱ እንደሚያያችሁ ራሳችሁን ማየት እንድትችሉ እየፀለያችሁ በትሕትና እና በጥበብ ዕለት ዕለት ማደግ እንድትችሉ ለምኑ። እርስ በርሳችሁም ወንጌልን ባነገበ ትሑት ልብ መስበክ እንድትችሉ ጸልዩ።

**ተጠያቂነት** (15 **ደቂቃ**)

የተጠያቂነት ቅጽ በመሙላት ለአጋራችሁ እና ለአነስተኛ ቡድናችሁ አጋሩት እንዲሁም አንዳችሁ ለሌላችሁ ጸልዩ።

ማስታወሻ

**ክፍለ-ጊዜ ዘጠኝ**

**የወንጌላዊው ዕድል**

**የወንጌላዊው አንድ ትልቅ ስጦታ ወንጌልን ለመስበክ በዙሪያው ያለውን ዕድልን መለየት፣ መመልከት፣ እና መጠቀም ነው።**

**በዚህ ክፍለ-ጊዜ ላይ የምናገኘውን ዕድል ሁሉ እንዴት መጠቀም እንዳለብን እንመለከታለን።**

**ክፍለ-ጊዜው በአንድ ዐረፍተ-ነገር**

**..................................................................................**

ወንጌላውንያን ለወንጌል የሚያገኙትን ዕድል ሁሉ በሚገባ መጠቀም አለባቸው። በእያንዳንዱ ቦታ እና ሁኔታ ውስጥ ወንጌልን በግልፅ እና በሚገባ ማስረዳት አለባቸው።

**የክፍለ-ጊዜው ዳራ**

**..................................................................................**

ሐዋርያው ጴጥሮስ ስላለን ተሰፋ ለሚጠይቀን ሁሉ ለመመለስ የተዘጋጀን እንድንሆን ያስተምረናል (1 ጴጥ. 3፡15)። ሐዋርያው ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ እንደሚነግረው፣ በጊዜውም አለጊዜውም ወንጌልን ለመስበክ የተዘጋጀ መሆን እንዳለበት ያስጠነቅቀዋል (2 ጢሞ. 4፡2)። በሌላ ክፍል ላይ ደግሞ፣ ሐዋርያው የምናገኘውን ዕድል ሁሉ በሚገባ መጠቀም እንዳለብን ያስተምራል (ቆላ. 4፡5)። ኢየሱስ ክርስቶሰስ ሌሎችን ለማገልገል እና ለማካፈል ሁሉን ዕድል እንደተጠቀመ ሕይወቱ ያሳያል። በመሆኑም የማንጠብቀው ቦታ ላይ ዕድልን መፈለግ አለብን - ልክ በሉቃስ 19፡1-10 በዘካርያስ፣ ወይም በማኅበራዊ የሕይወት ችግር ላይ በዮሐ. 4፡1-26 ላይ እንደ ሳምራዊቷ ሴት ወይም በሉቃስ 7፡36-50 ላይ በፈሪሳዊው ቤት እንደነበረችው ኃጢአተኛ ሴት በክብር ቦታዎች ላይ፣ በሉቃስ 17፡11-19 ላይ እንደተፈወሱት ለምጻሞች ከማኅበረሰብ በተገለሉ ሰዎች መሃልም ሆነ እንደ ኢየሱስ በሉቃስ 23፡ 39-43 ላይ በመስቀል ስቃይ ላይ ሆኖ በመከራው ውስጥ እውነትን እንደተናገረው ኢየሱስ እንዳደረጉት ማለት ነው።

ቢሊ ግራሃም ከማንም ሰው በላይ ለብዙዎች ወንጌልን በሰበኩባቸው የክሩሴዶቻቸውና የወንጌል መስበኪያ መንገዶቻቸው ይታወቃሉ። ነገር ግን ከሀገራት መሪዎች ጋር በነበራቸው ስብሰባም ሆነ፣ በቴሌቪዥን መርሃግብሮች ላይ ሲቀርቡም ሆነ ችግር ባለባቸው ቦታዎች ላይ እርዳታ ሲያቀርቡ፣ በግዳጅ ላይ ላሉ ወታደሮች እንዲሁም በተለያዩ መንገዶች ላገኟቸው ግለሰቦች ቢሊግርሃም ወንጌልን ለመስበክ የተዘጋጁ እና ፈቃደኛ ነበሩ። ቢሊ ግራሃም ለመጽሐፍ ቅዱስ ታዛዥ ወይም የታላቁን ተልዕኮ ትዕዛዝ በአገልግሎት ዕቅድ መሠረት በማድረግ ብቻ ዝም ብለው የተከተሉ ሰው ብቻ አልነበሩም። ነገር ግን፣ የአገኙትን ወንጌል የመስበክ ዕድል ሁሉ የተጠቀሙት ወንጌልን በሚገባ እና በእውነት ገብቷቸው፣ ተቀብለው እና ተሰጥተውለት ስለነበረ ነው።

ወንጌላዊው ወንጌልን ከመስበክ መድረክ ባለፈ፣ ለጠፉ ሰዎች ሰማያዊ የሆነ ሃዘኔታ አለው። ወንጌላዊ ሰዎች ወንጌልን እንዲሰሙ ጥልቅ ፍላጎት ያለው ሲሆን፣ መስበኩ ችግር የሚያስከትልበት ቢሆንም እንኳን ስለ ኢየሱስ ባገኘው ዕድል ሁሉ ከመናገር ወደ ኋላ አይልም (ሐዋ. ሥራ 4፡18-20)።

ሃክሶው ሪጅ በሚል ፊልም ላየ የተነገረው አስደናቂው የዴስመንድ ደስን ታሪክ በእግዚአብሔር ላይ ካው ጥልቅ እምነት የተነሣ በሁለተኛው ዓለም ጦርነት ላይ ለህክምና ሙያ በጦር ሠራዊትነት ውስጥ የነበረውን፣ ነገር ግን ምንም አይነት የጦር መሣሪያ በጃፓኖች ላይ ያላነሣበትን ታሪክ ያወሳል። ደስ በጠላት ሰፈር ከባድ ውጊያ በነበረበት በጃፓን ኦኪናዋ የተባለ ደሴት ላይ ከከባድ ጥቃት አገኘው፤ ነገር ግን ከአሜሪካ እና ጃፓን መንደር የተጎዱ ሰዎች ጩኸት ምላሽ በመስጠት ከሁለቱም ወገን የሆኑ ሰዎችን ከፍ ካለ ጋራ ላይ በገመድ ማውረድ ጀመረ። ደስ በአልሞ ተኳሽ እጁን ተመትቶ፣ እንዲሁም ዐሥራ ሰባት የጦር መሣሪያ ፍንጣሪዎች በሰውነቱ ውስጥ ቢገኙም፣ የሚችለውን ያህል የተጎዱ ሰዎቸን አትርፎአል። ስለ ነበረው ሁኔታ በኋላ ላይ ተጠይቆ ሲመልስ፣ "ዐቅም አጥቼ ድካም ሲወረኝ እግዚአብሔርን አንድ ሰው ማትረፍ እንድችል እለምነው ነበር" በማለት ተናገረ። ደስ 75 ሰዎችን ከጋራው ላይ በማውረድ አትርፎአል።

የደስን ጸሎት መመልከት እንችላለን "ጌታ ሆይ በየትኛውም አስቸጋሪም ሆነ ውድ ዕድል ውስጥ አንድ ተጨማሪ ሰው ስጠኝ።"

**የክፍለ-ጊዜው መምሪያ**

**(ክለሳ 10-20 ደቂቃ)**

..............................................................................

ሰዎች ያሉበትን ለማወቅ እና ለመበረታታት ጊዜ ውሰዱ፤ እርስ በርስ ታሪክ በመከፋፈል፣ ስለ ተገኙ ዕድሎች ያላችሁን ሃሳብ መከፋፈል እና ሌላ የትኛውንም ነገር በማንሣት እርስ በርስ ተነጋገሩ። ለአነስተኛ ቡድን እያንዳንዱ የቡድን አባላት ካለፈው የቡድን ስብሰባ በኋላ ያጋጠማቸውን አንድ ድል እና አንድ የተቸገሩበትን ነገር እንዲያካፍሉ ዕድል ስጡ። ለትልቅ ቡድን አራት/አምስት የሚሆኑ የቡድን አባላት ከባለፈው ስብበሳ በኋላ ያላቸውን ምስክርነት እንዲያካፍሉ ዕድል ስጡ።

**ጸሎት**

..............................................................................

ጊዜውን ለእግዚአብሔር በመስጠት እና በትውውቅ ጊዜ በተነሣ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ጉዳይ ላይ ጸልዩ።

**ትምህርት (25-35 ደቂቃ)**

..............................................................................

ራሳችሁ ልታቀርቡበት በምትችሉበት መንገድ ወይም ቃል በቃል ይህንን ትምህርት ማቅረብ ትችላላችሁ።

*"አንድ ቀን ጴጥሮስ እና ዮሐንስ በጸሎት ጊዜ፣ ይኸውም ከቀኑ በዘጠኝ ሰዓት፣ ወደ ቤተ መቅደስ ይወጡ ነበር። ወደ ቤተ መቅደስ ከሚገቡ ሰዎች ምጽዋት እንዲለምን፣ ሰዎች በየዕለቱ ተሸክመው "ውብ" በተባለው የቤት መቅደስ መግቢያ በር ላይ የሚያስቀምጡት አንድ ከተወለደ ጀምሮ ሽባ የሆነ ሰው ነበር። እርሱም ጴጥሮስ እና ዮሐንስ ወደ ቤተ መቅደስ ሲገቡ አይቶ ምጽዋት ለመናቸው። ጴጥሮስም ከዮሐንስ ጋር እርሱን ትኩር ብሎ አየውና "እስቲ ወደ እኛ ተመልከት" አለው። ሰውየውም ከእርሱ አንድ ነገር ለማግኘት አስቦ በትኩረት ተመለከታቸው። ጴጥሮስ ግን "እኔ ብር እና ወርቅ የለኝም ነገር ግን ያለኝን እሰጥሃለው በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሥተህ በእግርህ ተመላለስ" አለው።"* ወንጌላዊ ብርና ወርቅ የለኝም በማለት ማገልገል ማቆም የለበትም። በተጨማሪም፣ ለማገልገል የሚያስፈልገው የናዝሬቱ ኢየሱስ ከእኛ ጋር መሆኑ ነው እንጂ ገንዘብ አይደለም!

ሐዋርያት ሥራ 3፡1-6

ዕድሎች በቀላሉ ሊያመልጡን ይችላሉ። ሰዎች በሕይወታቸው ውስጥ ያለው ትልቅ ፀፀት የተሻለ በራስ መተማመን ቢኖራቸው፣ ወይም 'ሰው ምን ይለኛል' ብለው ሲጨነቁ የመጡ ዕድሎች ናቸው። የማኅበራዊ ሚድያ ዓለምን ወደ "ያመልጠኛል" በሚል እሳቤ ውስጥ ከቶናል፤ ሁሉም ሰው እርስ በርሱ ሁልጊዜ በተያያዘበት ዘመን ላይ ሌሎች ሰዎች ሁልጊዜ ምን እያደረጉ እንደሆነ ማወቅ በምንችልበት ሰዓት፣ የሌሎች ሰዎችን ሕይወት ስንመለከት እኛ ሕይወት ያመለጠን ይመስለናል። ምናልባትም "ያመልጠናል/አምልጦኛል" የሚለው እሳቤ ከግንኙነታችን አንዱ ጉዳት ነው። መጽሐፍ ቅዱስን ስናነብብ፣ በኢየሱስ እና በደቀ መዛሙርቱ ሕይወት የሚያጋጥማቸውን ተመልክተን "አመለጠን" በሚል ፍርሃት ተሞልተን እናውቅ ይሆን? የሐዋርያትን ሥራ ስናነብ፣ በእነርሱ ሕይወት እና አገልግሎት የተከሰቱት ነገሮችን ተመልከተን ቀንተን እና እንዳመለጡን ይሰማን ይሆናል። ብዙዎቻችን በድንጋይ መወገር ያለበትን መከራ ባንፈልገውም፤ ነገር ግን በዘመናቸው የነበረውን ድንቅ እና ተዓምራት ግን እንመለከት እና እንለማመድ ዘንድ ናፍቀን ይሆናል።

በሐዋርያት ሥራ 3 ውስጥ ጴጥሮስ እና ዮሐንስ ዕለታዊ የሆነ የሕይወት ምልልስ ላይ ራሳቸውን አገኙ። አንድ የአካል ጉዳተኛ የሆነ ለማኝ ገንዘብን ጠየቃቸው። ለሐዋርያቱ ትንሽ ገንዘብ ሰጥቶ ወይም ዝም ብሎ ማለፍ ቀላል ነበር። ክፍሉ የሚጠቀመውን ቃላት በሚገባ ተመልከቱት - እነርሱም ትኩር ብለው ሲመለከቱት፣ እርሱም ከእነርሱ የሆነን ነገር እንደሚቀበል በማመን በትኩረት ተመለከታቸው።

*ጥያቄ፦ በዙሪያችሁ ያለውን ዓለም ምን ያህል በትኩረት እየተለመከታችሁ ነው? በተለይም ከነባራዊው አገልግሎታችሁ ውጪ በሆነ መልኩ ወንጌልን የመስበክ ዕድል እንዳያመልጣችሁ በሚገባ ትመለከታችሁ?*

አካል ጉዳተኛ የነበረው ሰው ከምንም በላይ የሚስፈልገው ገንዘብ እንደ ሆነ በማመን ከእነርሱ ለማግኘት ተመለከታቸው። ነገር ግን፣ ሐዋርያቱ ከፊታቸው ያለውን ዕድል በሚገባ ተመልከተው ለእርሱ በእውነት የሚስፈልገውን ሰጡት - ኢየሱስን። ለጠፉ ሰዎች ያላቸው ፍቅር እንጂ፣ ለአንድ አካል ጉዳተኛ ለሆነ ሰው ከተሰማቸው ሀዘን ነው ሰውየውን አይተው እንዲቆሙ ያደረጋቸው።

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የሚያከብሩትን እንደሚያከብር ያስተምረናል (1 ሳሙኤል 2፡30)። ይህ በሕይወታችን ባሉ ትንንሽ ነገሮች ውስጥ እግዚአብሔርን ስናከብረው በሚገባ ይገለጣል። በትንንሽ እና በማይታዩ የሕይወት ቦታዎች ላይ እግዚአብሔርን ስናከብረው፣ እግዚአብሔር በትልልቁ ነገር ያከብረናል። ትልልቅ መድረኮች እና ጉባኤዎች ላይ እድል እናገኝ ይሆናል። ነገር ግን ከመንፈስ ቅዱስ ኃይል በሕይወታችን መገለጥ አይበልጡም። ለእግዚአብሔር በተገዛን ቁጥር፣ የእግዚአብሔር መንፈስ መገኘትን በሙላት መለማመድ እንችላለን። ነገር ግን እግዚአብሔር መንፈሱን በሙላት የሚያፈስሰው፣ ለሥራው በሚገባ ለሚጠቀሙት ሰዎች ነው። በእስራኤል ውስጥ ባለ በየትኛውም ሰው ተጠቅሞ እግዚአብሔር ጎልያድን ማሸነፍ ይችል ነበር። ነገር ግን፣ ዳዊት ለአገልግሎቱ የሚመጥን ሆኖ የተገኘ ሰው በመሆኑ የንግሥናው ጎዳና ለእርሱ ሆነ።

ትልቁን ልምምድ የምትናፍቁ ከሆነ፣ ለትንንሽ ነገሮች፣ ለዕለታዊ ዕድሎች እና እግዚአብሔር በእናንተ ሊሠራ ላለው ነገር የታመናችሁ ሁኑ። ዕድሎችን ለመጠቀም ስንፋችሁ ከሆነ፣ እግዚአብሔር ከምቾታችሁ እንዲያወጣችሁ እየፀለያችሁ በእያንዳንዱ ነገር አስባችሁ ለመሥራት ምረጡ። **ዕድሎችን ባለመከተላችሁ ጥፋተኝነት የሚሰማችሁ ከሆነ፣ እግዚአብሔር የሚጠብቅባችሁ ጥፋተኝነት እንዲሰማችሁ ሳይሆን፣ ለእርሱ ባላችሁ ፍቅር የሚመራ ለጠፉት የሚሆን ፍቅር እና መፈለግን ነው።** ሐዋርያቱ እንኳን ስህተትን የፈፀሙ እና ወንጌል የመስበክን ዕድል ያሳለፉ ነበሩ፣ ማንም ፍፁም አይደለም። ነጥቡ ልንደርስበት የማንችለው ቦታ ላይ ለመድረስ ራስን ማስጨነቅ ሳይሆን፣ ፀጋን በሚጨምር እና የሚወዳደረው በሌለው የእግዚአብሔር ፍቅር ላይ መታመን ነው ያለብን። በዚህ ውስጥ ማደግ እንችላለን። እንዲሁም በየዕለቱ እግዚአብሔር ወደ እኛ የሚያመጣቸውን ዕድሎች አብልጠን መጠቀም እንችላለን።

*ዲ. ኤል. ሙዲ አንድ ጊዜ ሲናገሩ "እግዚአብሔር ነፍስ-ኢድን ጀልባ ሰጥቶኝ - "የምትችለውን ሁሉ ኢድን" ብሎኛል፤* የመቅዘፍ እና የሚሰጥሙትን ሁሉ የማዳን ጥረታችን ለእግዚአብሔር እና ለሚጠፋው ዓለም ካለን ፍቅር የሚመነጭ ነው።"

በየቀኑ ወደ ሕይወታችን ለሚመጡ ዕድሎች ዐይናችን እንዲከፈት እና በታማኝነት መጠቀም እንድንችል የሚረዱ ሦስት ጥቆማዎች ቀጥሎ ተብራርተዋል፦

1. ማስታወሻ
   ማስታወሻ መጻፍ እጅግ ብዙ ጥቅም አለው። ስለ ዕድሎች እያሰብን ቀናችን እንዴት እንደነበር፣ ሥራ ቦታ ከማን ጋር እንዳሳለፍን፣ ወደቤታችን ባለው መንገድ ላይ በተደጋጋሚ የምንመከተው የጎዳና ተዳዳሪን፣ በትምህርት ቤት በረፍ ላይ የምታናግሩት ሰው፣ እነዚህን ሰዎች በማሰብ እንድንፀልይላቸው እና ለግል ተጠያቂነት ለማዳበር ይጠቅማል። በጊዜ ብዛት እምነት-ተኮር የሆነ ውይይት አላችሁ ወይ? በመካከላችሁ ያለው ንግግር ጉንጭ-አልፋ ከመሆን ወደ ጥልቅ ሃሳቦች መወያየት አድጓል ወይ? የተጠያቂነት ተጓዳኛችሁን፣ ማስታወሻችሁን እንዲያነቡ እና በእነዚህ ጉዳዮች ዙሪያ እንዲጠይቋችሁ ዕድል መስጠት ትችላላችሁ።
2. ራስን መፈተን/Challenge
   ዕለታዊ ዕድሎችን መጠቀም ካቃታችሁ፣ ለራሳችሁ ፈተና ማዘጋጀት ትችላላችሁ። ለምሳሌ፣ "በዚህ ሳምንት ለአንድ ለማላውቀው ሰው ስለ ኢየሱስ አወራዋለሁ፤" ሊሆን ይችላል። ፈተናው የማወጅ ወይም ተግባራዊ ሊሆን ይችላል ነገር ግን ከመደበኛው የወንጌል ስብከት መንገድህ/ሽ ሊያወጣ ይገባል።
3. አዲስ ነገርን መሞከር
   አዕምሮህን ከሥራ ወደ አዲስ ነገር ሙከራ አሸጋግር፤ የወንጌላዊነት ኃላፊነት አለብን። ይህን እግዚአብሔር የሚጠብቅብንን መፈፀም አለብን፤ ነገር ግን፣ ይህንን ኃላፊነት ከፍቅር ውጪ ተግባራዊ ማድረግ ያስቸግራል። በፊታችን ሳምንታት ያላችሁን ወንጌል የመስበክ ዕድል እንደ ሥራ ሳይሆን፣ አስገራሚ የሆነ የሕይወት ጀብድ እንደ ሆነ አስቡ። ብዙ ሰዎች፣ ሥራቸውን የሚወዱ ሰዎች እንኳን ቢሆኑ፣ ቅዳሜ እና እሑድን ይናፍቃሉ፤ እኛም ወንጌልን የመስበክ ዕድልን በዚያ አይነት መንገድ መናፈቅ የምንችል ይሆን? ከቻልን ይህንን ጉዞ በጤነኛ አመለካከት እና በሚገባ መቀበል እና ብንወድቅ እንኳን አቧራውን አራግፈን ተነሥተን መራመድ እንችላለን።

ማርቲን ሉተር እንደተናገረው

*“እምነት ካለው፣ አማኙ ራሱን አለመግዛት አይችልም። ራሱን ይከዳል፣ ይወጣል፤ ወንጌል ሕይወቱን በመስዋእትነት ቢያስከፍለው እንኳን ይሰብከዋል፣ ያስተምረዋል።”*

**ውይይት** (15 **ደቂቃ**)

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች/ሃሳቦች ተወያዩባቸው**

- ግልጽ የሆነ ወንጌል የመስበክ ዕድል አምልጧችሁ ያውቃል? ምን ልምድ ቀሰማችሁበት?
- ወንጌልን ለመስበክ ከሚያጋጥማችሁ ዕድል እንዳትጠቀሙ የሚደርጉ ችግሮች ምንድን ናቸው?
- ወንጌልን ለመስበክ ዕድሎች በሌሉበት ቦታ አስባችሁበት ዕድሎችን እንዴት መፍጠር ትችላላችሁ?
- ከላይ የተጠቀሱትን ሦስት ጥቆማዎችን (ማስታወሻ፣ ራስን መፈተንም ሆነ ጀብዱ) ዋጋቸውን እንዴት ታያላችሁ? ልትጠቀሙበት የምትችሉት እንዳለ ታምናላችሁ?

*“መርኸው ይህ ነው - የመለኪያ መሣሪያችሁን የምታገለግሏቸው ሰዎች የሚስፈልጋቸው ነገር ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት። ወንጌል አድማጮች ሊሰሙት በሚችሉበት መንገድ እና ሁናቴ ወደ እነርሱ መወሰድ አለበት።”*

ካትሪን ቡት

**ትግበራ** (5 **ደቂቃ**)

በዚህ ወር ውስጥ ከሌላው ጊዜ በተለየ ወንጌልን የምትሰብኩበት ዕድል እንዳያመልጣችሁ አስተውሉ። ልትደውሉለት/ ልታገኙት የምትችሉት የድሮ ጓደኛ ይኖር ይሆን? ምናልባት ቁጭ ብላችሁ ልታወሩት የምትችሉት የጎዳና ተዳዳሪ ወይም በየቀኑ ቡና የሚያቀብላችሁ አስተናጋጅ/ባሬስታ ጋር ጊዜን በመውሰድ ስለ ኢየሱስ የምታወሩበትን ዕድል ፍጠሩ።

በቡድን ውስጥ ያለው ሰው ሁሉ ወንጌልን አስቦበት ሊሰብክበት የሚችልበትን መንገድ ማሰብ ይኖርበታል። ይህንን ዕድል ተጠቅማችሁ አንዳችሁ ለአንዳችሁ እስከሚቀጥለው ወር ድረስ ተጠያቂ ሁኑ። አስተውሉ፣ ይህ ግብን አስቀምጠን ለማሳካት የምንሮጥበት ሳይሆን የሕይወት ልምምድን እና ባህርይን ለማዳበር የምንሠራበት መንገድ ነው። **ዛሬ አስበንበት የምንጀምረው ልምምድ ነገ ባህርያችን ወደ መሆን ያድጋል።**

ማስታወሻ መጻፍ ጀምሩ።

**ጸሎት**

እግዚአብሔር የማዳን መልዕክቱን ለሌሎች የምንናገርበት ዕድል ስለ ሰጠን አመስግኑት። በልባችሁ በሚከብዱባችሁ ሁናቴዎች እና በዕለታዊ ሕይወታችሁ ውስጥ እግዚአብሔር የመናገርን ዕድል እንዲሰጣችሁ ለምኑ። በዙሪያችሁ ለሚመጡ ዕድሎች አና ለእርስ በራሳችሁ ታማኞች እንድትሆኑ ጸልዩ።

**ተጠያቂነት** (15 **ደቂቃ**)

የተጠያቂነት ቅጽ በመሙላት ለአጋራችሁ እና ለአነስተኛ ቡድናችሁ አጋሩት እንዲሁም አንዳችሁ ለሌላችሁ ጸልዩ።

**ማስታወሻ**

**ክፍለ-ጊዜ *ዐሥር***

***የወንጌላዊው መሰጠት***

***መጽሐፍ ቅዱስ በክርስቶስ ኢየሱስ በማመናችን ከአመፃችን ተመልሰን፣ ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት እንድናደርግ***

***የሚጋብዘንን የጥሪ መገለጥ ይዟል። ወንጌል የሚለውን እያስረዳን ብቻ ሳይሆን፣ ሰዎች ምላሽ እንዲሰጡ በሚያስችል መልኩ***

***መናገራችንን እንዴት እናረጋግጣለን?***

**ክፍለ-ጊዜው በአንድ ዐረፍተ-ነገር**

**……………………………………………………………**

*ወንጌላዊ ወይንም መስካሪው የወንጌልን ሙሉ መልዕክት ለመናገር መሰጠት አለበት - ይህም ሰሚዎች መልዕክቱን ሰምተው በክርስቶስ ኢየሱስ ወዳለ መዳን በመምጣት መንገዳቸውን እንዲቀይሩ ነው።*

**የክፍለ-ጊዜው ዳራ**

**……………………………………………………………**

በሰርጉ ቀን ቤተ ክርስቲያኑ መድረክ ላይ ቆሞ የሚጠብቀው ሙሽራን አስቡ። ምርጡን ልብስ ለብሶ፣ የተጌጠውን ቤተ ክርስቲያንን፣ አምረው እና አጊጠው ለብሰው የመጡትን ቤተሰቡን እና ጓደኞቹን ይመለከታል። ከሁሉም በላይ ግን የሚጠብቀው የሚወዳትን ሙሽራውን ነው። ሙሽሪትን ሲጠብቅ ዐሥር ደቂቃ አለፈ፤ ሃያ ደቂቃ . . . 'ሙሽራ ማርፈድ ልምዱ ነው' በሚል መጠበቁን ቀጠለ። አርባ አምስተኛው ደቂቃ ላይ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተሰበሰውን ሰው ማጉረምረም እየሰማ በፈገግታ ውስጥ ጭንቀት ይሰማው ጀመረ። አንድ ሰዓት ሲሞላው ግን ውስጡ የበለጠ መጨነቅ ጀመረ፤ ማርፈድ ብቻ ሳይሆን ምናልባት የማይታሰበውን አድርጋ ይሆን፤ ቀርታ ይሆን? ብሎ ማሰብ ጀምረ። ሙሽራው ለምን ሙሽሪት እንደቀረች፣ ምን ምክንያት ሊኖራት እንደሚችልም ማሰብ ጀመረ። ምክንያቶችን ሲያወጣ እና ሲያወርድ ድንገት ልቡ ስንጥቅ ብሎ ያለመምጣትዋ ምክንያት ተገለጠለት - ሙሽራውን እንድታገባው አልጠየቃትም። ግብዣ ሰዎችን ለምታቀርቡላቸው ዕድል ምላሽ እንዲሰጡ አስፈላጊ ነው። የኢየሱስ ወንጌል በማርቆስ ወንጌል ላይ እንደሚከተለው በአጭሩ ተጽፏል፣ "ጊዜው ደርሷል፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለች፣ ንስሃ ግቡ፤ በወንጌልም እመኑ እያለ ይሰብክ ነበር" (ማር. 1፡15)።

'ንስሃ ግቡ' የሚለው ሃሳብ ትንሽ ችግር ሊያስከትል ይችላል። ዋናው ምክንያት ብዙ ሰዎች ምን ማለት እንደ ሆነ ስለማያውቁ ነው። ብዙ ሰዎች ከወንጌል ስብከት ጋር አብረው የሚሰሙት የፍርድ መልዕክት ስላለበት "ተመለስ ወይም ተቃጠል" በሚል ነው። ተመለሱ/ንስሃ ግቡ የሚለው ሃሳብ ዛሬ ላይ ያሉ ብዙ ሰዎች ከ "መልካም ዜና" ጋር አያያይዙትም። ነገር ግን፣ ንስሃ መግባትን በሚገባ ስንረዳው፣ በወንጌል እውነት ውስጥ አስደናቂ መገለጥ ነው። ንስሃ መግባት አስተሳሰብን እና የሕይወትን አቅጣጫ መቀየር ነው። የኢየሱስ መልዕክት "በተሳሳተ መንገድ እየሄዳችሁ ነው፤ ወደ ትክክለኛው መንገድ - ወደ አባታችሁ ወደሚወስዳችሁ ወደ እውነተኛ መንገድ ልመልሳችሁ ነው የመጣሁት" የሚል ነው። ንስሃ መግባት እውነተኛ መልካም ዜና ነው። ምክንያቱም ሰዎች ከሞት ወደ ሕይወት የሚመጡበት ዕድል ነው። በአመፃችን ምክንያት ከእግዚአብሔር ተለይተናል፤ ንስሃ መግባት ለዚህ አመጽ የሚገለጠውን የእግዚአብሔርን ቁጣ የሚያስታውሰን እና በክርስቶስ ኢየሱስ ያለውን ተስፋ እንዲያገኙ ነው።

በዋልተር ኤ. ኤልዌል እና ቤሪ ጄ. ቢትዜል መሠረት ንስሃ መግባት ሦስት ዋና ክፍሎች አሉት፡-

*"የመጀመሪያው ከሆነ ነገር መመለስ ነው - ከኃጢአት፣ ከሃሰተኛ አማልክት ወይም ለራሳችን ብቻ ከኖርነው ሕይወት መመለስ ሊሆን ይችላል (1 ተሰሎንቄ 1፡9፣ ራዕይ 9፡20፣21 እና 16፡11)፤ ሁለተኛ ንስሃ የእግዚአብሔር ፈቃድ እና የእርሱ ፀጋ ሥራ ውጤት ነው (ሐዋርያት ሥራ 11፡18፣ ሮሜ 2፡4፣ 2 ቆሮንቶስ 7፡10፣ 2 ጢሞቴዎስ 2፡25 እና 2 ጴጥሮስ 3፡9) ፤ ሦስተኛ ወደ አንድ ማንነት መመለስ፤ ሙሉ ሕይወትን በክርስቶስ ኢየሱስ ለእግዚአብሔር መስጠት ነው (ሐዋርያት ሥራ*

*14፡15፣ 1 ተሰሎንቄ 1፡9፣ 1 ጴጥ. 2፡25)። ንስሃ ሙሉ በሙሉ የሆነ የአቅጣጫ ለውጥ ነው፤ ትልቅም ሆነ ትንሽ፣ ድንገተኛም ሆነ ጊዜ የሚወስድ፣ ስሜታዊም ሆነ የተረጋጋ ታማኝነታችንን በሙሉ ለእግዚአብሔር የምናደርግበት መንገድ ነው። "*

የወንጌል የመጀመሪያ ሰባኪዎች ወንጌልን የሚሰብኩላቸው ሰዎች ምላሽን እንዲሰጡ ልክ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ዕድልን ሲሰጡ መመልከት እንችላለን። የክርስቶስ ታሪክ መሃል/ጫፍ ላይ ለንስሃ ዕድል ይሰጣሉ (ሐዋርያት ሥራ 2፡37-39፣ 3፡25-6፣ 4፡12፣5፡31፣ 10፡43)። ወንጌል ሰዎች ከእግዚአብሔር መሸሻቸውን እንዲያቆሙ እና በኢየሱስ ክርስቶስ እምነታችን እንድናደርግ እና ወደ እርሱ ፊታችንን እንድንመልስ እና አዕምሮአችን በማንነቱ ማወቅ፣ ሕይወታችን ደግሞ በመንፈሱ ኃይል እንዲቀየር ነው።

**የክፍለ-ጊዜው መምሪያ**

**(ክለሳ 10-20 ደቂቃ)**

..........................................................................................

ሰዎች ያሉበትን ለማወቅ እና ለመበረታታት ጊዜ ውሰዱ፤ እርስ በርስ ታሪክ በመከፋፈል፣ ስለተገኙት ዕድሎች ያላችሁን ሃሳብ መከፋፈል እና ሌላ የትኛውንም ነገር በማንሣት እርስ በርስ ተነጋገሩ። ያለፈውን ክፍለ-ጊዜ ትምህርት መሠረት በማድረግ በዚህ ወር ያጋጠማቸውን ተጨማሪ ዕድል እንዲያካፍሉ ዕድል ስጡ (የክፍለ-ጊዜ ዘጠኝ ትግበራ)

**ጸሎት**

..........................................................................................

ጊዜውን ለእግዚአብሔር በመስጠት እና በትውውቅ ጊዜ በተነሣ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ጉዳይ ላይ ጸልዩ።

**ትምህርት (25-35 ደቂቃ)**

..........................................................................................

ራሳችሁ ልታቀርቡበት በምትችሉበት መንገድ ወይም ቃል በቃል ይህንን ትምህርት ማቅረብ ትችላላችሁ። ባገኛችሁት አጋጣሚ ወንጌልን ሰብካችሁ ጌታን ላገኙ ሰዎች ጸልዩላቸው።

*"ሕዝቡ ይህን በሰሙ ጊዜ ልባቸው እጅግ ተነካ፤ ጴጥሮስንና ሌሎቹንም ሐዋርያት "ወንድሞች ሆይ ታድያ ምን እናድርግ?" አሏቸው። ጴጥሮስም እንዲህ አላቸው፣ "ንስሃ ግቡ ኃጢአታችሁም እንዲሠረይላችሁ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ትቀበላላችሁ። የተሰፋው ቃል ለእናንተ እና ለልጆቻችሁ እንዲሁም ጌታ አምላካችን ወደ ራሱ ለሚጠራቸው፤ በሩቅ ላሉትም ሁሉ ነውና።"*

*ሐዋርያት ሥራ* 2፡37-39

ለወንጌል መጋበዝ እንደ መስቀሉ ሁሉ ማዕከላዊ ነገር ነው። በጴንጤቆስጤ ቀን የመጣውን መንፈስ ቅዱስ በመለማድ፤ ጴጥሮስ ለተሰበሰበው ህዝብ ወንጌልን መስበክ ጀመረ። በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በሰበከው ስብከት የሰሙት ሰዎች ልባቸው ተነካ። የምናነብበው መልዕክት እዚህ ጋር ቢለወጥ ኖሮ፣ ሐዋርያው ጴጥሮስ ሰብኮላቸው የሰዎችን ልብ እንደተነካ "እናመሰግናለን፤ ሰላም እደሩ" በማለት ከወዳጆቹ ጋር ከስብከት በኋላ ጊዜን ሊያሳልፍ ቢለያቸው ኖሮ፣ መልዕክቱን ሰምቶ ምላሽ ሊሰጥ የተዘጋጀው ህዝብ ጥያቄውን እንደያዘ  እና እምነቱን በኢየሱስ ላይ ሳያደርግ ወደ ቀደመውም ኑሮ ይመለስ ነበር። ነገር ግን፣ በሚያስደስት ሁኔታ፣ የተፈጠረው ይህ አይደለም። ሰዎች ምላሽ እንዲሰጡ ጴጥሮስ በመጋበዝ - ሰምተው ለተረዱት መልዕክት እና በውስጣቸው ለተቀሰቀሰው መንፈስ ምላሽ እንዲሰጡ መልካም መንገድ ነበር። ሙሉ የወንጌል መልዕክት ንስሃ መግባት እና ለሰሙት መልዕክት በምን መንገድ ምላሽ መስጠት እንዳለባቸው ያስረዳል። ደቀ መዛሙርቱ ይህንን ሙሉ ወንጌል በሚገባ ሰብከውታል እኛም ይህንን ልናደርግ ይገባናል።

ስብከቶችን እና ትምህርቶችን በመደበኛነት ለምታዘጋጁ ሰዎች - አስፈላጊ የትግበራ መመርያ በስብከት ውስጥ ማዘጋጀት ምን ያህል አስፈላጊ እንደ ሆነ ታውቃላችሁ። ኢየሱስም ሆነ ደቀ መዛሙርት በትምህርታቸው ውስጥ ትግበራን አካተው ነበር። ኢየሱስ በማርቆስ ወንጌል ላይ ወንጌልን ያቀረበበት መንገድ - "የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለች እና ንስሃ ግቡ፤" የሚል

የትግበራ አካል ነበር። ይህ ማለት "በተሳሳተ መንገድ እየሄዳችሁ ነው፤ ብትመለሱ መታደስን ታገኛላችሁ" የሚል ነው። ኢየሱስ በወንጌል ላይ በተደጋጋሚ ሰዎችን ለንስሃ ይጋብዛል "ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ" ማቴ. 11፡28፣ "ኑ እና እዩ" ዮሐ. 1፡39፣ "ኑ፣ ተከተሉኝ" ማቴ. 4፡19፣ "ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣ እና ይጠጣ" ዮሐ. 7፡37፣ እና "ኑ እና ብሉ" ዮሐ. 21፡12። እነዚህ ጥሪዎች ድንገተኛ እና አላስፈላጊ አይደሉም። ነገር ግን ለዓለም፣ የክርስቶስን እውነተኛ ማንነት የሚያስረዱ ሆነው መልዕክቶችን የመቀበላችንም ሆነ የመካድ ውጤት አላቸው። **ግብዣ በተፈጥሮው ምላሽን ይፈልጋል።** ለመጋበዛችን መልስ ከመስጠት መቆጠብ እንደ ምላሽ ይቆጠራል፤ "አዎን" የሚለው ግብዣውን የመቀበል ምላሽ ብቻ ነው የሚያስፈልገው። ይኸውም በረከትን ያስከትላል።

ጥያቄ፡- ከመጽሐፍ ቅዱስ ለምሳሌነት የተወሰዱትን የሚከተሉትን ሦስት ግብዣዎችን ተመልከታችሁ ተወያዩባቸው።

የደቀ መዛሙርቱ መጠራት (ማር. 1፡17) - የኢየሱስ መጥራት ግላዊ ነው።

ለሀብታሙ ወጣት የመጣለት ጥሪ (ማቴ. 19፡16-22)- የኢየሱስ መጥራት ዋጋ ያስከፍላል።

ከሞት መጠራት (ዮሐ. 11፡43)- የኢየሱስ ጥሪ ኃያል ነው።

ለወንጌል ምላሽ እንዲሰጡ ለሰዎች የምናቀርበው ግብዣ የስብታችን ዋና አካል ነው። ወንጌልን በሚገባ እና በእውነት ለመስበክ ሰዎች ምላሽ እንዲሰጡ የምናቀርበው ግብዣ አስፈላጊ ነው። ይህ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፤ አንዳንድ ወንጌልን የምንሰብክባቸው ዕድሎች ከሌሎች በተሻለ ለወንጌል ምላሽ የሚሰጥባቸውን መንገዶች ይከፍታሉ። በየትኛውም ቦታም ሆነ ሁናቴ ውስጥ በመሆን ሰዎች በታማኝነት ለወንጌል ምላሽ እንዲሰጡ መጋበዝ እንችላለን? አንድ በአንድ በሆነ ስብከትም ሆነ ከመድረክ ላይ በሚደረግ ግብዣ ሰዎችን ወደ እሑድ የአምልኮ መርሃ ግብሮች ብቻ መጋበዝ የለብንም (በሚያስፈልግ ጊዜ ግን ማድረግ አለብን)። ነገር ግን ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መጋበዝ ነው ያለብን - በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይህንን የምናደርግበት መንገድ በግልጽ ባይቀመጥም ለመጀመር ግን የሚከተሉትን መርኾች ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይ መመልከት እንችላለን፡-

<u>ቀጥተኛ ጥያቄ መጠየቅ</u>

ጥያቄዎቻችሁ ቀጥተኛ እና አጭር ይሁኑ። ለምሳሌ፣ ኢየሱስ ማን እንደ ሆነ እና እርሱን መከተል ማለት ምን እንደ ሆነ ካስረዳችሁ በኋላ - ይህንን ቀላል ጥያቄ መጠየቅ ትችላላችሁ - "ዛሬ እምነትህ/ሽን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ በማድረግ ከእርሱ ጋር ግንኙነትን መጀመር ትፈልጋለህ/ያለሽ?"

አድማጮቻችሁን በሚገባ ለመድረስ በሚል ምሳሌ ወይም ታሪክ ተጠቅማችሁ ከሆነ፣ እርሱን ማዕከል በማድረግ ጀምሩ። ለምሳሌ ከጠፋው ልጅ ምሳሌ ላይ ተነሥታችሁ የምታወሩ ከሆነ፣ እንዲህ ብላችሁ መጠየቅ ትችላላችሁ "እግዚአብሔር ዛሬም ወደ ቤቱ ይጠራችኋል። የጠፋው ልጅ እንደተመለሰው ዛሬ ወደ አባትችሁ እቅፍ መመለስን ትፈልጋላችሁ?" በእንዲህ አይነት ጥያቄ አድማጫችሁ ለምትጋብዙት ሕይወት እሺታን እንደመለሰላችሁ እርግጠኛ መሆን ትችላላችሁ። ስለምላሻቸው የበለጠ ማስረዳት ትችላላችሁ ነገር ግን መጀመሪያ ጥያቄያችሁ ቀጥተኛ፣ ቀላል እና ካካፈላችሁች መልዕክት ጋር በግልጽ የተገናኘ መሆን አለበት።

<u>የሚያስፈልገውን ጊዜ ውሰዱ</u>

በጉባኤ መሃል ስትናገሩ፣ መንፈስ እንደመራችሁ መንፈስ ቅዱስ የሰዎችን ሕይወት እንዲነካ ጊዜ ስጡ። የሚወስደው ጊዜም ሆነ የሚሰማችሁ አለመመቸት አስፈላጊ አይደለም። ነገር ግን፣ ሰዎች የሰሙትን የሚያስተውሉበት እና እግዚአብሔር እንዲሠራ ጊዜን መስጠት አለባችሁ። አንድ ለአንድ በሆነ ምስክርነት ላይ የሰማው ሰው ምላሽ እንዲሰጥ ጊዜን መስጠት እና በሌላ ጊዜ ለማውራት መቃጠር ይጠቅማል።

<u>የምትጠብቁባቸውን ግልጽ አድርጉ</u>

የሚሰማው ሰው ለወንጌል መልዕክት ምላሹ እሺታ ከሆነ፣ ምን ይፈጠራል የሚለውን እንዲሁም ወዴት እንደተጋበዙ አስረዱ። ለምሳሌ- አብራችሁ እንደምትጸልዩ ንገሩአቸው፣ ምናልባትም መጽሐፍ ቅዱስ እና የንባብ እቅድ እንደምትሰጡአቸው እንዲሁም ከራሳችሁ ወይም ከሌላ ቤተ ክርስቲያን ወይም የደቀ-መዝሙር ክትትል ቡድን ጋር እንደምታያይዙአቸው ንገሩአቸው። ሕይወታቸው በአንድ ቀን እንደማይለወጥ፣ ነገር ግን በዕለታዊ ጥሞና ከኢየሱስ ጋር

በሚያሳልፉት ጊዜ ሕይወታቸው ቀስ በቀስ ኢየሱስ የሰጠው ተስፋ እንደሚጠራ አስረዱ። የሚቀጥለውን የሕይወት ልምምድ እና ለኢየሱስ ምላሽ የሰጠ ሰው ደቀ-መዝሙር መንፈሳዊ ሕይወት እውነታን አሳዩአቸው።

<u>ቅበላን እንደምታከብሩ፣ እንዲሁም እንቢታን በፀጋ ተቀበሉ</u>

ሰዎች የወንጌልን ግብዣችሁን የሚቀበሉ ከሆነ፣ በደስታ እና አክብሮት ተቀበሉ። በዚህ ለውጥ ደስተኛ ካልሆናችሁ፣ መጀመሪያም ወንጌልን ልትሰብኩበት የወጣችሁበትን መንፈስ መርምሩ። እንዲሁም አድማጫችሁ ወንጌልን ለመቀበል ካንገራገረም ሆነ ቀጥተኛ እንቢታን ከገለፀ በፀጋ እና ትሕትና ተቀበሉት። እግዚአብሔር ራሱን በሌላ ጊዜ ሊገልጥላቸው ከወደደ፣ በራሳቸው ጊዜ መቀበል እንደሚችሉ በሚገልፅ ክፍት የሆነ ግብዣ ተለዩአቸው። ይህን ከሆነ ሊገናኙት የሚችሉትን የራሳችሁን የሆነ የቤተ ክርስቲያንን አድራሻ ተውላቸው።

ሰዎቸ ለወንጌል ምላሽ የማይሰጡበት አንደኛው ምክንያት ምላሽ እንዲሰጡ ስለማይጠየቁ ሲሆን፣ ብዙ ወንጌላውያንም እንዲሁ ምላሽ አናገኝም ብለው ስለሚፈሩ ከወንጌል መልዕክት ጋር ሰዎች ጌታን እንዲቀበሉ አይጋብዙም። ሰዎቹን የማዳን ኃይል የእኛ አይደለም። ኢየሱስ ራሱ መልዕክቱን እየነገራቸው ሰዎች ትተውት ሄደው ነበር። ሰዎች ቢመልሱም ሆነ ባይመልሱ፣ መጠራታችን የወንጌልን መልዕክት ከግብዣው እንድንሰብክ ነው። የኢየሱስ ጥሪ እርሱን ስንከተለው ለራሳችን በመሞት ነው (ማቴ. 16፡24)። ይህም በወንጌል ሥራችን ውስጥ ምንም ያህል አድካሚ እና የሚሾፍብን ቢመስለንም፣ ለራሳችን መሞት ይገባናል ማለት ነው።

ኢየሱስ እና ደቀመዛሙርቱ ወንጌልን ሲሰብኩ ግብዣዎች አቅርበው ነበር። እኛም ይህንን ማድረግ ይገባናል። ምላሹ ምንም ቢሆን ምን፣ እኛ ግን የወንጌል ማዕከላዊ መልዕክት ለሆነው በክርስቶስ ኢየሱስ ላለው የመመለስ እና የመታዘዝ ጥሪ ታማኝ መሆን ይገባናል። የቀረውን እግዚአብሔር ይፈጽመዋል።

**ውይይት (15 ደቂቃ)**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች/ሃሳቦች ተወያዩባቸው**

- ለወንጌል ሰዎች ምላሽ እንዲሰጡ ሳንጠይቅ መልዕክቱን መናገር እውነተኛ የወንጌል ስብከት ነውን?
- ሰዎችን ለምላሽ በመጥራት ውስጥ የሚቀላችሁ እና የሚከብዳችሁ ምንድን ነው?
- ወንጌልን በምትሰብኩበት ጊዜ ሰዎችን ምላሽን እንዲሰጡ ስለመጋበዝ እና ማበረታታት ምን ተማራችሁ?

*"ወንጌል የእግዚአብሔር ጥሪ ነው፤ ወደ አዲስ ኑሮ እንዲቀላቀል አድማጩን በስብከት መጥራት ነው፤"*

ማይክል ግሪን

**ትግበራ (5 ደቂቃ)**

ወንጌልን በምትሰብኩበት ጊዜ ሁሉ ውስጥ ሰዎች ምላሽን መስጠት እንዲችሉ ግብዣን ማቅረብን በማስተዋል አካትቱ። ምናልባትም ይህንን የምታደርጉበትን መንገድ ያጣችሁ የመድረክ ሰባኪ ልትሆኑ ትችላላችሁ። በሚቀጥሉት ጊዜያት ማንም ምላሽ ባይሰጥም እንኳን፣ በመድረክ ላይ ሰዎች ወደ ጌታ እንዲመጡ ጋብዙ። እንዲሁም በግል ከሰዎች ጋር ስለ ወንጌል በማውራት ብርቱ ሆነህ፣ ነገር ግን ወደሚቀጥለው ርምጃ በምን መንገድ መጋበዝ እንዳለብህ አላወቅህ ይሆናል። በዚህ ወር በድፍረት ወጥተህ ወንጌል ተኮር ንግግር ካደረገው ሰው ክርስቶስን እንዲከተል ጋብዝ።

**ጸሎት**

ከእርሱ ጋር እንድንታረቅ የጋበዘንን እግዚአብሔርን አመስግኑ። እናንተም ወንጌልን በምትሰብኩበት ጊዜ ፍርድን ሳይሆን፣ ተስፋን እያሳያችሁ በግልጽ እና በድፍረት ሰዎችን ወደ መመለስ መጥራት የምትችሉበትን ድፍረት ለምኑ። እንዲሁም የምትጋብዟቸው ሰዎች የሚመልሱበት ልብ እንዲኖራቸው ጸልዩ።

**ተጠያቂነት (15 ደቂቃ)**

የተጠያቂነት ቅጽ በመሙላት ለአጋራችሁ እና ለአነስተኛ ቡድናችሁ አጋሩት እንዲሁም አንዳችሁ ለሌላችሁ ጸልዩ።

ማስታወሻ

**ክፍለ-ጊዜ ዐሥራ አንድ**

**የወንጌላዊው ተነሣሽነት**

**እንደ ወንጌላውያን ሥራችን ለጠፉት ወንጌልን መስበክ ብቻ ሳይሆን ቤተ ክርስቲያንን ወደ ወንጌል ሥራ ማነሣሣት ጭምርም ነው። በዚህ ክፍለ-ጊዜ ላይ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለወንጌል ሥራ ለእግዚአብሔር ታማኝ እንድትሆን ማነሣሣት ነው።**

**ክፍለ-ጊዜው በአንድ ዐረፍተ-ነገር**

................................................................................

ወንጌልን ከመስበክ ባሻገር ወንጌላውያን ቤተ ክርስቲያንን ውስጥ ያሉ ቅዱሳንን ለእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት ሥራ ለማበረታታት እና ለማስታጠቅ መሰጠት አለባቸው።

**የክፍለ-ጊዜው ዳራ**

................................................................................

በክፍለ-ጊዜ ሁለት ላይ በዚህ አድቫንስ ቡድን ውስጥ ስንማር፣ የወንጌላዊው ማንነት የሰማዩ አባታችን መልዕክተኛ ልጆች እንደሆንን ተመልክተናል። ይህንን በሃሳባችን ይዘን እንደ ወንጌላውያን ለዓለም ብቻ ሳይሆን ለቤተሰባችን እና ለቤተ ክርስቲያናችን ያለብን ኃላፊነት ምንድን ነው?

ማኅበራዊ ሚድያ ማደግ ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ አዲስ አይነት ታዋቂነት በዓለም ላይ አለ። ይህም “ተጽዕኖ ፈጣሪ” የሚባል ነው። እነዚህም ሰዎች በማኅበራዊ ሚድያ ላይ ብዙ ተከታዮች ያፈሩ ሲሆን፣ በዚህም ምክንያት በብዙ ሰዎች ላይ ተጽዕኖ ማምጣት የቻሉ ናቸው። ይህ አዲስ ሃሳብ አይደለም። ለዘመናት አርቲስቶች እና ስፖርተኞች የምንለብሰውን፣ የምንበላውን፣ የምንጠጣውንም ሆነ የምናሸተውን ሲነግሩን ቆይተዋል። እነዚህ አዲስ ታዋቂዎች ግን በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በሰዎች ላይ ተጽዕኖ ለማምጣት ብለው ብቻ ብለው የሚከተሏቸውን ሰዎች የሰበሰቡ ናቸው።

ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ መልዕክቱ ላይ ለዚህ ዓለም ተጽዕኖ እንዳንወሰድ፣ ነገር ግን ለመንፈስ ቅዱስ በመገዛት በአዕምሮዓችን እንድንለወጥ ያስተምረናል (ሮሜ 12፡2)። **እንደ እግዚአብሔር ቅዱስ ህዝብ እኛ የመጀመሪያ ተፅዕኖ አድራጊዎች ለመሆን ተጠርተናል።** ይህም ሕይወት፣ ነፃነት እና ተስፋ ያለበት መልዕክት ነው። በሰባተኛው ክፍለ-ጊዜ ላይ ጣዕም የሌለው ጨው ለምንም እንደማይጠቅም ተምረናል። የማኅበራዊ ሚድያ ተፅዕኖ ፈጣሪዎች ዐቅም የሚወሰነው በሚከተሏቸው ሰዎች ብዛት እና እነርሱ በሚናገሩት ነገር ጠቀሜታ ልክ ነው። እንደ  ቤተ ክርስቲያን መለየታችን እጅግ አስፈላጊ እና ካጣነው እጅግ ዋጋ የሚያስከፍለን ነው። የማኅበራዊ ሚድያ ተጽዕኖ ፈጣሪዎች ከተፅዕኖ መፍጠር ሲጎድሉ፣ ከዝናም ሆነ ከሥራቸው ይወጣሉ። ነገር ግን፣ ቤተ ክርስቲያን ከተፅዕኖ ፈጣሪነት ከጎደለች፣ ወንጌል በሰዎች ሕይወት ውስጥ ሲተገበር እና ሊረዱት በሚችሉበት መንገድ ወንጌልን ለዓለም የሚገልፅ አይኖርም።

ዓለም ወንጌልን እንዲቀበል ወንጌላውያን ታላቅ መሻት አላቸው። እንዲሁም ቤተ ክርስቲያን በወንጌል ዓለም ላይ ተፅዕኖ ለማምጣት እንድትነሣሣ ወንጌላውያን ማበረታታት አለባቸው። የክርስቶስ ኢየሱስ አምባሳደር ለሆነችው ለቤተ ክርስቲያን፣ ከወንጌል ውጪ ምንም ሌላ ምርጫ የላትም። ቤተ ክርስቲያን ይህንን በረሳች ወይም በተዘናጋች ቁጥር፣ ወንጌላውያን በፍቅር የወንጌል ሥርጭት እሳትን በሚገባ በመቆስቆስ የወንጌል ብርሃን የበለጠ ተፅዕኖ ሊያመጡ ይገባል።

**የክፍለ-ጊዜው መምሪያ**

**(ትውውቅ 20-30 ደቂቃ )**

...........................................................................................

ሰዎች ያሉበትን ለማወቅ እና ለመበረታታት ጊዜ ውሰዱ፤ እርስ በርስ ታሪክ በመከፋፈል፣ ስለተገኙ ዕድሎች ያላችሁን ሃሳብ መከፋፈል እና ሌላ የትኛውንም ነገር በማጋሣት እርስ በርስ ተነጋገሩ። በባለፈው ክፍለ-ጊዜ መሠረት ሰዎች ለወንጌል ምላሽ እንዲሰጡ የነበራችሁ ልምምድ ምን ይመስል እንደነበር ተወያዩ (ክፍለ-ጊዜ ዐሥር)።

**ጸሎት**

..............................................................................................

ጊዜውን ለእግዚአብሔር በመስጠት እና በትውውቅ ጊዜ በተነሣ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ጉዳይ ላይ ጸልዩ።

**ትምህርት (25-35 ደቂቃ)**

..............................................................................................

ራሳችሁ ልታቀርቡበት በምትችሉበት መንገድ ወይም ቃል በቃል ይህንን ትምህርት ማቅረብ ትችላላችሁ። ባገኛችሁች ወንጌልን ሰብካችሁ ጌታን ላገኙ ሰዎች ጸልዩላቸው።

*"አንዳንዶች ሐዋርያት፣ አንዳንዶቹ ነቢያት፣ አንዳንዶቹን ወንጌል ሰባኪዎች ሌሎች ደግሞ እረኞችና አስተማሪዎች ይሆኑ ዘንድ የሰጠው እርሱ ነው። ይኸውም የክርስቶስ አካል ይገነባ ዘንድ ቅዱሳንን ለአገልግሎት ሥራ ለማዘጋጀት ሲሆን፤ ይህም የሚሆነው ሁላችንም የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኘው አንድነት በመምጣት እና ሙሉ ሰው በመሆን፣ በክርስቶስ ወዳለው ፍፁምነት ደረጃ እስከምንደርስ ነው።*

ኤፌ. 4፡ 1-13

በሕይወት ውስጥ ትልልቅ መድረክ ያላቸው ሰዎች እንኳን በሕይወታቸው የሚያነሳሣቸው ነገር ይፈልጋሉ፤ የሆሊውድ ታዋቂ የፊልም ተዋኒ የሆነው ድዌን "ዘ ሮክ" ጆንሰን ሲናገር እነዲህ ብሎ ነበር

"የስምንት ዓመት ልጅ እያለሁ ለመጀመሪያ ጊዜ "ሬይደር ኦፍ ዘ ሎስት አርክ" የሚለውን ፊልም በቫርሎት፣ ሰሜን ካሮላይና ካየሁ በኋላ ስወጣ ፊልሙን አይቼው ከመውደዴ የተነሣ በዚያ ጊዜ ይህንን አይነት ሰው መሆን እንደምፈልግ ገባኝ።"

*ጥያቄ:- በሕይወታችሁ እንደ እርሱ ለመሆን ወይም የምትሠራውን አይነት ሥራ ለመሥራት እጅግ የሚያነሳሣ ሰው ገጥሟችሁ ያውቃል? ስለ እነርሱስ ያስደነቃችሁ ወይም ይሠሩት ከነበረው ነገር በጣም ተጽዕኖ ያመጣባችሁ ምንድን ነው?*

ከቤተሰብ አባል፣ በታሪክ ውስጥ ከነበሩ ሰዎች መካከል፣ ከታዋቂ ሰዎች ወይንም ከልብ-ወለድ ስብዕናዎች መካከል ሊሆን ይችላል የሚያነሳሣን ነገሮችን ልናገኝ እንችላለን። አንዳንድ መነሳሣቶች የምንወዳቸውን ልምምዶቻችንን እና የምንሠራቸው ሥራዎች ላይ ያለንን ምርጫ እንዲሁም ባህርያቶቻችን እና ንጽረተ-ዓለማችንን የምንመርጥበት መንገድ ላይ ተጽዕኖ አላቸው። አንዳንድ ጊዜ ይህ በተቃራኒው ሊከሰት ይችላል። በሥራቸው ላይ እጅግ ስኬታማ የሆኑ ሰዎችን ስንመለከት ተስፋ እንቆርጣለን፣ "እንደ እነርሱ ያህል ልሠራው ስለማልችል ቢቀርብኝስ" እንላለን።

ከመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ብዙ ልናነሣቸው የምንችላቸው ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ ሰዎች አሉ። ከመጽሐፍ ቅዱስ ገጾች ውስጥም ሆነ ውጪ የእምነት ምሳሌዎችን ማግኘት እንችላለን። በተለይም የሠሯቸው ሥራዎች አስደናቂ ቢሆኑም፣ እነዚህ ግን እንደማንኛውም ሰው፣ ተራ ሰዎች የሆኑ፣ ነገር ግን ለእግዚአብሔር የታመኑ ነበሩ። ሙሴ በፈርዖን ፊት በድፍረት መናገር የቻለበት ምክንያት የማውራት ክህሎቱ ሳይሆን ለእግዚአብሔር ጥሪ መታመኑ እና ለእግዚአብሔር ኃይል መስጠት እንደሚያነሳሣው ያህል ያነቃቃል። እግዚአብሔር የማይለወጥ አምላክ ነው፤ እኛም እንደዚሁ መኖር እንችላለን። ከሁሉም በላይ አንድ ሰው ሊያነሳሣን እና ሊያስታጥቀን ይችላል፤ በኢየሱስ ውስጥ ልንኖረው የሚገባ ፍፁም የሕይወት ምሳሌ እና ለዚህ ሕይወት የሚያስታጥቅ ፍፁም ኃይልን እናገኛለን። በኢየሱስ ምሳሌ እና ትምህርት በተገራን እና በእርሱ በእምነት ሕይወታችን በታጠቅን ቁጥር በዙሪያችን ያሉ ሰዎችን ላይ ያለንን ተጽዕኖ ልናስተውል ይገባል።

ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳለው ኢየሱስ ለመንግሥቱ ሥራ ቤተ ክርስቲያንን በተለያዩ ስጦታዎች ባርኳል:- ወንጌላውያን ሐዋርያት፣ ነቢያት፣ አስተማሪዎች እና መጋቢዎች። እነዚህ ስጦታዎች ያሏቸው ሰዎች መጠራታቸው ቤተ ክርስቲያንን ለሥራ ለማስታጠቅ እና የክርስቶስን አካል ለመገንባት ነው።

*". . . የሆነ ቦታ ላይ ቤተ ክርስቲያን ውሰጥ ማገልገል ያለባቸው የሚከፈላቸው፣ ባለሙያ የሆኑ የነገረ-መለኮት ሥልጠና ያላቸው ሰዎች መሆን አለባቸው የሚለው ሃሳብ በክርስቲያኑ ማኅበረሰብ መካከል የበቀለ እና እጅግ ተቀባይት ያገኘ ሃሳብ*

*ነው። በዚህ አስተሳሳብ ውስጥ የምዕመኑ ብቸኛ ሥራ በቤተ-ክርስቲያን ውስጥ በእነዚህ ሰዎች የሚሰጡ እንደ ስብከት፣ ትምህርት፣ ማማከር እና ሌሎች ከቤተ ክርስቲያን የሚጠበቁ ነገሮች መገልገል ብቻ ይሆናል። ነገር ግን አንዳንድ የመሪነት ስጦታዎች የተሰጡት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰዎችን ለአገልግሎት ለማሳደግ ነው፤ ቤተ ክርስቲያን ክተት ያወጀ ሠራዊት መሆን አለባት!"*

አር. ሲ. ስፕሮል

በኤፌሶን ምዕራፍ 4 ላይ የተጠቀሱትን ስጦታዎቹን ተመልክተን አገልግሎትን ለጥቂት ሰዎች ብቻ የተሰጠ እንደ ሆነ ማሰብ ችግር አለው። የሐዋርያው ጳውሎስ መልዕክት ከዚህ የተለየ ነገር ያስተምረናል፤ እነዚህ አገልግሎቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉት ቤተ ክርስቲያን ራስዋ ልዩ ስለሆነች ነው። እግዚአብሔርም በእያንዳንዱ ተራ አማኝ ውስጥ በመሥራት ወደ አንድ ብስለት እንድናድግ ይሠራናል። በቤተ ክርስቲያናችን አካል ውስጥ ያለውን ማኅበረሰብ እየተንከባከብን በውጪ ያሉትን ደግሞ አንደርሳለን፣ ሁሉም ሰው ሠራተኛ ነው።

እኛም ስጦታችንን የመጠቀም ሃላፊነት አለብን። ይህም ማለት ደግሞ ሰዎችን ለማነሳሣት በሚገባ ማሰብ አለብን ማለት ነው። ይህን ደግሞ ከዚህ በፊት በተመከትናቸው የትሕትና እና ቅድስና ሃሳቦችን በመተግበር፣ የፀጋ ስጦታዎችን በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውሉ እና ቤተ ክርስቲያን ከዚህ የተነሣ ከመለያየት መትረፍ አለባት። ትዕቢት፣ ኩራት፣ ቅንዓት እና ስልጣንን ያለአግባብ መጠቀም ለቤተ ክርስቲያን መከፈል አቋራጭ መንገዶች ናቸው።

ጥያቄ:- በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ተጽዕኖ በሚገባ ሊያሳድር የሚችል ሰው ማን ነው? ይህንን እያሰባችሁ ሰዎችን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አብዝተው የሚሹት ቦታ ምንድን ነው? ምናልባትም መጋቢነት ወይም የወጣት አገልጋይ ወይም የዝማሬ መሪነት ሊሆን ይችላል፤ ብዙ ሰዎች ወንጌል ለመሥራት እና ማሠራጨት ይፈልጋሉ? የማይፈልጉ ከሆነ ለምን?

እነዚህ አራት ነጥቦች ሰዎች ወንጌልን በታማኝነት እንዲያሠራጩ ልናበረታታ የምንችልባቸው መንገዶች ናቸው:-

1. ወንጌልን ማወጅ
   ወንጌልን እንዲያሠራጩ ሰዎችን ልናበረታታ የምንችልበት አንደኛው መንገድ በመሰባሰባችን ጊዜ በተደጋጋሚ ወንጌልን በመስበክ ነው። ሌላው መንገድ ሰዎችን ወንጌል በምንሰብክባቸው መድረኮች ላይ በመጋበዝ የጸሎት አጋሮች ብቻ ሳይሆን ወንጌል ሲሰበክ እና ሰዎችን ለመጀመሪያ ጊዜ የወንጌልን መልዕክት እና ኃይል ሲለማዱ በመመልከት እንዲነሳሡ መሥራት ነው። ወንጌልን ባካፈልን ቁጥር፣ ሥራው የሁሉም አማኝ ዕድል እንደ ሆነ ማስገንዘብ ይገባል።
2. ምስክርነት ማዘጋጀት
   ሰዎች የሕይወት ምስክርነታቸውን እንዲያስቡ እና እግዚአብሔርንና በክርስቶስ ኢየሱስ ሕይወትን ካገኙበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ያላቸውን የሕይወት ዕድገት እንዲያስቡ ማበረታታት። መጀመሪያ እምነታቸው በኢየሱስ ላይ እንዴት ሊያደርጉ ቻሉ? እንዲሁም፣ እግዚአብሔር በቅርብ ጊዜያቶች በሕይወታቸው ምን ሠራ? አስበንበት የምናዘጋጀው የሕይወት ምስክርነት ሌሎችን ለማነሳሣት እና ለማስታጠቅ እንዲሁም እግዚአብሔርን በሕይወታችን የሠራውን ሥራ ተመልክተን ለማመስገን አስፈላጊ ነው።
3. ታሪክን ማውራትን አስቀድሙ
   በመሰብሰባችን እና ንግግሮቻችን ውስጥ የምናደርጋቸውን የወንጌል ሥርጭት ሥራ ታሪኮችን ማውራት አስፈላጊ ነው። እግዚአብሔር የሥራችን ውስጥ የሚሰጠንን ድል የምናከብር እና የምንበረታበት እና ካልተሳኩ ነገሮች ውስጥ አዎንታዊውን እና መሠራት ያለብንን መውሰድ ይገባናል። ቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ ያለው ጉባኤ እግዚአብሔር በተራ ሰዎች ውስጥ የሠራው ሥራ በሰሙ ቁጥር እንደሚጠቀምባቸው በማወቅ ለሥራ ያላቸው በራስ መተማመን ይጨምራል።
4. ዕድልን አዘጋጁ
   በቤተ ክርስቲያናችሁ እና በጓደኞቻችሁ መካከል ሰዎች ወንጌልን ሊሠሩበት የሚችሉበትን ዕድል አዘጋጁ። በዙሪያችሁ ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚሆን የወንጌል ሥራ በር መክፈት፣ በምትሠሩት ሥራዎች ውስጥ እንዲሳተፉ ሰዎችን ወደ አገልግሎት ቡድኖች መጥራት ወይም ጥቂት ወዳጆቻችሁን ለመንገድ ላይ ወንጌል ምስክርነት ይዛችሁ ውጡ። ይህንን መሥራት የምንትሉባቸው መንገዶች ብዙ ናቸው ከመውጣችሁ በፊት ሥልጠና ስጡ እንዲሁም ከተመለሳችሁ በኋላ ሥራው ላይ ተወያዩ ። በጊዜ ውስጥ ሰዎች የሚወስዱትን እነዚህን

ሥልጠናዎች ወደ ግል ሕይወት ልምምዳቸው በመውሰድ ወንጌል የሚሠሩበት መንገድ በየሳምንቱ በቤተ-ክርስቲያን ከሚዘጋጅ መርሃ- ግብር ወደ ዕለታዊ የሕይወት እንቅስቃሴ ይሻገራል።

በየትኛውም መንገድ ብንሠራው እንደወንጌላውያን በክርስቶስ የሆኑ ወንድሞች እና እህቶታችንን ለወንጌል ሥራ እና እንደእግዚአብሔር ልጆች ላለ መልዕክተኛ ማንነታቸው ለማነሳሳት እና ለመርዳት ራሳችንን መስጠት ይገባናል።

**ውይይት** (20 **ደቂቃ**)

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች/ ሃሳቦች ተወያዩባቸው**

- ሐዋርያው ጳውሎስ በኤፌሶን ምዕራፍ 4 ላይ ቤተ ክርስቲያንን በመገንባት ሲል ምን ማለት ነው?
- በምድር ላይ እንደ ኢየሱስ ተከታዮች መለየታችንን እንዲሁም አንደ ቤተ ክርስቲያን የተሰጠን ወንጌላዊነት የምንጠብቀው እንዴት ነው?
- በዚህ ክፍለ-ጊዜ ላይ ከተመለከትናቸው አራት መንገዶች በተጨማሪ ሰዎች ለወንጌል ሥራ እንዴት ማነሳሳት እንችላለን?

*“እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ፤ በተራራ ላይ ያለች ከተማ ልትደበቅ አትችልም፣ ሰዎችም መብራት አብርተው ከዕንቅብ ሥር አያስቀምጡትም፣ በቤት ውስጥ ላሉት ሁሉ እንዲያበራ በመቅረዝ ላይ ያስቀምጡታል እንጂ። እንደዚሁ ሰዎች መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማይ ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ በሰዎች ፊት ይብራ።”*

ማቴ. 5፡14-17

**ትግበራ** (10 **ደቂቃ**)

ይህ የመጀመሪያ ዓመት ከተገባደደ በኋላ ከዚህ ቡድን ጋር በመቆየት አብራችሁ በወንጌላዊነት መንገዳችሁ አብራችሁ ለማደግ እንደምታስቡ እናምናለን፤ ነገር ግን ቤተ ክርስቲያንን ለወንጌል ሥራ ለማነቃቃት በምትሰሩት ሥራ ውስጥ የራሳችሁን የአድቫንስ ቡድን ለመመሥረት እንደምትሰሩ ይታሰባል።

መባዛት የአድቫንስ እንቅስቃሴ ዋና መርህ ነው ምክንያቱን እንደወንጌላውያን ሌሎች ወንጌላውያንን ማበረታታት ዋና አላማችን ስለሆነ፡፡ በመሆኑም ይህንን እናነተ የተጓዛችሁትን መንገድ መሄድ እንዳለባቸው የምታስቡ እና ልባቸው ያለ ሰዎችን ስም በመዘርዘር በሚቀጥሉት ሳምንታት ውስጥ እያንዳንዳቸውን አናግሩ፤ የዚህን ቡድን ልምድ እና የአድቫንስ መርጃ መሣሪያዎች በመጠቀም የራሳችሁን ቡድን የምትመሰርቱበትን መንገድ አሰናዱ።

**ጸሎት**

ስለ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችሁ በጸሎት ጊዜ አሳልፉ፤ በተለይም አባላት ያለባቸውን የወንጌል አደራ በሚገባ እንዲፈፅሙ ጸልዩላቸው። እግዚአብሔር ሌሎችን የምታበረታቱበት መንገድ እንዲከፍትላቸሁ እና እያንዳንዱ የቡድኑ አባል ወንጌል ለዓለም ለመመስከር ብቻ ሳይሆን እያንዳንዱን የኢየሱስን ተከታይ ለወንጌል ሥራ እንዲያበረታታ አንዳችሁ ለአንዳችሁ ጸልዩ።

**ተጠያቂነት** (15 **ደቂቃ**)

የተጠያቂነት ቅጽ በመሙላት ለኢጋራችሁ እና ለአነስተኛ ቡድናችሁ አጋሩት እንዲሁም አንዳችሁ ለሌላችሁ ጸልዩ።

**ማስታወሻ**

**ክፍለ-ጊዜ ዐሥራ ሁለት**

**የአንድነት ጊዜ**

የመጀመሪያው ዓመት ላይ ያሳለፋችሁት አድቫንስ ቡድን ሥልጠና ጥግ፤ ይህ የአንድነት ጊዜ ነው። ይህንን የምታደርጉበት መንገድ የፈለጋችሁነት ሊሆን ይችላል ነገር ግን ጊዜውን እንዴት እንደምታሳልፉ በአድቫንስ ቡድን መርሆቸች እና የመጀመሪያውን አመት ወደሚገባ ማገባደጃ የሚያስፈልጉ ጥቆማዎች ተዘርዝረዋል።

**የአድቫንስ ቡድን የአንድነት ጊዜ እንዴት እንምራ?**

ዋናው ሃሳብ በመደበኘት የምንትገናኙበትን ቦታ በመቀየር እና የምታሳልፉነት ጊዜ በማርዘም ነው። የምትችሉ ከሆነ አንድ ሙሉ ቀን መውሰዱ እጅግ አስፈላጊ ነው፣ የማትችሉ ከሆነ ግን አንድ ሙሉ ጠዋት፣ ከሰዓት ወይም ምሽት ውሰዱ። በዚህ ጊዜ ላይ ምን ልታደርጉ እንደምትችሉ የሚከተሉት ጥቆማዎቸን ተመልከቱ

**ቁልፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች**

በዚህ የአንድነት ጊዜ ላይ አንድ ትኩረት ሰጥታችሁ ማጥናት የምትችሉት የቆላስያስ ክፍል የሚከተለው ሊሆን ይችላል

*“ከማመስገን ጋር ነቅታችሁ በትጋት ጸልዩ። እኔ እስረኛ የሆንሁለት የክርስቶስን ሚስጥር ማወጅ አንድንችል፣ እግዚአብሔር የቃሉን በር እንዲከፍትልን ስለ እኛ ደግሞ ጸልዩ፤ ደግሞም መናገር እንደሚገባኝ ቃሉን በግልጽ እንድናገር ጸልዩልኝ። በውጪ ካሉት ሰዎቸን ጋር ባላችሁ ግንኙነት በጥበብ ካሉት ሰዎች ጋር ባላችሁ ግንኙነት በጥበብ ተመላለሱ። በተገኘው ዕድል ሁሉ ተጠቀሙ። ለእያንዳንዱ ሰው እንዴት መልስ መስጠት እንደሚገባችሁ ታውቁ ዘንድ ንግግራችሁ በጨው እንደተቀመመ ሁል ጊዜ በፀጋ ይሁን።”*

ቆላስያስ 4፡2-6

ለወንጌላዊነት ሥራችን ከዚህ ክፍል ላይ ከሐዋርያው ጳውሎስ የምንማራች ዐሥራ ሁለት ነጥቦችን መመልከት እንችላለን

---

1. ትጉዎቸን ሁኑ (*ነቅታችሁ በትጋት ጸልዩ)*
2. መንፈሳዊ ኅብረትን አበረታቱ (ለእኛም ደግሞ ጸልዩልን)
3. በእግዚአብሔር ታመኑ (*እግዚአብሔር የቃሉን በር እንዲከፍትልን)*
4. ወንጌልን ለማወጅ ታማኞች ሁኑ( *የክርስቶስን ሚስጥር ማወጅ አንድንችል፣*
5. ግልጸነትን ፈልጉ ( *መናገር እንደሚገባኝ ቃሉን በግልጽ እንድናገር ጸልዩልኝ)*
6. ለወንጌል የሚገባውን ዋጋ መክፈል (*እኔ እስረኛ የሆንሁለት*)
7. በሰማያዊ ጥበብ ላይ ታመኑ (*በጥበብ ተመላለሱ።*)

---

8. ዕድሎችን ተጠቀሙ (*በተገኘው ዕድል ሁሉ ተጠቀሙ*)

9. ተናገሩ እንዲሁም አድምጡ (*ንግግራችሁ*)

10. መልካም እና ትሑታን ሁኑ (*ሁል ጊዜ በፀጋ ይሁን*)

11. የተለያችሁ ሁኑ (*በጨው እንደተቀመመ*)

12. የተዘጋጃችሁ ሁኑ (*ለእያንዳንዱ ሰው እንዴት መልስ መስጠት እንደሚገባችሁ ታውቁ ዘንድ*)

ይህንን ክፍል የምታጠኑበት በአንድነት ሆነ በየግላችሁ፣ ነጥቦችን የምትመለከቱበት መንገድ ሆነ በአብራችሁ የምትወያዩበት መንገድን ራሳችሁ የአንድነት ጊዜያችሁን በምትመሩበት ሁናቴ መምረጥ ትችላላችሁ። ነገር ግን የሚከተሉትን የተጠቆሙ እንቅስቃሴዎችን መካከል ስትመርጡ ይህንን ክፍል እንዴት እንደምትጠቀሙ አስቡ።

***ቃል*** - የአድቫንስ ቡድን ዋና አላማ ወንጌላውያን በእግዚአብሔር ቃል እንዲያድጉ ማስቻል ነው፤ ይህ የአንድነት ጊዜ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ በጥልቀት ለማደግ አመቺ ነው።

***ረጅም የእግዚአብሔር ቃል የማንበቢያ ጊዜ*** **(*በግል ማንበብ*)**- ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የምናሳልፈው ጊዜ በምን አይነት የባከነ ጊዜ አይደለም። በአንድ ጊዜ ሙሉ የማርቆስን ወንጌል ወይም አንድ የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ማንበብ የመጽሐፉን ሙሉ ሃሳብ በአንድ ጊዜ ለመረዳት አስፈላጊ ነው። አጭር መጽሐፍ ከሆነ ደጋግመን አያነበብን፤ በእያንዳንዱ ምንባብ መሃል በጸሎት፣ በምልከታ እና ማስታወሻ ጊዜን መውሰድ ደጋግመን ማንበብ እንችላለን። ሁላችሁም አንድ መጽሐፍ ማንበብ ትችላላችሁ ወይም ሁላችሁን የተለያዩ መጻሕፍት በማንበብ እርስ በርሳችሁ የተማራችሁን መከፋፈል ትችላላችሁ።

---

***የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት*** **(*የቡድን ጥናት*)**- በአንድነት ጊዜ ላይ የተለየዩ መጽሐፍ ቅዱስ ማጥኛ መንገዶችን ማሰለጥ ትችላላችሁ፤ ምናልባት ወደሃላ ተመልሳችሁ በአድቫንስ ቡድን ውስጥ የተመለከታችሁነትን ክፍሎች ደግማችሁ መመልከት ትችላላችሁ። ምናልባትም አንድ ክፍል ወይም አንድ ሀሳብ ወስዳችሁ በዚህ የአንድነት ጊዜ ላይ ትኩረጥ ሰጥታችሁ መመልከት ትችላላችሁ፤ ሁልጊዜ እንደምናደርገው ወንጌላዊነትን ከማሳደግ ላይ መሥራት አለባችሁ።

***ተጨማሪ ትምህርቶች እና ግብዓቶች*** - በዚህ መጽሐፍ ላይ የሚገኙት ሁለት የ,ተጨማሪ ጥናቶች ውስጥ ሁለቱም ሆነ አንዱ በአንድነት ጊዜው ላይ ለጥናት መጠቀም ትችላላችሁ፤ወይንም የራሳችሁን ትምህርት በዚህ የአድቫንስ ጥናት ቅርጽ በመጠቀም ማጥናት ትችላላችሁ። ከቡድናችሁ ጋር ልታጡት የምትቹሏቸው ጥቂት ሃሳቦች

- ስላሴ
- የእግዚአብሔር መንግሥት
- የክርስቶስ መስቀል
- የክርስቶስ ትንሣኤ
- የመንፈስ ፍሬዎች
- አምልኮ እና ወንጌል ሥርጭት

**ከሌሎች ጋር እምነትን መካፈል** - በአድቫንስ ድረ-ገጽ ላይ ያለው 'One Thing' Blog ላይ የተለያዩ ወንጌላውያን አገልግሎት ከመጀመራቸው በፊት ብናውቀው ብለው ስለሚመኙት አንድ ነገር ይፅፋሉ። ይህ አጭር ጽሁፍ ጥሩ የውይይት መጀመሪያ ሆኖ ያገለግላል።

**አዳዲስ ግብዓቶች**- ከዚህ የመጀመሪያ ዓመት በኋላ እንደ ቡደን መቀጠል እንምትፈልጉ ይታሰባል። አንድ እንደቡድን ልትጠቀሙበት የምትችሉት መንገድ በክፍለ-ጊዜያት መካከል የጠለያ መጽፍት በማንበብ በእነርሱ ላይ ለመወያየት ጊዜን መውሰድ ነው። በዚህ መምሪያ መጨረሻ ላይ ያለው የንባብ ጥቆማዎች- በተለይም የደመቁት አጫጭር ፣ ከዋና ርዕስ ጋር የሚዛመዱ በመሆናቸው ከሌሎቹ በበለጠ እንዲነበቡ ይመከራል።

**ጸሎት** - በአንድነት ጊዜው ላይ በቂ ሰዓት ለጸሎት ለዩ፣ አንድ ትኩረት የምታደርጉት ነገር ላይ የጸሎት ጊዜያትን አሳልፉ እንዲሁም በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ እና በሚመጡላችሁ ሃሳቦች ላይ ጸልዩ፤ በጸሎት የምትወዱትን ብታደርጉም የሚከተሉት ሶስቱ ሃሳቦች ይካተቱ ዘንድ ይመከራል

**እርስ በርሳችሁ ጸልዩ** - የአንድነት ጊዜያችሁ ዋና የጸሎት ሃሳብ እርስ በርስ መጸለይ ይሁን፤ ሰዎቸን እግዚአብሔርን ማመስገን የሚፈልጉበትን እና አንድትጸልዩላቸው የሚፈልጉበትን አንድ አንድ ሃሰቦች ውሰዱ። ሰዎች ግልጽ እና የተወሰነ የጸሎት ጥያቄን እንዲያቀርቡ እያበረታታችሁ የይድረስ ሳይሆን ጊዜ ወስዳችሁ እርስ በርሳችሁ ጸልዩ። በዚህ ጊዜ ላይ የሚመጡ ቃሎችን እና በመረታታትን ከመመዝገብ አትቆጠቡ።

**ለአካባቢያችሁ እና ለዓለም ጸልዩ** - ጊዜን ወስዳችሁ ላላችሁበት አካባቢ እና ለዓለም ወንጌል መስፋት ጸልዩ። በሁለቱም ሆነ በአንደኛው ላይ የተለየ ሸክም ካላችሁ በጸሎት ግለሰቦችን፣ ቤተ ክርስቲያኖችን፣ ሁኔታዎቸን፣ሚስዮናውያንን፣ ስለምትሰሙት ዜና ጸልዩ።

**ስለ አድቫንስ ጉዞ**- በዚህ ቡድን ውስጥ ስለነበራችሁ ጉዞ፣ ስለ ግል ዕድገታችሁ፣ ስለ ሰማችሁን የፍሬያማነት ታሪኮች እና ድነቶች ጌታን አመስግኑ። በእናንተ የጀመረውን ሥራ እንዲፈጽም እና የሚፈለጥ ክብር ወዳለበት የእርሱ መልክ መለወጥ እንዲሆንላችሁ ፀልዩ።(2 ቆሮንቶስ 3፡17-18ን እያነበባችሁ መጸለይ ትችላላችሁ)

**አምልኮ**- ጸሎት፣ የእግዚአብሔር ቃል ንባብ እና ኅብረትን ማድረግ አምልኮ ናቸው፤ በተጨማሪም በዝማሬ ሆነ በተለየ መንገድ አምልኮ ማድረግ ትችላላችሁ

**የዝማሬ አምልኮ** - በቡድናችሁ ውስጥ በዝማሬ መምራት የሚችል ሰው ካለ ጋብዙት እና በዝማሬ ጊዜን አሳልፉ፤ ነገር ግን ይህንን መምራት የሚችል ሰው ከሌለ ከኢንተርኔት ላይ የአንድነት የዝማሬን ጊዜ ሊመሩ የሚችሉ ብዙ መንገዶች ልታገኙ ትችላላችሁ፣ በተለይም ዩ-ቲዮብ ላይ በመግባት በግላችሁ ሆነ በኅብረት የምትወዱት መዝሙርን ከነግጥሙ ልታገኙ እና ለዝማሬ አምልኮ ልትጠቀሙት ትችላላችሁ።

**መላክ**- ሌላ እግዚአብሔርን ልታመልኩበት የምትችሉበት መንገድ እግዚአብሔር ለጠራችሁ ፣ ላስታጠቃችሁ እና ለሚከብርበት የወንጌላዊነት አገልግሎት እርስ በርሳችሁ መላላክ ስትችሉ ነው። በመጀመሪያው ዓመት የአድቫንስ ጥናት መጨረሻ ላይ ይህን ማወቅ እና እርስ በርስ በመረታታት ወሳኝ ነው፤ ለዚህ ጌታን እያመሰገናችሁ እያንዳንዳችሁ ለሰዎች መዳን እና ለእግዚአብሔር ክብር ይዛችሁት ስለምትወጡት ወንጌል እርስ በርሳችሁ ጸልዩ።

**ኅብረት** - አብረን ጊዜ ባሳለፍን ቁጥር በወዳጅነት እና እርስ በርስ በመተማመን እናድጋለን። ይህ የእድቫስ ቡድን ኅብረት በረከት እንደ ሆነላችሁ እናምናለን፤ ይህንን ኅብረት አንዳችሁ ለአንዳችሁ ተጠያቂ በመሆን እና ባላችሁ ኅብረት ለመደሰታችሁን በዚህ የአንድነት ጊዜ ላይ መ ቀጠል ትችላላችሁ።

**ተጠያቂነት** - ተጠያቂነት በዚህ የቡድን ጥናት ውስጥ ማዕከላዊ የሆነ ሥራ ነበር፤ አሁንም አንዳችሁ ለሌላችሁ በቅድስና እና በትሕትና ለመኖር ተጠያቂዎች ሁኑ።

**ፆም** - የዚህ የአንድነት ጊዜ አካል በሆነ መልኩ የፃም ጊዜ ለራሳችሁ መወሰን ትችላላችሁ ወይም የውይይት ጊዜያችሁን ምግብ ሰዓቶች ላይ በማድረግ ይህንን ጊዜ ለምክክር መጠቀም ትችላላችሁ። የአንድነት ጊዜያችሁን ግብ መፈፀም እስከቻላችሁ ድረስ ይህንን የምታደርጉበት ትክክኛ የሆነ የተሳሳተ መንገድ የለም ።

**የተለያዩ እንቅስቃሴዎች-** በአንድነት ጊዜ ላይ አብራችሁ ልትፈጽሙት የምትችሉትን እንቅስቃሴዎች ማቀድ ትችላላችሁ። የአንድነት ጊዜውን በተፈጥሮ በተከበበ ቦታ የምታሳልፉ ከሆነ በአንድነት ለጉዞ በመውጣት አንዳንድ የጥሞና አካላትን በዚህ ውስጥ ማካተት ትችላላችሁ። በከተማ መሃል ከሆነ ይህንን የምታደርጉት ምናልባትም የስዕል አውደ ርዕይ በመጎብኘት ውስጥ የጥሞና እና ውይይት ጊዜያቶች ማሳለፍ ትችላላችሁ።

እንዲሁም አብራችሁ የጨዋታን ጊዜ ማሳለፍ ትችላላችሁ- በቡድን የሚሠሩ ሥራዎችን፣ ስፓርት፣ መዝናኛ፣ የተለያዩ ነገሮች ማድረግ ትችላላችሁ። በጥሞና ሆነ በምታሳልፉት የአንድነት ጊዜ ውስጥ እርስ በርሳችሁ ለማደግ ጥሩ ጊዜ እንዲኖራችሁ ስሩ።

**የሚቀጥለው** ርምጃ

የመጀመሪያው የአድቫንስ የጥናት አመት ከመጠናቀቁ እና የአንድነት ጊዜው ከማለቁ በፊት ለዚህ ቡድን እና ለሚቀጥለው አዲስ ለሚመሠረት ቡድን ያለው የሚቀጥለውን ርምጃ ምን እንደሚመስል ተመልከቱ

**ይህ ቡድን**

ይህ የአድቫንስ ቡድን በተሳታፊዎችን ላይ የነበረውን ተጽዕኖ ላይ ተወያዩ፤ የቡድኑ  አባላት ያላቸውን ሃሳብ እና ግምገማ እንዲናገሩ እነዲሁም በግል እና በቡድን ምን ያህል እንዳደጉ እና በአመት ውስጥ ያከናወኑት ዋና ትምህርት ምን እንደ ሆነ እየተወያያችሁ እርስ በርሳችሁ ተበረታቱ።

ይህንን የቡድን መሰባሰብ ስለመቀጠል ካለወሰናችሁ፤ አሁን ተነጋገሩ እና ለመውታት የሚፈልግ ወይ መቀጠል የማይችል ካለ ካሁኑ ምን ያህል ሰው መቀጠል እንደሚችል እንድታውቁ ይህንን ተነጋገሩ። በመሆኑም በቂ የሚቀጥ ሰው ካኞችሁ ከዚህ በኋላ የሚኖራችሁን መሰባሰብ ምነ አይነት ቅርጽ እና እንሲሁም በሚቀጥሉት ወራት ምን አዲስ ግብዓት እነደምትጠቀሙ በመወሰን ስለመጀመሪያው አመት የአድቫንስ ቡድን ጊዜ ጌታነ እያመሰግናችሁ ሊመጣ ስላለው ጊዜ ጸልዩ።

**አዲስ ቡድን**

ካለፈው ክፍለ-ጊዜ ላይ በተሰጠው የትግበራ ኃላፊነት በመመሠረት የአዳዲስ ቡድኖች መቋቋም ሂደት እና ሰዎን ለሚሰሩት ቡድን ምን ያህል እያናገሩ እንደ ሆነ የቡድን አባላቶቻችሁን ጠይቁ።

ይህንን የአንድነት ጊዜ በየትኛውም መንገድ ለመምራት ብትወስኑም፤ የአድቫስን ትኩረት እንዳትስጡ ጠጠንቀቁ፤ እንደቡድን ያሳለፋችሁትን ጊዜ እየገመገማችሁ ስለመጣው ፍሬ እና ዕድገት እግዚአብሔርን እያመሰገናችሁ ስለወደፊቱ ደግሞ እግዚአብሔር እርዳ ለምኑ።

# ተጨማሪ ክፍለ-ጊዜያቶች
# እና
# ግብዓቶች

**ተጨማሪ ክፍለ-ጊዜ አንድ**

**በንግግር ወንጌልን መመስከር**

ይህ ክፍለ-ጊዜ የምናገኛቸውን ይህም ከመድረክ ላይ ብቻ የሆኑ ሁሉ ወንጌልን የመመስከር ዕድሎች በሚገባ መመልከት እና መጠቀም እንደሚገባል የምንመለከትበት ነው።

**ክፍለ-ጊዜው በአንድ ዐረፍተ-ነገር**

................................................................................

አብዛኛው ወንጌል የሚሰበክበባቸው ንግግሮች የሚካሄዱት በሰዎቸን ዘንድ ባለ የግል ውይይት/ ተግባቦት ነው። በመሆኑም መድረክ ላይ ብቻ የመስበክ ዕድል ስናገኝ ሳይሆን እግዚአብሔር በሚከፍትልን መንገዶች ሁሉ ወንጌልን በግልጽ ለመናገር የተዘጋጀን መሆን አለብን።

**የክፍለ-ጊዜው ዳራ**

................................................................................

በእያንዳንዱ ቀናችን ከሰዎች ጋር በሚኖረን ንግግር የተሞላ ነው፤ ፊት ለፊት ሆነ የዘመኑ ቴክኖሎጂ አመቺ ባደረገልን መንገድ በዓለም የትኛው ቦታ ካሉ ሰዎች ጋር መነጋገር እንችላለን። እነዚህ በተለያዩ የመገናኛ መሣሪያዎች የሚደረግ ተግባቦት ፊት ለፊት የመጋገር ያህል ባይሆንም በዘመናችን ከወዳጆቻችንም ሆነ ከማናውቃቸው ሰዎች ጋር ለምናደርው ንግግር ዋና የማይገኝለት እና መደበኛ ሆኗል።

ከመድረክ ላይ ያለ ስብከት ለንግግር ብዙ ቦታ አይሰጥም፤ ብዙውን ጊዜ መልዕክታችን ከተናገርን በኋላ ሰዎች ለመልዕክታችን በሰሚያችን ልብ ውስጥ እንደሚያርፍ እና ስር እንደሚሰድ እናምናለን። ነገር ግን በንግግር ውስጥ ጥያቄን ለመጠየቅ፣ ግንኙነትን ለመመሥረት እና ለማድመጥ ዕድል ይሰጣል። አንዳንድ ጊዜ ከመድረክ ላይ ለሚመጣ መልዕክት ምላሽ ለመስጠት አይመችም ነገር ግን በንግግር ውስጥ ግን ለሰዎቸን የግል ፍላጎት እና ጥያቄዎች ቀጥተኛ ምላሽ ለመስጠት ዕድል ይከፍታል።

ሁሉም የወንጌል እወጃ ከመድረክ ላይ መሆን የለበትም፤ በመጽሐፍ ቅዱሳችን ላይ ኢየሱስ ለጉባኤ ከሰበከው በላይ በግል ከሰዎች ጋር የተጋገረባቸው ጊዜያት ይበዛሉ። በማርቆስ ምዕራፍ 10፡15 ላይ ኢየሱስ ለበርጠለሚዮስ "ን,ም እዳደርግልህ ትወዳለህ" ለሚለው ጥያቄ ምላሹ "ማየትን እፈልጋለው" አለው። ይህ የሰውየውን ፍላጎት እና ኢየሱስ ማድርግ እንደሚችል ኃይል እንዳለው እንደሚያውቅ የሚያሳ ቀላል ምላሽ ነው። ይህ ግንኙነት ወንጌልን ለመስበክ ለኢየሱስ ምንም አይነት በርን ባይከፍትም ነገር ግን ለኢየሱስ የሰውየውን ፍላጎት የሚያሟላበት ዕድል ነበር- ከዕውርነት ወደ ኅብረት እንዲመጣ ሆነለት።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ወንጌላዊ የተባው ብቸኛው ፊሊጶስ በእግዚአብሔር መልዓል ለኢትዮጲያዊው ጃንደረባ አንድ ለአንድ በሆነ ንግግር እንዲሰብክለት ለትልልቅ ጉባዔ ስብከቶቹ መሃል ወሰደው (ሐዋርያት ሥራ 8፡26-40)። ለአብዛኛው የኢየሱስ ክርሰቶስ ደቀ መዛሙርት ወንጌል የተሰበከበት ዋና መንገድ በግል ንግግር፣ ለወዳጆች፣ ለሥራ ባደረቦቻቸው እና ለማያውቁት ሰው ሁሉ ወንጌል በግል ይሰብኩ ነበር። የአዲስ ኪዳን ታሪኮች እንደሚያሳዩን ኢየሱስም ሆነ ደቀመዛሙርቱ ወንጌልን በጀማ ሆነ በግል ለመስበክ የተዘጋጁ እንደሆኑ ነበር፤ እኛስ የተዘጋጀን ነን?

**የክፍለ-ጊዜው መምሪያ**

ሰዎች ያሉበትን ለማወቅ እና ለመበረታታት ጊዜ ውሰዱ፤ እርስ በርስ ታሪክ በመከፋፈል፣ ስለተገኙ ዕድሎች ያላችሁን ሃሳብ መከፋፈል እና ሌላ የትኛው ነገር በማንሣት እርስ በርስ ተነጋገሩ። ለትንንሽ ቡድን እያንዳንዱ የቡድን አባላት ካለፈው የቡድን ስብሰባ በኋላ ያጋጠማቸውን አንድ ድል እና አንድ የተቸገሩበትን ነገር እንዲያካፍሉ ዕድል ስጡ፤ ለትልቅ ቡድን አራት/ አምስት የሚሆኑ የቡድን አባላት ከባለፈው ስብበሳ በኋላ ያላቸውን ምስክርነት እንዲያካፍሉ ዕድል ስጡ።

**ጸሎት**

.............................................................................................

ጊዜውን ለእግዚአብሔር በመስጠት እና በትውውቅ ጊዜ በተነሣ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ጉዳይ ላይ ጸልዩ።

**ትምህርት (25-35 ደቂቃ)**

.............................................................................................

ራሳችሁ ልታቀርቡበት በምትችሉበት መንገድ ወይም ቃል በቃል ይህንን ትምህርት ማቅረብ ትችላላችሁ። ባገኛችሁት ወንጌልን ሰብካችሁ ጌታን ላገኙ ሰዎች ጸልዩላቸው።

*" በዚህ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ተመልሰው መጡ፣ ከሴት ጋር ሲነጋገር በማግኘታችን ተደነቁ። ሆኖም ግን "ምን ፈከግህ?" ወይም "ለምን ከሴት ጋር የምትነጋገረው ለምንድን ነው?" ብሎ የጠየቀው ማንም አልነበረም። ሴትዮዋም እንሥራዋን ትታ ወደ ከተማ ተመለሰች ለሕዝቡም "ያደረግሁትን ሁሉ የነገረኝን ሰው ኑና እዩ፤ እርሱ ክርስቶስ ይሆን እንዴ?" አለች ። እነርሱም ከከተማ ወጥት ወደ እርሱ አመሩ ።"*

ዮሐ. 4፡27-30

ለመጨረሻ ጊዜ ስለ እምነታችሁ ለማያምን ወዳጃችሁ ወይም ከማታውቁት ሰው ጋር የተነጋገራችሁት ? ብዙ በስብከት የሚያገለግሉ ወንጌላውያን በግል የሆነ ንግግር ይከብዳቸዋል፤ መድረክ እና ማይክ ብንሰጣቸው ጀግና የሆኑ ሰዎች መንፈስ ቅዱስ ካፌ ውስጥ አንድን ሰውን እንዲያናግሩ ሲያነሳሳቸው ግን ሌላ ታሪክ ነው።

***ጥያቄ፡ በመድረክ ላይ ለመስበክ ጎበዝ የሆኑ አንዳንድ ሰዎች በግል አንድ ለአንድ ንግግር ለምን ይከብዳቸዋል? በግል የአንድ ለአንድ ስብከት/ ንግግር በሚገባ ትጠቀማለህ ወይንስ ይከብድሃል?***

ኢየሱስ ሰውን በግል መድረስ ይፈልጋል፤ ጉባኤን እንደሚደርስ ሁሉ ሰዎችን በግል አነድ ለአንድ የሆነ ግንኙነት እና የሰዎቸን ሕይወት በግል በመድረስ አገልግሎት ውስጥ በሚገባ ሰዎች ሲፈልግ እና ሰዎችም ሲፈልጉት እንመለከተዋለን። ኢየሱስ ለጉባኤ ሆነ ለግል፣ ስብከቱን ለመስማት ለሚፈልጉ ሆነ ሊገሉት ለሚሹ ፣ ለተለያዩ አይነት ሰዎች - ለሀብታም ሆነ ድሃ፣ ለወንድ ሆነ ሴት፣ ለበሽተኛ ሆነ ጤነኛ፣ ለሃይማኖተኛው ሆነ እምነት የለሽ መልዕክቱን ለመናገር ዝግጁ ነበር።

ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል ላይ የተጠቀሰው ታሪክ ውስጥ ከሳምራዊቷ ሴት ጋር ከነበረው መስተጋብር ውስጥ ብዙ መሠረታዊ ነገሮቸን እንማራለን

1. ***ለመስተጋብሩ የተዘጋጃችሁ ሁኑ***

ለሳምራዊቷ ሴት ይህ መስተጋብር የማይጠበቅ ምናልባትም ትክክል ያልሆነ ነበር፤ ኢየሱስ ግን ሊያናግራት የመጀርያውን ርምጃ በአካዊ ውሃ የመጠጣት ፍላጎቱ በመግለፅ ጀመረ። ስለ አንድ ነገር ያለንን ፍላጎት መሠረት በማድረግ ንግግርን መጀመር እንችል ይሆን? የቤታችሁን የውሃ ቆጣሪ ለመሥራት የሚመጣው ሠራተኛ፣ ቡና የምታፈላ እና የምታቀርብላችሁ ሠራተኛ፣ አስፈሪ የሆነ የህከምና ውጤት የሚሰጣችሁ የህክምና ባለሙያ፣ ሊሆኑ ይችላሉ ምናልባት ለአድማጮቻችን ይህ ድንገተኛ ሊሆን ይችላል ነገር ግን ይህንን ጊዜ ለመጠቀም ሁል ጊዜ በክርስቶስ ያለው ተስፋ ለመናገር በየተዘጋጀን መሆን አለብን።

2. ***በግል እና አዎንታዊ በሆነ መንገድ ግንኙነት ፍጠሩ***

ኢየሱስ ሳምራዊቷን ሴት የሚያናግርበት መንገድ እጅግ የሚደንቀው ንግግሩ በመልካምነት፣ ስሜቷን በሚጠብቅ መንገድ እና በሃዘኔታ የተሞላ ነበር። ጤነኛ በሆነ መንገድ ንግግራችን መጀመር በተፈጥሮ የሚመጣ መንገድ መጀመር አለበት ለዚህ ነው ንግግሩ ከግል ሕይወቷ እና እውነትን በፍቅር የሚገልፅበት መንገድ መመልከት እንችላለን።

3. ***በሚገባ ማድመጥ***

ሰዎች ስለምናምነው ነገር መጠየቃቸው አይቀርም፤ በነዚህ ጥያቄዎች ከመደናገጥ ይልቅ በሚገባ በማድመጥ እውነተኛ እና ለልብ በሆነ መልኩ መመለስ አለብን። ይህ አንዳንድ ጊዜ እኛ ራሳችንን የምንጠይቃቸው ጥያቄዎች ሊሆኑ ይችላሉ- ልክ

እንደኢየሱስ ከሳምራዊቷ ሴት ጋር እንዳደረገው ማለት ነው። የምናቀርባቸው ሃሳቦችን እንዲሁ እንዲቀበሉ ሳይሆን ነገር ግን ሃሳቦቸ ላይ ሰዎች ምልከታ ሊያቀርቡ እንዲሁም የራሳቸውን ሃሳብ ሊያቀርቡ ይችላሉ። ኢየሱስ ወንጌል በሚያቀርብ ጊዜ ጥያቄ በመጠቀም የሰዎቸን ችግር በራሳቸው ንጽረተ ዓለም ላይ በመነሳት እውነትን ያቀርብላቸው ነበር።

4. **ከመረዳት ወደ መገለጥ ተሻገሩ**

ኢየሱስ የሚናገረውን ነገር በመጀመሪያ ሳምራዊቷ ሴት በሚገባ አልተረዳችም ነበር (ቁጥር 11) ነገር ግን ኢየሱስ በሚያደርገው ንግግር ፀንቶ የሚነጋገሩበትን ሃሳብ እስከትረዳ ድረስ ቅርፅን ሰጠው። በሰው ንግግር መካከል አለመግባባት እና የትርጉም መዛባት የሚያጋጥም ነው፤ ሳትደናገጡ በንግግር መፅናት አለባችሁ። የምትነጋገሩት ነገር በሚገባ እስከትግባቡ ድረስ በሚገባ ድልድይ መሥራትን አታቋርጡ የእናንተ ኃላፊነት ሃሳባችሁን ግልፅ ማድረግ ነው፤ የተናገርነውን መልዕክት ወደ መረዳት የሚያደርሰው እግዚአብሔር ነው።

5. **ዋናውን ነገር ዋና አድርጉ**

ኢየሱስ ውሃ እንድትሰጠው ከጠራት በኋላ በሚኖረው ንግግር ተከትሎ ወደ ፓለቲካዊ ሆነ ባህልን መሠረት ያደረገ ውይይት መግባት ይችል ነበር፤ ነገር ግን ዋናውን ነገር ዋና በማድረግ የወንጌልን ዋና መልዕክት ከማድረግ አልረሳም። በንግግር ውስጥ በሚደረግ የወንጌል ሥርጭት ብዙ ጊዜ ወደሌላ ሃሳብ የመዞር ዕድሎች አሉ ነገር ግን ዋና አላማችን የክርስቶስን መስቀል ማዕከላዊ ማድረግ አለብን።

6. **ማደግ የሚቻለውን ነገር ተመልከቱ**

የምትነጋገሩት ሰው ወንጌል የመቀበል እና ለዚህ ወንጌል ነገ ምስክር ወደመሆን ማደግ ይችላል። በቅርቡ ወንጌልን ሰምተው ወደጌታ የመጡ ሰዎች የሚገርሙ የወንጌል ምስክሮች ናቸው፤ ይህ ሊያስፈራን እና መፈለግን ሊያደርግ ይገባል - የወንጌልን አስደናቂ እና የሚጋባ ደስታ እንዳናታው መፍራት እንዲሁም የምንመሰጅርላቸው ሰዎች ስኬታማ እና ሌሎችን የሚማርኩ የወንጌል ሰባኪያን መሆን እንዲሆኑ መፈለግ አለነትን

ምናልባት ሁላችንም የምንሰብክበት መድረክ ላይኖረን ይችል ይሆናል (ምናልባትም 'የሚሰብክ ወንጌላዊ' የሚል ጥሪም ሆነ ስጦታ ላይኖረን ይችል ይሆናል) ነገርግን ሁላችንም ወንጌልን የመስበክ ኃላፊነት አለብን።በዓለም ላይ ወንጌልን ለማሠራጨት ከሚደረጉ ውይይቶች አብዛኞቹ የሚደረጉት በግል መስተጋብር - ወንጌል መናገር የሚሹ ሰዎች ወንጌል ለመስማት ከሚፈልጉ ሰዎች ጋር በሚያደርጉት ውይይት ውስጥ ነው። ኢየሱስ እንዲሁም ደቀመዛሙርቱ ለዚህ አይነት ወንጌልን ማድረስ የተሰጡ ነበሩ እኛም ይህንን ልናደርግ ይገባል።

**ውይይት (20 ደቂቃ)**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች/ ሃሳቦች ተወያዩባቸው**

- ስለ እምነት ከሰዎች ጋር በሚኖረን ውይይት ውስጥ ማዳመጥ ምን ያህል አስፈላጊ ነው?
- በውይይት ውስጥ የሚደረግ ወንጌል ሥርጭት የምናደርገው ሰው ወዳጅ ወይም የማናውቀው ሰው በመኖኑ መካከል ምን ልዩነት ሊኖር ይችላል?
- በግል ወንጌልን ለመመስከር ምን ያህል ዕድሎችን በመፈለግ ምን ያህል አስበን መንቀሳቀስ እንችላለን?
- በግል ወንጌልን መስበክ የሚከብዳቸውን ሰዎች በምን መንገድ መደገፍ ትችላላችሁ?

*" ወንጌልን በመስበካችን ውስጥ ያለብን ትልቁ ትግል ወንጌል የምንሰብክባቸው መንገዶች ሳይሆኑ ዕድገታችን ነው። የእግዚአብሔር ልብ በእኛ ውስጥ አለን? እንዲሁም እግዚአብሔር ስለጠፉት ግድ እንደሚለው ግድ ይለን ይሆን? የእግዚአብሔር ልብ በእኛ ውስጥ ካለ፤ የእግዚአብሔርን መንግሥት አላማ ለማስፋት ከማያምኑ ሰዎች ጋር በሚኖረን የትኛውም ንግግር ውስጥ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማስፋት ማድረግ የሚገባንን ሁሉ እናደርጋለን?"*

ኖርማን እና ዴቪድ ጊስነር

**ትግበራ (10 ደቂቃ)**

በግል ሕይወታችሁ አካል ከሆነ አንድ ሰው ጋር በአገልግሎት ባልተያያዘ መንገድ ስለ ወንጌል ተወያዩ- በመደበኛ መስተጋብር ስለ እምነታችሁ ጥያቄ ካላቸው እንዲጠይቁ እና ምላሽን ለመስጠት ደስተኛ እንደሆናችሁ ግለፁ ወይንም ስለኢየሱስ ምን እንደሚያስቡ ጠይቁ እና ይህ ውይይት ወዴት እንደሚደርስ ተመልከቱ።

**ጸሎት**

በየዕለቱ በዙሪያችሁ ያለውን ወንጌል የመሥራት ዕድል አይኖቻችሁ ተከፍተው ማየት እንድትችሉ እየለመናችሁ፤ በፊታችሁ እግዚአብሔር ስላዘጋጀው ዕድል እና በዚህ ሥራው ውስጥ ባለአደራ ስላደረጋች አመስግኑት። አንድ ለአንድ በሆነ የወንጌል ምስክርነት ለሚቸገሩ ሰዎች እየፀላያችሁ እርስ በእርሳቹ መንገድን ስትቀጥሉ ተደጋገፉ።

**ተጠያቂነት (15 ደቂቃ)**

**የተጠያቂነት ቅጽ በመሙላት ለአጋራችሁ እና ለአነስተኛ ቡድናችሁ አጋሩት እንዲሁም አንዳችሁ ለሌላችሁ ጸልዩ።**

**ተጨማሪ ክፍለ-ጊዜ ሁለት**

**ክርስትናና ምካቴ-እምነት**

*ይህ ክፍለ-ጊዜ የምካቴ-እምነት መንገዶችን የምንመለከትበት ሲሆን ዓለም ሊያነሳቸው ለሚፈልጋቸው ጥያቄዎች በሚገባ የተዘጋጀን እና ሁል ጊዜ ወደ ኢየሱስ የምንጠቁም እንድንሆን ይረዳናል።*

**ክፍለ-ጊዜው በአንድ ዐረፍተ-ነገር**

..............................................................................

*ምካቴ-እምነት ማለት ስለእምነታችን ለሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽ እንዲኖረን እና እምነታችንን ለሚቃወሙ ምኪታን መስጠት የምንችልበት የወንጌል ሥርጭት አንድ መንገድ ነው።*

**የክፍለ-ጊዜው ዳራ**

..............................................................................

ስለእምነታችን እና ስለምናገረው መልዕክት ጥያቄዎች ስንጠየቅ እውነተኛ ምላሽን በመስጠት ወደ ኢየሲስ ክርስቶስ ሰዎችን የመምራት ኃላፊነት አለብን። ክርስቲያናዊ ምካቴ-እምነት በቀላሉ ሲተረጎም "ለክርስትና እምነት ዘብ መቆም ነው"። ምካቴ-እምነት አዲስ የንጌል ስርጭ መንገድ ሳይሆን ወደሃላ ተመልሰን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኘው ነው፤ በ 1ጴጥሮስ 3፡15 ላይ ያለውን የህግ ቃል የሆነውን "አፓሎጂያ" ላይ በመነሳት እና ሐዋርያው ጳውሎስ በሐዋርያት ሥራ 17 ላይ የነበረውን ንግግር የተሰናዳበት እና የቀረበበት መንገድ መሠረት ያደረገ እሳቤ ነው። መጽሐፍ ቅዱሳችን ወንጌል ላይ ለተነሰ ጥያቄዎች ፣ ሃሳቦች ሆነ ተቃርኖ የሚቀርበው አመክኖአዊ በሆነ እና ከመደበኛው መንገድ የተለየ አቀራረብ ያለው ሃሳብ ምካቴ-እምነት ነው።

የምካቴ-እምነት ዋና አላማ እግዚአብሔር ተቀባይት እንዲኖረው ሳይሆን ሰዎቸን ወደ እውነት ለመምራት እና ያለንን ተስፋ እውነተኝነት ለማሳየት ነው። ለእምነታችን ዘብ የምንቆመው እምነታቸን ላይ ጥያቄ ያለቸው ሰዎች ይህንን ተመልከተው ወደ ክርስቶስ እንዲመጡ ነው። ማንም ሰው ግን በክርክር ወደ ክርስቶስ አይመጣም - በእግዚአብሔር የማዳን ኃይል ብቻ ነው።

*"ምካቴ-እምነት ማንንም ኢያድንም ነገር ግን ምካቴ-እምነት እንደ መጥምቁ ዮሐንስ ወደ መስቀል መንገድ የሚጠርግ እና የሚያቃና መሆን አለበት"*

ጄ. ደብልዩ. ሞንትጎመሪ

ምካቴ-እምነት ኢየሱስን ከዙፋኑ ላይ ለማውረድ ለሚሞክር የትኛውም መንፈሳዊ ሆነ አዕምሮአዊ ትግል የሚሰጥ ምላሽ ነው። ይህ አስቸጋሪ ወደሆኑ ውይይቶች ሊያመራ ይችላል በዚህ ጊዜ ግን ክሪስ ሲክሰን ያለውን መርሳት የለብንም "አላማችን ሰዎችን ማሳዘን አይደለም ነገር ግን የክርስቶስ ተቃዋሚ የሆነውን ሁሉ ግን ማጋለጥ ነው።"ምካቴ-እምነት የወንጌል ሥርጭት መንገድ ብቻ አይደለም፤ በውጪ ያሉት ወንጌልን ሰምተው የሚመጡበት እንደ ሆነ ያህል ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አማኞችን ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ጥልቅ እውነት እንዲያድጉበት መጠቀም እንችላለን።

**የክፍለ-ጊዜው መምሪያ**

..............................................................................

**የትውውቅ ጊዜ (10-20 ደቂቃ)**

ሰዎች ያሉበትን ለማወቅ እና ለመበረታታት ጊዜ ውሰዱ፤ እርስ በርስ ታሪክ በመከፋፈል፣ ስለተገኙ ዕድሎች ያላችሁን ሃሳብ መከፋፈል እና ሌላ የትኛው ነገር በማንሣት እርስ በርስ ተነጋገሩ። ለትንንሽ ቡድን እያንዳንዱ የቡድን አባላት ካለፈው የቡድን ስብሰባ በኋላ ያጋጠማቸውን አንድ ድል እና አንድ የተቸገሩበትን ነገር እንዲያካፍሉ ዕድል ስጡ፤ ለትልቅ ቡድን አራት/ አምስት የሚሆኑ የቡድን አባላት ከባለፈው ስብበሳ በኋላ ያላቸውን ምስክርነት እንዲያካፍሉ ዕድል ስጡ።

**ጸሎት**

..............................................................................................

ጊዜውን ለእግዚአብሔር በመስጠት እና በትውውቅ ጊዜ በተነሣ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ጉዳይ ላይ ጸልዩ።

**ትምህርት (20-30ደቂቃ)**

..............................................................................................

*ራሳችሁ ልታቀርቡበት በምትችሉበት መንገድ ወይም ቃል በቃል ይህንን ትምህርት ማቅረብ ትችላላችሁ።*

*"ክርስቶስን ጌታ አድርጋችሁ በልባችሁ ቀድሱት። እናንተ ስላላችሁ ተስፋ ምክንያትን ለሚጠይቋችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ሁልጊዜ የተዘጋጃችሁ ሁኑ፤ ነገር ግን ይህን ሁሉ በትሕትናና አክብሮት አድርጉት"*

1ጴጥ. 3፡15

ሐዋርያው ጴጥሮስ ስላለን ተስፋ ለሚጠይቁን ሁሉ መልስን ለመስጠት የተዘጋጀን መሆን አለብን። ወንጌልን መስበክ ቅድሚያ የሚሰጠው ሲሆን ለሚነሱ ጥያቄዎች በሚገባ የታሰበባቸው እና ትርጉም ያላቸው ምላሾችን ማዘጋጀት አለብን። *መሠረታዊ የሆኑ የፍልስፍና ጥያቄዎች እንዲሁ የሕይወት አስቸጋሪ ጥያቄዎች ናቸው "እዚህ ያለሁት ለምንድን ነው?"* ፣ "ከየት ነው የመጣነው?"፣ "የሕይወት ትርጉም ምንድን ነው?" እንዲሁም በነባራዊው ጉዳየች ላይ- ለምሳሌ - ስለጻታዊ ፍላጎት፣ ስለፆታ ማንነት፣ ስለ ፍቺ እና ውርጃ ጥያቄዎች ሊነሱ ይችላሉ። ራሳችንን ባህላዊ የሆኑ ክርስቲያናዊ እሴቶቸን ለመጠበቅ በሚል ዘመነኛ ሳይንሳዊ ሃሳቦችን ልንቃወም እንችል ይሆናል ለምሳሌ በዘፍጥረት ላይ እግዚአብሔር ዓለምን የፈጠረበት መንገድ ከሳይንሳዊ ዝግመተ ለውጥ ጋር እናወዳድር ይሆናል፤ ሌላው ምሳሌ መልካም የሆነ እግዚአብሔር አንዴት መከራን እንደሚፈቅድ ያለ ጥያቄ ሊሆን ይችላል።

*ጥያቄ፡ ከዚህ በፊት እምነታችሁን እንድታስረዱ ተጠይቃችሁ ታውቃላችሁ? ይህንን በተጠየቃችሁ ጊዜ ለመመለስ ምንያህል የተዘጋጃችሁ ነበራችሁ?*

ምካቴ-እምነት በራሱ ሰዎች ማዳን አይችልም አለበለዚያ የሰዎች ማዳን ግፊት እና ኃላፊነት በክርክሮቻችን አመክኖያዊነት ላይ ይወድቅ ነበር። ምካቴ-እምነት ግን ሰውን ካለማመን ወደ ማመን የሚሄድበትን መንገድ ማዘጋጀት ይችላል፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ራሱ ብቻ ነው ሰዎችን የምንነግራቸውን እውነት በመጠቀም ካለመዳን ወደ መዳን ሊያመጣ የሚችለው። ከማያምን ሰው ጋር በመንገድ ዳር ቆመን ከመንገዱ መድረሻ ላይ ባዶ የሆነው የክርስቶስ መስቀል ይታያል፤ በእኛ እኛ በመስቀሉ መካከል ጉድጓድ፣ የተሰባበረ መንገድ፣ ግድግዳዎች፣ ፍርሥራሽ እና የተሰባበሩ ሹል ነገሮች መንገዱን ዘግተውታል፤ መስቀሉ ራሱ በጉም ስር በሚገባ አይታይም። ምካቴ-እምነት ይህንን የማያምነውን ሰው በመያዝ ጉድጓድ እየሞላን፣ የተሰበረውን መንገድ እየተውን፣ ፍርሥራሹን እያነሳን እና መንገዱን የዘጉትን ነገሮችነ ዘወር እያደረግን በጉም ውስጥ የማያምነውን ሰው ወደክርስቶስ መስቀል የምናደርስበት ነው። አላማችን የማያምነው ሰው ወደ መስቀል በማድረስ ከሞት የተነሣው ክርስቶስ ጋር ማገናኘት ነው፤ ምካቴ-እምነት በወንጌል ሥርጭት ውስጥ ገና ያላመነው ሰው ክርስቶስን እንዲመለከት የምንረዳበት መንገድ በመሆን ነው።

ስኬታማ ለሆነ የምካቴ-እምነት ውይይት የሚከተሉትን አራት ነጥቦች በሚጋባ መያዝ አለብን

1. ***የዝግጅት ኃይል ጋር መሥራት*** - ራቪ ዛካራያ፣ ዊልያም ሌን ክሬግ እና ጀን ሌኖክስን የመሳሰሉ ታዋዊ የሆነ የምካቴ-እምነት ሙሁራን ፤ ምካቴ-እምነትን ወንጌል ሥርጭት ማዕከል በማድረግ - ስነመለኮት፣ ፍልስፍና፣ ሳይንሶች፣ ታሪክ፣ ነባራዊ ሁቤታዎች፣የዓለም ውስጥ ያሉ ኃይማኖቶች እና ሌሎች ሃሳብ ጥናቶች አስፈላጊ ይሆናሉ። ለሌሎቻችን ሃሳቦች ሲገጥሙን ለመወያየት መዘጋጀት፤ በተለይም ለወዳጆቻችን ይህ ሃሳብ አስፈላጊ ከሆነ ዝግጁ መሆን አለብን። ይህ ማለት ግን በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ የምናሳልፈውን ጊዜ በመጠቀም እግዚአብሔርን ለማወቅ እና ወደ እውነት ለመድረስ አስፈላጊ ነው።
2. ***ለጸሎት ኃይል የተሰጣችሁ ሁኑ*** - በወንጌል ሥርጭት ውስጥ እንደሚያስፈልገን ሁሉ፣ በምከካቴ እምነት ውስጥም ጥያቄዎች በትሕትና እና በአክብሮት ለመመለስ ጸሎት አስፋላጊ ነው።

3. **የትሕትናን ኃይል አስተውሉ** - ኩራተኝነት እና አውቃለው ባይነት ክፉ እና የማይጠቅሙ ባሕርያት ናቸው ፡፡ ለጥያቄዎች በመስጠት ለመመለስ ትሕትናን መጣል የለብንም፤ ትሕትና ማለት ሁሉንም እንደማናውቅ ማመሳከርያ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ “ጥሩ ጥያቄ፤ መልሱን ግን አላውቀውም” ልንሰጠው ከምንችላቸው አስፈላጊ ምላሾች መካከል አንዱ ነው፡፡
4. **የጥያቄን ኃይል ተጠቀሙ** - ሰዎችን የፈለጉት ሊጠይቁ እናንተም ለመመለስ መዘጋጀታችሁን ማሳወቅ እጅግ መልካም ንግግርን የመጀመሪያ ቦታ ነው፡፡፡ በተለይም ጥያቄን መጠየቅ የሚወዱ ወይ የሚፈልጉ ሰዎች ምናልባትም በጥያቄዎቻችሁ የሚያሳዝኑኃችሁ ከመሰላችው ላይጠይቁ ስለሚችሉ፤ ፈቃደኝነት አሳዩ፡፡ በተረፈ የራሳችሁ ለመጠየቅ አትፍሩ፣ ውይይት አንድ ሰው ንግግር ብቻ አይደለም ሁለታችሁም መጠየቅ እና መመለስ ትችላላችሁ፡፡ ሰዎች የሚሰቡት/ የሚጠይቁት ነገር የማይረባ እንደ ሆነ እንዲያስቡ በማድረግ በውይይት ውስጥ ጥያቄ መጠየቅ እንዲፈሩ ማድረግ የለብንም፡፡ኢየሱስ በአገልግሎቱ ውስጥ ጥያቄ በመጠየቅን ይወድ ነበር፤ ምላሽ ከሰጠበት የጠየቀበት ጊዜ ይበዛል፡፡

ማንም ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በክርክር ገብቶ አያውቅም ወይንም ክርክር ስለተሸነፉ የክርስቶስ ተከታይ ሆነው አያውቁም ነገር ግን በትሕትና እና በአክብሮት የሚደረግ የምካቴ-እምነት ውይይት ሰዎችን ወደ ክርስቶስ መስቀል ያቀርባቸዋል፡፡

**ውይይት** (20 **ደቂቃ**)

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች/ ሃሳቦች ተወያዩባቸው**

- ሰዎች የሚጠይቁትን ጥያቄ በአክብሮት መቀበል የሚያስፈልገው ለምንድን ነው?
- የምካቴ-እምነት ገደቦች ምን ሊሆኑ ይችላሉ?
- ወንጌልን ስታካፍሉ ለሚመጡባችሁ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ዝግጁ ናችሁ?
- ምካቴ-እምነት ጥናት አምልኮ ሊሆን የሚችለው እንዴት ነው?

*“ምካቴ-እምነት ግብዓት ነው፤ በዘመነው ዓለም ውስጥ ሃሳቦችን ከሰው ሕይወት ጋር ማዛመድ የምካቴ - እምነት አቀንቃኝ ሥራ ነው፡፡ ይህ ማዛመድ ከሌለ ፅንሰ ሃሳቦች፣ ፅንሰ ሃሳብ ብቻ ሆነው፤ ረቂቅ ሃሳቦችን በአየር ላይ ተንቀልጥለው ከሰው ሕይወት ጋር ሳይዛመዱ ይቀራሉ”*

*አሊስተር ማክግራዝ*

**ትግበራ** (5 **ደቂቃ**)

የሚከተሉትን በክርስትና ውስጥ ጥያቄ የሚነሳባቸው ሃሳቦችን ጊዜ ወስዳችሁ አስቡባቸው፤ አዲስን ሰው ወደ ክርስቶስ መስቀል መንገድ የጀመረን ሰው መምራት የምንችልበት ይሆናል

- እግዚአብሔር ማን ነው?
- ሳይንስ ክርስትናን ሀሰተኛ እንደ ሆነ አላረጋገጠምን?
- ታላቁ ፍንዳታ እና ዝግመተ ለውጥን እንዴት ታስረዳላችሁ?
- እግዚአብሔር መልካም ከሆነ መከራ በምድር ላይ እንዲሆን ለምን ይፈቅዳል?
- መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ስዕተቶች እና የሚቃረኑ ነገሮች የሉንም?
- እግዚአብሔር እውነት ከሆነ፤ ራሱን ለምን እራሱን አያሳይም?
- አንድ ፍፁም እውነት በምድር ላይ የለም፤ ስለዚህ ሁላችንም የፈለግነውን ማመን አንችልም?
- እኔ መልካም ሰው ነኝ..... መኖሩን ባለማመኔ ብቻ ለምን ወደ ሲዖል ይልከኛል?
- ከሌላው እምነት ለምን ክርስትናን እመርጣለው?
- በታዕምራት ታምናለህ?

**ጸሎት**

ከሰማይ የሚመጣ ጥበብን ጥያቄዎችን እና የዓለም ችግሮችን በትሕትና እና በፍቅር እንዲሁም እግዚአብሔርን በታማኝነት እና በድፍረት በመወከል መመለስ እንድትችሉ ጸልዩ፤ እግዚአብሔር የተከፈተ አዕምሮን እና የሚቀበሉ ልቦችን እንዲሰጠን መለመን አለብን፤ ይህ ማለት ግን ጥሩ እና አመክኖያዊ የሆነ መልስን ማካፈላችን ሰዎቸን ወደመዳን አያመጣም።

**ተጠያቂነት** (15 **ደቂቃ**)

የተጠያቂነት ቅጽ በመሙላት ለአጋራችሁ እና ለአነስተኛ ቡድናችሁ አጋሩት እንዲሁም አንዳችሁ ለሌላችሁ ጸልዩ።

## ተጨማሪ ክፍል፦

## የወንጌል አስተምሮ

አንተ አጋጣሚ አይደለህም፤ ፍፁም እና ቅዱስ በሆነው እና አለማትን ሁሉ ደግፎ በሚይዘው  በእግዚአብሔር (አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ) አምሳል በእርሱ የተፈጠርክ ነህ (ዘፍጥረት 1)።

ሁላችንም በፈጣሪያችን መንገድ ከመከተል በራሳቸን በመንገድ በመሄድን በመምረጣችን እግዚአብሔርን ክደናል (ኃጢአትን ሰርተናል)። በዚህ ምክንያት ወደ ዓለም መከራ እና ችግር የተሞላች ሆነች፤ ይህ ኃጢአትን እንዲሁ የማይተወውን ወይም የማይረሳውን ነገር ግን እንደሚገባ የሚቀጣውን እግዚአብሔርን ያሳዝነዋል (ሮሜ 3፡23)።

የዓለም ንጉሥ በሆነው በእግዚአብሔርን ከከዳን እና በእርሱ ላይ ካመፅን በኋላ ነገሮችን በራሳችን ማስተካከል አንችልም። እግዚአብሔርን መክዳት ሕይወትን ራሱን መክዳት ነው፤ በመሆኑን የተረፈን ዘላለማዊ ሞት ነው። ሕይወትን መክዳታችን እና የእግዚአብሔርን ትክከለኛ ሕይወት ገደብ በማለፋችን የተሰጠን ቅጣት ሞት ነው(ሮሜ 6፡23)።

እግዚአብሔር ግን ማንም ሞትን እንዲቀምስ አይፈልግም፤ እርሱ ራሱ ፍቅር ነው፤ ደግሞም ከሰው፣ ከሚወዳቸው ልጆቹ ጋር ዘላለማዊ ግንኙነት እንዲኖረው ስለሚፈልግ ሰዎችን የሚድንበትን  ተልዕኮ ጀመረ (1 ጢሞቴዎስ 2፡4-6)።

እግዚአብሔር ልጁ ኢየሱስ ክረስቶስን ሰው ሆኖ ወደ ምድር እንዲመጣ ላከው፤ ኢየሱስም ፍፁም የሆነ አባቱን ያልካደ ሰው ሕይወትን ኖረ። ኢየሱስም እኛ እግዚአብሔርን በመካዳችን ለእኛ የሚገባውን ሞት እኛን ተክቶ በመስቀል ላይ ሞተልን (ዮሐ. 3፡16፣ ሮሜ 3፡23-25)

ኢየሱስን በሦስተኛው ቀን ከሙታን በመነሳት የሞትን ቀንበር ሰበረ፤ አዲስ ሕይወት የሚገኘው እምነታችንን በክስቶስ በማድረግ እና የኃጢአታችንን ስርየት በመለመን ነው (ምሳሌ 28፡13፣ ኤፌ. 2፡1-10፣ 1 ዮሐ. 1፡ 7-9)።

በኢየሱስ ሞት እና ትንሣኤ መታረቅን፣ መፅደቅን፣ስርየትን እና የክፋትን መሸነፍ አገኘን። ኃጢአታችን በክርስቶስ ላይ ሆኖ የእርሱ ጽድቅ ለእኛ ሆነልን። በዚህ ውስጥ ከእኛ የሚጠበቀው እምነታችንን በክርስቶስ ላይ ብቻ በማድረግ እግዚአብሔር ከሞት እንዳስነሳው ማመን ነው፤ መዳን በማመን ብቻ ነው (ማቴ. 20፡8፣ ሮሜ 10፡9፣ 2 ቆሮ. 5፡18-21፣ ዮሐ. 12፡31፣ ቆላ. 2፡15)

ከሰማያዊ አባታችን ጋር የታደሰ ግንኙነት ማድረግ የምንችልበት መንገድ አግኝነተናል፤ አሁን በእርሱ ሰላም ያለን እና ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብነት መቀቀላቀን ችለናል። ለአሮጌው ማንነታችን ሞተን ለአዲሱ ሕይወትን አግኝተናል (ሉዋ 9፡23፣ ቆላ. 1፡20፣2፡13-14፣ ሮሜ 5፡1-2፣ ገላ. 4፡4-7)

ኢየሱስ ወደ ሰማይ ተመልሶ በአባቱ ቀኝ ተቀምጦ ይመራል ፤ በምድር ላለን ተከታዮቹ እንደሚገባው በሙላት እንድንኖር እና የእርሱን መልካም ዜና ለዓለም መናገር እንድንችል መንፈስ ቅዱስ ዐቅም አንዲሆነን ልኮልናል። ወደ ፍሬያማነት የሚመራ መንፈስ ቅዱስ የሆ አዲስ ፍጥረት- ደቀመዛሙር - ልውጠትን አግኝተናል። የእግዚአብሔር እንደራሴዎች በመሆን የሰላም መንግሥቱ ተወካዮች፣ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ታሪክ በሥራ እና በተግባር ምስክሮች ሖነናል (ሚክያስ 6፡8፣ ሐዋርያት ሥራ 1፡8፣ 2ቆሮንቶስ 5፡11-21፣ ገላትያ 5፡22-23)

አንድ ቀን ኢየሱስ በህያዋን እና በሙታን ላይ ሊፈርድ ተመልሶ ይመጣል።የእግዚአብሔር ፍፁም መንግሥት የምትታደስ ስትሆን እምነታቸውን በክርስቶስ ኢየሱስ ያደረጉ ሰዎች ሁሉ ከአባታቸው ጋር የዘላለም ህይት ይጠብቃቸዋል፤ ለማያምኑት ግን የዘላለም ሞት ይጠብቃቸዋል። መልካ ዜና ማንም ሰው የዘላለምን ሞት መሞት የለበትን ነገር ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን የዘላለም ሕይወት እና ተስፋን መውረስ ይችላሉ (1 ቆሮ. 15፣ ራዕይ  21፡1-8፣ 22፡1-5)

## ተጨማሪ ክፍል

## የወንጌል ትረካ

እግዚአብሔር ከዚህ ሁሉ ነገር በፊት በራሱ አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ በፍፁም አንድነት ይኖር ነበር። እግዚአብሔር እጅግ መልካም የሆነን ዓለም ፈጠረ በዚህ በፈጠረው ዓለም ውስጥም ከነበረው የሰው ልጅ ጋር መልካም ኅብረት ነበረው። ሕይወት እና የአለማት ንጉሥ ከሆነው ከራሱ ከእግዚአብሔር ጋር መልካም ኅብረት እንዲኖረን የተፈጠርን ነበርን። እግዚአብሔር ግን ሰዎች እንዲወዱት አላስገደደም ነገር ግን ለሰው ልጅ ምርጫን ሰጠው፤ በዚህ ነጻ ምርጫ የሰው ልጅ እግዚአብሔርን ለመተው እና በራሱ መንገድ ለመሄድ መረጠ።

የአለማትን ንጉሥ መክዳት ሀገር የመክዳት ወንጀል ነው፤ ይህ ሕይወትን አልፈልግም ብሎ የመክዳት ነው። ሞት፣ መከራ እና ችግር በዚህ ምክንያት ወደ ዓለም ገቡ፤ የሰው ልጅ ራሱን ፍጹም ከሆነው አባቱ ጋር መመለሻ በሌለው መልኩ ተለያየ። እግዚአብሔር ይህንን ክህደት መተው አይችልን፤ ይህንን ካደረገ በእርሱ ዘንድ ፍትህ አይኖርም። ፍፁም እና ጻድቅ የሆነው አምላክ ለተፈፀመው አመፅ ፍርድን መስጠት አለበት፤ ይህን በሕይወት ላይ ለተፈጸመ ክህደት ፍርዱ ሞት ነው።

እግዚአብሔር ግን ዓለምን ከመውደዱ የተነሣ - ፍቅሩን እና ሕይወቱን በሙላት ለዘላለም ማወቅ እንዲሆንልን የሰውን ልጅ ከሞት የማዳን ሥራ ጀመረ። እግዚአብሔር ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን በምድር ላይ ፍፁም ሕይወትን እንዲመራ ልኮታል ይህ ሕይወት በእግዚአብሔር ላይ የማያምጽ እና ምንም ኃጢአት የሌለበት ሕይወት ነው።

ኢየሲስ ለሰው ልጅ ከአመፁ የተነሣ የሚገባውን ሞት በእኛ ፈንታ በመስቀል ላይ በፈቃደኝነት ወሰደልን። ከሦስት ቀን በኋላ አምላክ የሆነው ክርስቶስ ሞት ሊይዘው ስላልቻለ ሞትን ድል ነሥቶ ተነሣ። በዚህ ጊዜ አመፃችን ምሕረትን ብቻ ሳይሆን በክርስቶስ ኢየሲስ ያለውን ዘላለማዊ ሕይወት የመካፈ ዕድል ሆነልን። የሞት እርግማን ተሰበረ።

ኢየሱስ "የሞተ እና ሞትን ድል ነሥቶ የተነሣ የዓለም አዳኝ እና የአለማት ንጉሥ ነኝ" የሚለውን ብቻ ማመን ነው ከእኛ የሚጠበቀው፤ በእርሱ ለሚታመኑ ሁሉ ድነት እና ሕይወት አለ፤ እንዲሁም የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ልንኖረው የተፈጠርንለን ሕይወት - ይኸውም እግዚአብሔርን መልክ በመምሰል ሰውን ሁሉ ወደዘላለም ሕይወት መጋበዝ ነው ፤ ይህንንም የምንኖርበትን ዐቅም ይሰጠናል። ለድሮው ሕይወታችን እየሞትን ወደ አዲሱ ማንነታችን ዳግም እንወለዳለን። አንድ ቀን ኢየሱስ ዳግም ይመጣና የእግዚአብሔርን ፍፁም መንግሥት ያድሳል። በእርሱ የሚያምኑ ሁሉ በእርሱ መንግሥት ውስጥ ለዘላለም ይኖራሉ በመሆኑም ይህንን የዘላለም ተስፋ እና የእግዚአብሔር ፍቅር ሰዎች አውቀው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንዲፈልሱ ተጠርተናል።

---

## ተጨማሪ ክፍል ፡

### የ10 ደቂቃ የወጣቶች ወንጌል- ውይይት ምሳሌ

#### አንድ፡ አንተ አጋጣሚ አይደለህም

ብዙ ሰዎች በምድር ላይ በአጋጣሚ የመጡ እንደሆኑ ያምናሉ፤ እነሱ በምድር ላይ ያሉት በድንገት በተከሰተ ዓለም ላይ ከጥቂት ቢሊየን አመታት በኋላ ሰዎች ወደ መኖር ስለ መጡ እንደ ሆነ ያስባሉ። ይህ ግን ምንም ትርጉም አይሰጥም እንዲሁን ስለሕይወት አላማ ሆነ ተስፋ አይሰጠንም።

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ከሁሉ በፊት የነበረ እና ለዓለምን ሁሉ ፍቅሩን ሊያካፍን ከመፈለጉ የተነሣ በእርሱ የተፈጠረን ሰዎች እንደሆንን ያስረዳል።

ስለዚህ አንተ አጋጣሚ አይደለህም ነገር ግን በእግዚአብሔር በአላማ እና በፍቅር የተፈጠርክ የእጁ ሥራ ነህ።

**ሁለት- ነጥቡን ስተሃል**

ሰዎች እግዚአብሔር እንደፈጠራቸው እና እንደሚወዳቸው ስለማያውቁ የሕይወትን ሁሉ አላማ ይስታሉ። እግዚአብሔርን ማወቅ ማለት ሕይወትን እንደሚገባ መኖር ማለት ነው ይህም ማለት - ከፈጣሪያችን ጋር በወዳጅነት - ከሚወደን፣ መልካም፣ መሃሪ፣ ባለጠጋ፣ ታጋሽ እና ጠቢብ ከሆነ መለኮት ጋር ኅብረት ሲኖረን ነው። መጽሐፍ ቅዱሳችን ስለፍጹም እና ለልጆቹ መልካምን ነገር ስለሚፈልግ እግዚአብሔር ይነግረናል።

እግዚአብሔን አለማወቅ ማለት ወደ ዓለም ዋንጫ ሜዳ ላይ ለዋንቻ ጨዋታ ገብተን፤ ነገር ግን የገባንበት ሜዳ ላይ የጎል መረብ ሳይኖር ሲቀር ማለት ነው። ማንም ሰው ጎል የማያገባበት እና ማንም ዋንጫ ሙብላት የማይችልበት ጨዋታ ይሆናል።

**ሦስት - ሕይወትን በሙላት ማወቅ ትችላላችሁ**

ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ግንኙነት ውስጥ ነጥቡን ስንስት እግዚአብሔር ለእኛ ያዘጋጀውን መልካሙን ሕይወት እያጣን ብቻ ሳይሆን የአለማት ንጉሥ የሆነው እግዚአብሔር ላይ ፊታችንን እያዞርንም ነው።መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን ሕይወትን ያዘጋጀልንን እግዚአብሔርን ስንተው እና ከእርሱ ይልቅ ሕይወትን እንዴት መኖር እንዳለብን ያወቅን ሲመስለን ነው ክፉ የሆኑ ነገሮች ወደ ዓለም መግባት የሚጀምሩት። መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን ኃጢአት ይለዋል፤ ምናልባት ሌላው ልንረዳበት የምንችልበት መንገድ ራስ ወዳድነት በሚል ነው። ከእግዚአብሔር መንገድ ይልቅ እኛ ለራሳችን ያወቅን ይመስለናል፤ እግዚአብሔርን "ካንተ እሻላለው፣ ካንተ የበለጠ አውቃለው እና አታስፈልገኝም" ማለት ነው።ምን ያህል የተበላሸ ዓለም ላይ እየኖርን እንደ ሆነ ለማወቅ ዜናን መመልከት ብቻ ነው የሚያስፈልገን፤ ሰዎች የሕይወትን ዋና ነጥብ መሳታቸው ይህ ነው- ከአፍቃሪ እና መልካም አባታችው ይልቅ ለራሰው መኖር መምረጥ ነው።

ይህ ክህደት በእኛ እና በእግዚአብሔር መካከል ገደብን ይፈጥናል- ሕይወትን ከሚሰጠው ከእግዚአብሔርን ስንከዳው የሚቀረን ሞት ብቻ ነው።

እግዚአብሔር ግን እንድንሞት አይፈልግም - እግዚአብሔር ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስን ሰው አድርጎ ልኮታል- አምላክ በሰው ሆኗል- ፍፁምንም ሕይወት በመካከላችን **ኖሯ**ል። ይህም ሕይወት ለእኛ ሕይወትን በሚገባ እንዴት መኖር እንደሚገባን ለማሳየት ነው። እግዚአብሔርን ስንከዳው በሕይወታችን የምንከፍለው ቅጣት አለ።

ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሲሞት ሁላችንም እግዚአብሔርን በመካድ መረጥነውን ሞት ነው የሞተልን፤ እርሱ የእኛን ቅጣት ወሰደልን።

ከሦስትም ቀን በኋላ ሞተን ድል ነሥቶ ተነሣ፤ እርሱ መለኮት ነው ሞት ሊዘው አይችልም።ይህን ለሃጥታችን ንስሃ ስንገባ እግዚአብሔር ኃጢአታችንን የሚምር እና ወደ ሕይወት እንደሚመልሰን ማሳያ ነው።

**አራት - የሕይወትህን መሪ የያዘው ማን ነው?**

"ዘ ቢድ ባንግ ቲዮሪ" የሚል ተከታታይ ፊልም ላይ ሼልደን የተባለ ገጸ ባህርይ በቤቲ ውስጥ ባለው ሶፋ ላይ ከእርሱ በስተቀር ማንም ሰው የማይቀመጥበት ቦታ አለው። እኛም በሕይወታችን እንዲሁ እንሆናለን እግዚአብሔርን "ይህ የሕይወቴ ክፍል ላይ እንድትቀመጥ አልፈልግም" እንለዋለን።እግዚአብሔር ግን በፍቅሩ ውስጥ እውነትን እንድናውቅ ይፈልጋል እርሱ እኛን ፈጥሮናል፣ ይመራናል፣ ይረዳናል፣ በሚገባው ቦታ መቀመጥ አለበት- በሕይወታችን መሪ ላይ።

ብዙዎቻችን የሕይወት ትርጉም አይገባንም፤ ድብርት፤ ራስን መጥላት፣ የሚገባ የመመገብ ችግር፣ ውስጥ እንዋዥቃለን። በመስታወት ውስጥ በምንመለከተው ሰው ደስተኛ አይደለንም፤ በሕይወታችን በምንም መሥራት የማንችል እንደ ሆነ በማመን ሃዘንተኞች እና የተጨናነቅን ነን

እግዚአብሔር እነዲህ ይላል "ነጥቡን ሰስታችሁታል፤ ወደ እኔ ተመለሱ፣ እኔን ስለመካዳችሁ ኃጥያታችሁን ተናዘዙ እኔም እምራችኋለው።መታመናችሁን በእኔ አድርጉ ሙሉ እና እውነት የሆነን ሕይወት እሰጣችኃለው ፤ ሞትንም አትቀምሱም "

አጋጣሚ አይደላችሁም፤ በእግዚአብሔር የተወደዳችሁ ናችሁ። እግዚአብሔር ግን እርሱን እንድትመርጡት አያስገድዳችሁም፤ ወደ እግዚአብሔር በመመለስ እርሱን ምረጡ እና እውነተኛ ሕይወትን እወቁ።

## ተጨማሪ ክፍል ፡

## የወንጌል መንገዶች

አራቱ መንፈሳዊ ህጎች

4laws.com

የቢል ብረይት የወንጌል መሠረታዊ ሃሳቦች ማብራሪያ

አራቱ-ነጥቦች

The4points.com

ለወጣቶች የተዘጋጀ አራቱ መንፈሳዊ ህጎች ማብራሪያ

ሦስቱ ክቦች

የተለያዩ የዩ-ቲዩብ ምሳሌዎች

አጭር እና ማንም ሰው ደግሞ ሰርቶ ሊሳያቸው የሚችሉ የወንጌል ማብራሪያዎች

## ተጨማሪ ክፍል ፡

## "አንድ - ጉዳይ" ጽሑፎች

ጥቂት ታዋቂ ወንጌላውያን ወንጌልን መስበክ ከመጀመራቸው በፊት ብናውቀው ኖር ብለው የተመኙት አንድ ነገር የዘረዘሩት ጽኁፈ ነው። ለቡድን ውይይት፣ ለግል የቤት ሥራ ንባብ ሆነ ወንጌላውያን በራሳቸው ለመበረታታት እንዲያነቡ የተቀመጡ ጽኁፎች ናቸው።

### አንድሪው ፓሉ ሉዊስ ፓሉ ማኅበር

**"በእምነት አንጂ በዕይታ አትራመድ"**

2 ቆሮንቶስ 5፡7

አባቴ ሉዊስ ፓሉ አነዚህ ቃላት ደጋግሞ ሲናገራቸው ትዝ ይለኛል ፤ የንግግሩ ዘዬ፣ የነበረው ስሜት፣ ጥልቅ ሆነ መሰጠቱ፣ ለክርስቶስ ያለው መታዘዝ ከመጀመር እስከ መጨረሻ ድረስ የነበረው የእምነት ጎዞ ትዝ ይለኛል። አባቴ ለኢየሱስ ክርስቶስ የነበረውን መሰጠት የነበረው ደስታ ይህም አገልግሎቱ እና በሕይወቱ ለእኔ ምልክት/ ሞዴል ሆኖ አል፥ል። ይህ የኢየሱስ ተከታይ የመሆን ጉዞ - መጠራታችን ምንም ቢሆንም ለክርስቶስ ታዛዣ መሆን አለብን። ይህንን ቀድሜ ባውቀው ደስ ይለኝ ነበር፤ ይህንን ለማወቅ 27 ዓመታት ፈጅቶብኛል።

አባቴ ይህንን እውነት በፍፁም ኖሮታል፤ ከአርጀንቲና የመንገድ ላይ ሰባኪነት ጀምሮ እስከ አሁን በደረጃ አራት የሳንባ ካንሰር የኬሞቴራፒ ህክምና ውስጥ ሆኖ እንኳን በየቀኑ በእግዚአብሔር ላይ መታመን እና እርሱን ማድመጥ ይለማመዳል።

የአባቴ የሚወደው ግጥሞች መካከል የሲ.ቲ. ስተድ ግጥም አንዱ ነው "ይህ የሚያልፍ አንድ ሕይወት ነው/ለክርስቶስ ብቻ የተኖረው ሕይወት ብቻ ነው ዋጋ ያለው"፤ ይህንን ግጥም ከነገረኝ በኋላ አባቴ ሁልጊዜ እግዚአብሔር በምድር ላይ ያለውን ሕይወት ሲያልቅ የሚጠይቀን ጥያቄ ያስታውሰናል

"በሰጠዋችሁ ሕይወት ምን አደረጋችሁበት፤ ከራሳችሁ ጋር ማንን ይዛችሁ መጣችሁ?"

ይህ አስቸጋሪ እና አስፈሪ ጥያቄ ነው፤ ዘላለም ላይ ትኩረት ያደረገ እና ወንጌልን ማዕከል ያደረገ ኑሮ ለመኖር መማር. አለብን። ከባድ ወደ ሆነ ሕይወት ይመራናል፤ አሁን ግን ይህንን ተምረናል ይህ ልንኖረው የሚገባ ሕይወት ነው።

*"የክርስቶስ ፍቅር ግድ ይለናል፣ ምክንያቱም አንዱ ስለ ሁሉ እንደሞተ እርግጠኞች ሆነናል፤ ከዚህም የተነሣ ሁሉም ሞተዋል። በሕይወት ያሉት ለሞተላቸውና ከሙታን ለተነሣላቸው አንጂ ከእንግዲህ ለራሳቸው እንዳይኖሩ እርሱ ስለሁሉ ሞተ"*

2 ቆሮንቶስ 5፡14-15

ወንጌልን መስበክ ለምንችልለው ሰው ሁሉ መስበክ መቻል አለብን። ወንጌልን ለማወጅ የተሰጠን መሆን አለብን፣ ለኢየሱስ ክርስቶስ የምንችለውን ያህል ሰዎችን ማሸነፍ አለብን፤ ይህንንም ቤተ ክርስቲያንን በማነቃቃት እና ዓለም አቀፍ በሆነ መልኩ ከተሞችን መንካት ነው።

ይህ በሕይወት ለመኖር ድንቅ ቀን ነው፤ ወንጌልን ለመስበክ ግሩም ቀን ነው፤ በታላቁ ተልዕኮ ውስጥ አብረን ወንጌልን ለመሥራት የሚያስችል ቀን ነው-ይህንን መሥራት ግን ቀላል አይደለም። እግዚአብሔርን በየዕለቱ መስማት እና በእርሱ መታመን ስንችል ምርጥን ሕይወት መለማመድ እንጀምራለን።

### ሬይ ክሮውን ዋና ሥራ አስኪያጅ፣ ሆፕ ቱጌዘር

**ሁሉም ነገር በፀጋው ነው**

ሐዋርያው ጳውሎስ በቆሮንቶስ ላሉ ምዕመናን ይህንን እሰደናቂ የሆነ ነገር ተናግሯል፤ እኑ ከሁሉም የከፋው ኃጢአተኛን ወደ ሐዋርያ አድርጓል። በነዚህ ሁለት ሰዎች መካከል ያለው ልዮነት የእግዚአብሔር ፀጋ ነው።

*“ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋ አሁን የሆንሁትን ሆኛለው፣ ለእኔም በተሰጠኝ ጸጋ ከንቱ አልሆነም፤ እንዲያውም ከሁሉም በላይ በትጋት ሠርቻለው፤ ዳሩ ግን እኔ ሳልሆን ከእኔ ጋር ያለው የእግዚአብሔር ጸጋ ነው። እንግዲህ እኔም ሆንሁ እነርሱ የምንሰብከው ይህንኑ ነው። እናንተ ያመናችሁት ይህንኑ ነው።”*

1ቆሮንቶስ 15፡ 10

አገልግሎት እንጀመርኩ የምሠራው ሥራ ስለእኔ ሆነ በእኔ ሳይሆን በጌታ ጸጋ የሚሠራ እንደ ሆነ የሚነግረኝ ባገኝ ደስ ይለኝ ነበር። የእግዚአብሔርን መገኘት እና ጥሪ ለመረዳት እጅግ አስፈላጊው ነገር “አመሰግናለው” ማለት ነው። ብዙ ጊዜ ነገሮች በተለይም ስጦታችን፣ መጠራታችን እና ክህሎቶቻችን ስለራሳችን ይመስሉናል። የሆነ ሰው አስቀድሞ ሁሉም ስለ እግዚአብሔር ፀጋ እና እኛን ለመጠቀም እና ለመባረክ የሚፈቅደው እግዚአብሔር ምርጫ ነው። እኛን ተጠቅሞ እግዚአብሔር ሌሎችን ወደራሱ ሲጠራ ይህም የሚሆነው በእግዚአብሔር ፀጋ ነው። የተሰጣችሁ ፀጋ በጥቅም ላይ ሲውል ስትመለከቱት ይህ ሁሉ የሆነው በእግዚአብሔር ነው።

በመሆኑም መረዳት ያለብን እግዚአብሔር በእኛ ሊሠራ ያሰበውን ነው የምንኖረው፤ የምናከናውነውም እግዘዓብሔር በእኛ ውስጥ ሊከውን የወደደውን ነው። ይህንን ቀድሜ ባውቅ ኖሮ ከብዙ ጭንቀት እዲሁን እኔ ብቻ እንደምገመገም፣ እንደምዳኝ እና ስለእኔ ነበር ብኣ ብዬ የነበረውን ሃሳብ እተው ነበር።

ለሚያጋጥሙኝ አገልጋዮች እና በሚገባ አገልግለው የጨረሱ በሙሉ የስኬታቸው ምንጭ በእግዚአብሔር ጸጋ ላይ መታመናቸው ብቻ ነው። ጳውሎስ ከሁሉም በላይ እንደሠራ ይህም የሆነው በክርስቶስ ፀጋ እንደ ሆነ ይናገራል። ይህ አስደናቂ የመኖር መንገድ ነው፤ የጠራንን የምንፈጽምበት ኃይል እና ስጦታ የሚቸረን ምንም መሠረት ያላደረገው የእግዚአብሔር ፍቅር ነው።በዚህ የፀጋ ስጦታ ውስጥ ስንኖር ሁሉንም ነገር ማድረግ የቻልነው ከእግዚአብሔር መሆኑን እየተረዳን በትሕትና በመንገዱ መሄድ እንችላለን።

እንደየትኛውም እውነት ሥራዬን ስጀምር ይህንን በተረዳው ኖሮ እላለው፤ አሁንም ግን ለምኖረው ኑሮ እና ለአገልግሎቴ ይህ እውነት አስፈላጊ ነው።

**ጋቪን ካልቨር** **የሚሽን ሥራ አስኪያጅ፣ ኢቫንጀሊካል አሊያንስ**

**እግዚአብሔር ትንንሽ ጥረቶቻችን በሚያስደንቅ መንገድ ይጠቀማቸዋል**

የወንጌል ሥርጭት አገልግሎቴን ስጀምር ባውቀው ብዬ የምመኘው ነገር ትንሹን ነገሬን፣ ሃሳቤን ሊሆን ይችላል ለእግዚአብሔር ከሰጠሁት ሊጠቀምበት ይችላል። መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን አስደናቂ እውነት ከተለያዩ ቦታዎች ላይ አስተምሮኛል፡ በተለይም በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 6 ላይ የ5000 ሰዎች ምገባ ነው፤ ይህ ቁጥር ላይ ሴቶች እና ህጻናትን ስናስገባ 11000-15000 ሊደርሱ የሚችሉ ሰዎች በምሳ ሰዓት ላይ ተርበው በዚህ ቦታ ላይ እናገኛቸዋለን።

አንድርያስ ወደ ኢየሱስ መጥቶም *“አምስት ትንንሽ የገብስ እንጀራ እና ሁለት ትንንሽ ዓሳ የያዘአንድ ልጅ እዚህ አለ፤ይህ ግን ለዚህ ሀሁሉ ህዝብ እንዴት ይጋረሳል።”* (ዮሐ. 6፡9)ላይ ሲጠይቅ እመለከተዋለን። እንድርያን ይህንን ያህል ትንሽ የሆነ ነገር እንዴት እንደሚዳረስ ባያውቅም፤ ነገር ግን መንፈሳዊ የሆነ መረዳት ቢጎድለውም ድንቅ ሊያደርግ ወደሚችለው ኢየሱስ አቀረበው። የቀረበው ምግብ ለሰው ሁሉ ቀርቶ ለአንድ የተራብ ሰው እንኳን የማይበቃ ነው፤ ነገር ግን ታዕምራትን ማድረግ የሚችለው ኢየሱስ ጋር አቀረበ።ውጤቱን ኢየሱስ በሜዳ ላይ ተንሰታፍቶ የተቀምጠው የህዝብ መገቦ ብዙ ተረፈ። እንድርያስ እንደሌሎቹ ሁሉ የተደነቀ ይመስለኛል፤ ነገር ግን ይህ ኢየሱስ ትንሽ የሆነው ነገር ወስዶ ትልቅ ማድረግ እንደሚችል ተረድተዋል።

ዛሬ ላይ ላለነው ወንጌላውያን ይህ እውነት ነው፤ ያለንን ትንሽ ነገር ስንሰጠው እና ባለን አናሳ ግብዓት ኢየሱስ ብዙ ትልልቅ ነገሮችን መሥራት ይችላል።ግልጹ እና ቀላሉ እውነት ይህ ነው ኢየሱስ ከእኛ ጋር ከሆነ የትኛውንም ነገር ማድረግ ይቻላል።

በዚህ ምክንያት ምንም የምንሰጠው ነገር እንዳለን ባናስብም፣ ማንም ምላሽ የሚሰጥ በማይመስለን ጊዜ ውስት ያለንን ጥቂቱን ነገር ወደ እግዚአብሔር ማምጣት ይኖርብናል። የትንሹን ልጅ ትንሽ ምሳ ወስዶ ሺዎችን እንደመገበበት የእኛን ትንሽ የወንጌል ሥራ በመውሰድ ሚያስደንቅ መንገድ ይጠቀምበታል። በእኛ ጥቂቱ ጥረት የሰዎችን ሕይወት በዚያው ጊዜ እና ቦታ ላይ መቀየር ይችላል።

ራሳችንን ከሌሎች ጋር ማስተካከል ማቆማችን እጅግ አስፈላጊ ነው፤ አንዳንድ ሰዎች ወነጌልን ተናግረው በባቡር ላይ፣ ፓርክ ውስጥ ሰዎችን ወደ ጌታ መምራት እንደቻሉ አንሰማለን ፤ እንደዚህ አይነት ምስክርነቶች እኛ ምንም መሥራት እንደማንችል ራሳችንን እንድንቆጥር ያደርጉናል።ራሴን ግልጽ ላድርግላችሁ፣ እኛ እራሳችን የእግዚአብሔር ፀጋ ምልክቶች ነን እንጂ ለፊልም ሥራ ታሪክ የምንሰበስብ ሰዎች አይደለንም።

ሁል ቀን ባለን እንቅስቃሴ የምናመጣው ለውጥን መመልከት በዚያ መደሰት ነው እንጂ የሚገባን ካይሮስ - ወይንም በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ የተመደበውን ጊዜ የተሠራን ሥራ መመልከት አለብን። ሁላችንም ዛሬ ያለንን ትንሽ ነገርወደ ኢየሱስ ይዘን ስንመጣ እርሱ ይህንን ትንሽ ነገር ተጠቅሞ ብዙዎችን ወደራሱ ማምጣት ይችላል።ስለዚህም እያንዳንዳችን ያለንን ትንንሽ ስጦታ ወደ ኢየሱስ ይዘን በመምጣት እርሱ የብዙ ሰዎችን ሕይወት ሊለውጥበት ይችላል፤ ይህንን ቀድሜ ብረዳ አመኝ ነበር።

## ሬይቸል ጆርዳን ዎልፍ ዘ ቸርች ኦፍ ኢንግላንድ

**ተነስ እና መሄድህን ቀጥል**

የዛሬ 28 ዓመት ጆርጅ ቨርወር የተባለ ሰው ወጣቶችን ለዓለም ወንጌል ሥርጭት ሲጠራ፤ ራሴን ለዚህ አገልግሎት ሰጠው፤ ከ28 ዓመት በኋላ በዚህ አገልግሎት መሰጠት ውስጥ ነኝ ዛሬም ያለሁት፤ ስለዚህ ዛሬ የምነግራችሁ ባውቀው ኖሮ የምለውን ሳይሆን"አንድ ሰው ነግሮኝ የጠቀመኝ ነገር" ነው የማካፍላችሁ

ቨርወር "ሪቮሉሽን ኦፍ ላቭ" በሚለው መጽኃፉ ላይ ሲናገር

*" በዚህ አስደናቂ የዓለም ወንጌል ሥርጭት ሥራ ላይ ለእግዚአብሔር ማራቶን ሯጭ እንድትሆኑ አበረታታለው፤ ስትጣሉ ተነስታችሁ ወደ ሩጫው ተመልሳችሁ ተቀላቀሉ። ስትወቅቁ ተነሱ፣ ልክ እጃችሁ መሬቱን ሲነካው ተመልሳችሁ ተነሱ ፤ የሆነ ቀን ምናአልባትም ከሃያ ወይም ሠላሳ ኣመት በኋላ ልክ እንደኔ ራሰችሁን አሁንም በሩጫው ውስጥ ታገኙታላችሁ፤ አንዳንዴ ትደክማላችሁ፣ አንዳንዴ ትጎዳላችሁ ነገር ግን ለኢየሱስ ክርስቶስ፣ ለእግዚአብሔር መንግስት፣ ዓለም በወንጌል መደረስ እንዳለበት አስታውሱ"*

ስለዚህ አድቫንስ 2020 ቡድን ሥራ እጅግ ደስተኛ ነኝ የቬርወርን ማበረታታት 30 ዓመት ስለሞላው ለአዲስ ትውልድ ደግሞ መስጠት አስፈላጊ ነው። ነገሮች ይበላሹብሃል፤ ይህ ጉዞ አድካሚ ሆኖ ታገኝዋለሽ- ትልቁ ሚስጥር ግን መነሳት እና ጉዞውን መቀጠል ነው ። እናንተም ደግሞ ከ30 ዓመት በኋላ ይህንን መልዕክት እና ማበረታቻ ለሚቀጥለው ትውልድ ታሻግራላችሁ "መንዝ መቀጠላችን ነው የሚቆጠረው"....ትቀጥሉ ይሆን?

*"ይህንን ሁሉ አግኝቻለው ወይም ፍፁም ሆኛለው ማለት አይደለም፤ ነገር ግን ክርስቶስ ኢየሱስ እኔን ለራሱ ያደረገበትን ያን፣ እኔም ለራሴ ለማድረግ እጣጣራለው...የኃላዬን ያለውን እየረሳው ከፊቴ ወዳለው እዘረጋለው። እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ ወደላይ ስለ ጠራኝ፤ ሽልማትን ለመቀናጀት ወደ ግቡ እፈጥናለው። "*

ፊል. 3፡12፥14

## ስቲቭ ሁፓል ዋና መሪ. ኦል ኔሽንስ ቸርች ውልቨርሀንፕተን

**መጽሐፍ ቅዱስን ስበኩ**

ለ31 ኣመታት የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል የመስበክ ትልቅ ዕድል አግኝቻለው። ወደ ታዳጉ ዕድሜዬ ተመልሼ ራሴን የምመክረው አንድ ምክር መጽሐፍ ቅዱስን ብቻ ስበክ ብዬ ነው። ለስብከታችን ኃይልን የሚሰጠው እግዚአብሔር ቃል በድፍረት መሰበክ እንደ ሆነ እራሴን እመክረዋለው፤ የሚከተሉትን ለራሳችሁ አድርጉ

**መጽሐፍ ቅዱስን በየዕለቱ አንብቡ ፡** በዚህ እግዚአብሔር ቃልን መውሰድ ውስጥ ልምምዳችሁን አዳብሩ። በትንሹም ቢሆን የሚነበብ የእግዚአብሔር ቃል በሕይወታችሁ ውስጥ ኃይልን ሊያስታጥቃችሁ፤ ሊያሳድጋችሁ እና ሊለውታችሁ ይችላል። መጽሐፍ ቅዱስ እናንተንም እንደሚያነባችሁ እንዳትረሱ - እንደጌታችሁ እንድርሆኑ በእናንተ ውስጥ መቀየር ያለበትን ነገር ይገልጠዋል።

**ጥሩ ስብከቶችን አዳምጡ፡** በቀጥታም ሆነ በተቀረፀ መልኩ እንደ ምግብ ነፍሳችሁን፣ መንፈሳችሁን እና አዕምሮዓችሁን በመመገብ የምታስቡበትን መንገድ የሚሠራ እና ዓለምን የምትመለከቱበትን መንገድ ይሠራሉ። ትሑታን እና በሚማር. ልብ የእግዚአብሔርን ቃል ማድመጥ።

**መጽሐፍ ቅዱስ አጥኑ-** *መጻሕፍትን፣ ሃሳቦችን፣ ቃላትን፣ ገፀባሕርያትን ወስዳችሁ በጥልቀት አድምጡ። መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት የበለጠ በጥልቀት እና ሥራችሁ እንዲጠነክር ይረዳል። መጽሐፍ ቅዱስን በመደበኛነት ማጥናት በሕይወታችሁ፣ በየጥቂት ቀናት ወይም በሳምንት አንድ ቀን በሕይወታችሁ ጉዞ ውስጥ አስገቡ።*

**የምጽኃፍ ቅዱስ ጥቅሶችን፣ ክፍሎችን፣ ምዕራፎችን ወይም ሙሉ መጻሕፍትን በቃላችሁ ያዙ፡** ይህ በመመጀመሪያ ስትሰሙ የሚከብድ ይመስላልበመንፈስ ቅዱስ ዕርዳታ ግን ማድረግ ትችላላችሁ።በምትስበኩበት ጊዜ ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይ መጥቀስ መቻላችሁ ለምትናገሩት መልዕክት መንፈሳዊ ኃይል እና ጉልበት ይሰጠዋል።

**ከቅዱስ ቃሉ ውስጥ ጊዜ አሳልፉ ፡** በቀን ውሎኣችው ውስጥ የእግዚአብሔርን ቃል በአዕምሮአቻሁ እና በልባችሁ ስታስቡ ዋሉ፤ በመንገድ ጉዞ ላይ ሆነ በአልጋችሁ ውስጥ - ከእግዚአብሔር ቃል ውስጥ አንድን ሃሳብ ወስዳችሁ እሰባችሁ መንፈስ ቅዱስ እንዲያባራላችሁ እና የገባችሁን እውነት በሕይወታችሁ ውስጥ እንዲተክለው ለምኑ።

**መጽሐፍ ቅዱስን ጸልዩ፡** መዝሙር ወይም ሐዋርት ከፀለዩት ፀሎቶች መካከል መርጣችሁ መልሳችሁ ጸልዩት። የእግዚአብሔርን ቃል መልሰን ወደ እግዚአብሔርን እንደመጸለይ ሃያል ጸሎት የለም። የምትጸልዩት እንደቃሉ ስለሆነ በፀሎታችሁ ላይ ያችሁን እምነት ይጨምርላችኃል።

የሰዎች ሕይወት የመቀየር ኃይል ያለው በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ነው፤ በመሆኑም የሚገርሙ ሃሳቦችን ሆነ ታሪኮችን ከመስበክ ይልቅ የእግዚአብሔርን ቃል ስበኩ። ከሚመጣ ባጊዜ ከሚመስል ወሬ ራቁ፤ ለመስበክ የተሰጣችሁን ጊዜ የራሳችሁን ሃሳብ ብቻ በማውራት ዕድሉን አታቃጥሉት - ዘላለማዊ እና የሰዎች ሕይወት የመቀየር ኃይል ያለው የእግዚአብሔርን ቃል አካፍሉ።

---

## የንባብ ጥቆማዎች / Recommended Reading

The Gospel and Evangelism

Rapheal Anzenberger, *rediscovering the Ministry of the Evangelist*

Robert E. Coleman, *The Masterplan of Evangelism*

Mark Denver, *The Gospel and Personal Evangelism*

Mark Greenwood, *Big Yes, Little Yes, Small Maybe*

Andy Hawthorne, *Here I am; joining God's Adventurous Call To Love the World*

**Ben Jack, *The Simple Gospel***

R.T. Kendall, *Whatever Happened to the Gospel?*

Will Metzger, *Tell the Truth*

J.I. Packer, *Evangelism and the Socerignty of God*

Luis Palau, *Out of the Desert*

**Rico Tice, *Honest Evangelism***

David Watson, *I Believe in Evangelism (currently out of print but second-hand copies*

*are available cheaply through amazon marketplace)*

Tom Wright, *Simply Good News*

**Mission**

David J. Bosch, *Transforming Mission*

Peter Greer & Christ Horst, *Mission Drift*

Christopher J. Wright, *The Mission of God*

**Basic Christian Belief and Introductory Theology**

Oswald Chambers, *My Utmost to His Highest*

Wayne Grudem, *Systematic Theology: An Introduction to Biblical Theology*

George Eldon Ladd, *A Theology of The New Testament (Revised)*

Alister McGrath, *Christian Theology: An Introduction*

J.I. Packer, *Concise Theology: A Guide to Historic Christian Belief*

J.I. Packer, *Knowing God*

**John Stott, *Basic Christianity***

**The Cross and Resurrection**

Paul Beasley-Murray, *The Message of the Resurrection (The Bible Speaks Today)*

D. A. Carson , *Scandalous: The Cross and Resurrection of Jesus*

John Stott, *The Cross of Christ*

Derek Tidball, *The Message of the Cross (The Bible Speaks Today)*

**Preaching and Communication**

Brayn Chappell, *Christ Centered Preaching*

Zack Eswin, *Preaching to A Post – Everything World*

Carmine Gallo, *Talk like TED: The 9 Public Speaking Secrets of the World's Top Minds.*

Tim Keller, *Preaching: Communicating Faith in an Age of Skepticism*

Derek Tidball, *Preacher, Keep Yourself from Idols*

**The Bible**

Craig L. Bloomberg, *Jesus and The Gospels*

Gorden D. Fee and Douglas Stuart, *How to Read the Bible for all its Worth*

Gorden D. Fee and Douglas Stuart, *How to Read the Bible Book by Book*

Mark L. Strauss, *Four Portraits, One Jesus*

Peter J. Williams, *Can We Trust the Gospels?*

Get hold of a good study Bible, if you don't have one already(the majority of the major translations such as ESV, NIV, KJV, NRSV, NLT, Amplified have atleast one study version) and a roboust Bible dictionary/ encyclopedia (Baker, Eerdmans, Harper Collins, New Bible Dictionary)

**Apologetics**

Tim Keller, *The Reason for God*

Tim Keller, *Making Sense of God*

C. S. Lewis, *Mere Christianity*

Josh McDowell, *The new Evidence that Demands a Verdict*

Alister McGrath, *Mere Apologetics: How to Help Seekers and Skeptics Find Faith*

Frank Turek, *Stealing From God*

J. Warner Wallace, *Cold Case Christianity*

Lee Strobel, *The Case for Christ*

Christopher Yuan, *Holy Sexuality and The Gospel*

**Commentary**

**Basic/ Devotional :** 'For Everyone' series; 'For You' series

**Introductory :** The Bible Speaks today, NIV Application

**Intermediate :** IVP; Tyndale: Expositor Bible Commentary (Revised); understanding the Bible

**Advanced: Pillar (NT): Apollos(OT):** New International commentary: Two Horizon

**Leadership**

Ken Blanchard & Phil Hodges, *Lead Like Jesus*

Robert Greenlead and Larry Spears, *The Power of Servant Leadership*

Hoag, Rodin & Willmwe, *The Choice*

Peter Scazzero, *The Emotionally Healthy Leader*

**Online Resources**

**Reasonablefaith.org**

**Coldcasechristianity.com**

**Apologetics315.com**

**DVD/USB resources**

**Talkingjesus.org**

**Alpha.org**

**Dare2Share.org**

## የተጠያቂነት ጥያቄዎች

ቁልፍ

/ መልካም

\- ጥሩ

X መጥፎ

“እግዚአብሔር ሆይ, መርምረኝ፤ ልቤንም ዕወቅ፤ ፈትነኝ፤ ሐሳቤን ዕወቅ።”

መዝ 139፡23

እርስ በርሳችሁ ተቀባበሉ (ሮሜ 15፡7)፣ እርስ በርሳችሁ ኃጢአታችሁን ተናዘዙ (ያዕቆብ 5፡16)፣ አንዳችሁ ሌላችሁን እያበረታታችሁ አርስ በእርሳችሁ ተገባበዙ (1 ተሰሎንቁ 5፡11)

“ስለዚህ በሰማይ ያለ አባታችሁ ፍጹም እንደ ሆነ  እናንተም ፍጹማን ሁኑ” ማቴ. 5፡48

| | |
|---|---|
| በሕይወት ያለኝ አላማ ምን ያህል ግልጽ ነው? | |
| በተሰማራሁነት ሥራ ውስጥ ያለን አላማ ምን ያህል ግልጽ ነው? | |
| በምሠራው ሥራ ደስተኛ ነኝ? | |
| በምሠራው ሥራ የእግዚአብሔር ደስተኛ እንደ ሆነ ይሰማኛል? | |
| ምን ያህል በስሜት ተሰጥቼ እሠራለው? | |
| ከኢየሱስ ጋር ጥልቅ ግንኙነትን እያዳበርኩ ነው? | |
| ለጸሎት ጊዜ እያዘጋጀው ነው? | |
| በግል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜን እያሳለፍኩ ነው? | |
| መጽሐፍ ቅዱስ ዛሬ ለእኔ ህያው ነውን? | |
| በሕይወቴ እና በአገልግሎቴ የእግዚአብሔርን ኃይል ምስክርን አያለው? | |
| ኢየሱስ ለእኔ እውነት ነውን? | |
| የሚማር. እና ተጠያቂነት ያለው ሕይወት አለኝን? | |
| ለሰዎች የምገኝ እና ሊቀርቡኝ የሚችሉ ነኝን? | |
| በሚገባ አደምጣለውን? | |

| | |
|---|---|
| ለሌሎች ሰዎች በሚገባ ራሴን እገልጣለውን? | |
| በአገልጋይ ልብ እየመራው ነውን? | |
| ታማኝ ነኝ? | |
| ቃሌን የምጠብቅ ነኝ? | |
| ጤነኛ የሆኑ እይታ አለኝን? | |
| ጫናን በሚገባ እያስተናደግኩኝ ነውን? (ከሰዎች፣ ከሥራ ሆነ ከሁኔታዎች) | |
| ጤናዬ እንዴት ነው? | |
| በሚገባ እተኛለውን? | |
| አዕምሮዬን በማይገቡ ሃሳቦች ላይ እንዲዋልል እፈቅዳለውን? | |
| የታመሙትን፣ የሚቸግራችውን እና በጉዳት ላይ ያሉትን አስባለሁን? | |
| ቤተሰቦቼ ደስተኞች ናቸውን? | |
| ወዳጅቶቼ እንዴት ናቸው? | |
| ከማገለግላቸው ጋር ያለኝ ኅብረት ጤናማ ነውን?(ጓደኞች፣ መሪዎች፣ የተቃራኒ ፆታ) | |
| በምራብ፣ በደከመኝ፣ በንዴት ሆነ በብቸኝነት ጊዜ ያለኝ ምላሽ ምን ይመስላል? | |
| በማይገባ የዝሙት ሃሳብ ውስጥ እገኛለውን? | |

| | |
|---|---|
| የሚያስፈልገኝን ያህል ዕረፍት እየወሰድኩኝ ነውን? | |
| ጊዜዬን በሚገባ እየተጠቀምኩ ነውን? | |
| ያለኝን ትርፍ ጊዜ በሚገባ መንገድ አሳልፋለውን? | |
| በቤተ ክርስቲያን ፣ ሥራ እና ቤተሰብ መካከል ጤነኛ ሚዛናዊነት እየጠበቅሁ ነውን? | |
| ከማያምኑ ሰዎች ጋር ግንኙነቶችን እየመሠረትኩ እና እያሳደግሁ ነውን? | |
| ለዝሙት ለሚጋብዙ ነገሮች ራሴን እያጋለጥኩ ነውን? | |
| በየትኛውም የሕይወት ቦታ ላይ ተሸንፌያለውን ፤ቅናት፣ ንጹህ ያልሆነ ሃሳብ፣ ተቺ፣ ብስጩ፣ ቁጡ፣ የማያምን ሆኛለውን? | |
| ገንዘቤን በሚገባ አስተዳድራለውን? | |
| በደግነት ለሌሎች እሠጣለውን? | |

| | |
|---|---|
| በሰዎች ላለመቅናት እወስናለውን? | |
| ላለመነጫነጭ እወስናለውን? | |
| በሀቀኝነት እመላለሳለውን? | |
| በራሴ የምተማመን እና መወሰን እችላለውን? | |
| የሚመጣውን ለመቀበል ፈቃደኛ ነኝን? | |
| ግቦችን እያዘጋጀው ፤ እነሱ ላይ ለመድረስ እሠራለውን? | |
| መስዋትነትን ለመክፈል የተዘጋጀው ነኝ? | |
| የሚጠበቅብኝን ሁሉ ለማድረግ ዝግጁ ነኝ? | |
| በመንፈስ ኃይል እንቀሳቀሳለውን? | |
| ይቅርታን ያላልኩት ሰው አለን? | |
| ከሚያጠፉ ልምምዶች እና ሃይሎች ለመውታት ነፃነትን እፈልጋለውን? | |

*“በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን፤ በራስህ ማስተዋል አትደገፍ፤ በመንገድህ ሁሉ እርሱን እወቅ፤ እርሱም ጎዳናህን ቀና ያደርገዋል፤ በራስህ አስተያየት ጠቢብ ነኝ አትበል፤ እግዚአብሔርን ፍራ፤ ከክፋትም ራቅ።”*

*ምሳሌ 3፡5-7*